# ታሪክና ምሳሌ

## ፪ኛ መጽሐፍ

ከበደ ሚካኤል

## ፊደል

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሱ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኵ | ኲ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጕ | ጒ | ጓ | ጔ |
| ቈ | ቍ | ቊ | ቋ | ቌ |
| ኈ | ኍ | ኊ | ኋ | ኌ |

፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲
፳ ፴ ፵ ፶ ፷ ፸ ፹ ፺ ፻ ፼

965

# ታሪክና ምሳሌ

## ፪ኛ መጽሐፍ

ከበደ ሚካኤል

© ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

© ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ፲፱፻፺፱

፩ኛ እትም ፲፱፻፴፩

፪ኛ እትም ፲፱፻፵፪

፫ኛ እትም ፲፱፻፵፫

፬ኛ እትም ፲፱፻፷

፭ኛ እትም ፲፱፻፷፩

፮ኛ እትም ፲፱፻፺፱

☎ 011-5-52 14 64

011-1-23 29 05

011-1-23 29 06

011-1-57 44 84

✉ 9144

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# አገር ።

አገር ፤ በታሪክ ፡ በቋንቋ ፡ በሃይማኖት ፡ በልማድ ፡ በተስፋ ፡ በደስታና ፡ በመከራ ፡ ተሳስሮ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ ፡ የሚኖርበት ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ነው ።

አገር ፡ ማለት ፤ አያት ፡ ቅድም ፡ አያት ፡ የተወለዱበት ፤ አድገውም ፡ በጀግንነት ፡ ከውጭ ፡ ጠላት ፡ እየተከላከሉ ፤ ለሕዝብና ፡ ለመንግሥት ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ዕድሜያቸው ፡ ሲደርስም ፡ ልጆቻቸውን ፡ ተክተው ፡ የተቀበሩበት ፡ ጉድጓድ ፡ ነው ።

በመወለድ ፡ እትብት ፤ በመሞት ፡ አካል ፡ ከአፈሩ ፡ ጋራ ፡ ስለሚዋሐድ ፤ የአገሩ ፡ አፈር ፡ ሕዝቡ ፡ በላዩ ፡ የሚኖርበት ፡ ማለት ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ከምድርዋ ፡ ፍሬ ፡ ሕይወት ፡ እንዲገኝባት ፡ በማድረጉ ፡ አገር ፤ እያጠባች ፡ የምታሳድግ ፡ ፍቅርዋ ፡ በአጥንት ፡ በሥጋ ፡ ገብቶ ፡ የማይደመሰስ ፡ የሆነች ፡ እናት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከልጅነት ፡ ጀምሮ ፡ ወንዙን ፤ ተራራውን ፤ ሜዳውን ፤ ቆላውንና ፡ ደጋውን ፡ በማየት ፡ ስለ ፡ ማደግ ፡ አባቶች ፡ በሕይወትና ፡ በሞት ፡ የሠሩበት ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ በአእምሮ ፡ ታትሞ ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ በአገር ፡ እስካሉ ፡ ሲታይ ፤ በስደት ፡ ሲሆኑ ፡ ሲታሰብ ፡ ፍቅርና ፡ ናፍቆት ፡ የሚያሳድር ፡ አገር ፡ ነው ።

አገር ፤ አባት ፡ እናት ፡ ዘመድ ፡ ምግብ ፡ ጌጥና ፡ ሀብት ፡ ዘመሆኑ ፤ ድኽነትና ፡ ጥቃት ፡ በመጣ ፡ ቍጥር ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ እንዲሠራበት ፡ ከአያት ፡ ከቅድም ፡ አያትና ፡ ከአባቶች ፡ በጥብቅ ፡ የተሰጠ ፡ ያደራ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

# ሕዝብ ።

ሕዝብ ፤ በአንድ ፡ አገር ፡ በአንድ ፡ መንግሥት ፡ በአንድ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በአንድ ፡ ሕግ ፡ ጥላ ፡ ተሰብስበው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሕዝብ ፤ በትውልድ ፡ በቋንቋና ፡ በሃይማኖት ፡ መገናኘት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ባለፈው ፡ ኑሮው ፡ ደስታንና ፡ መከራን ፡ በአንድነት ፡ የተካፈለ ፤ በአስተዳደሩም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ የተሳሰረ ፤ ለወደፊትም ፡ እሠራዋለሁ ፡ በሚለውና ፡ ስለ ፡ አገሩና ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ ያለው ፡ ተስፋ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ሰንደቅ ዓላማ ።

ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ የነጻነት ፡ ምልክት ፡ የአንድ ፡ ሕዝብ ፡ ማኅበረሰብ ፡ ማተብ ፣ የኅብረት ፡ ማሰሪያ ፡ ጥብቅ ፡ ሐረግ ፡ ነው ።

« ተመልከት ፡ ዓላማህን ፡
ተከተል ፡ አለቃህን ። »

ነጋሪቱ ፡ እየተጐሰመ ፣ ሠራዊቱ ፡ እየተመመ ፡ ሲሄድ ፣ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ትእምርተ ፡ ኀይል ፡ ትእምርተ ፡ መዊዕ ፡ ነው ።

ሰንደቅ ፡ ዓላማችን ፡ አረንጓዴ ፣ ብጫና ፡ ቀይ ፡ ሦስት ፡ ቀለማት ፡ ናቸው ። ምሳሌያቸውም ፡ አረንጓዴው ፡ ተስፋ ፣ ልምላሜና ፡ ሀብት ። ብጫው ፡ ሃይማኖት ፣ አበባና ፡ ፍሬ ። ቀዩ ፡ ፍቅር ፣ መሥዋዕትነትና ፡ ጀግንነት ፡ ነው ።

## ማውጫ ።


| አርእስት ፡ | ገጽ |
|---|---|
| ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ነገር ፣ | ፩ |
| ጨዋታ ፡ የሚወድ ፡ ልጅ ፣ | ፩ |
| ይቅርታ ፣ | ፫ |
| የሰዱኛ ፡ መለወጥ ፣ | ፫ |
| ሕልምና ፡ ማድረግ ፣ | ፬ |
| ድመትና ፡ ገልገሎችዋ ፣ | ፭ |
| ምድር ፡ | ፮ |
| የአካል ፡ ስሞች ፡ | ፯ |
| አንበሳና ፡ ቀበሮ ፣ | ፯ |
| ብልህ ፡ ተኩላ ፣ | ፰ |
| ግመል ፡ | ፰ |
| ደግ ፡ ሥራ ፣ | ፱ |
| የንጉሥ ፡ የካህን ፡ ግራ ፡ ዐይን ፣ | ፲፩ |
| ሁለት ፡ ፍየሎች ፣ | ፲፫ |
| አሁን ፡ አርጅቻለሁ ፣ | ፲፬ |
| ነብርን ፡ የሚመስል ፡ አውሬ ፣ | ፲፭ |
| ጢትና ፡ ማታ ፣ | ፲፮ |
| የሕንድ ፡ ሰውና ፡ የእስፓንያ ፡ ሰው ፣ | ፲፰ |
| ዕድልና ፡ ለማኝ ፣ | ፲፱ |
| የሚያስገርም ፡ ግብዣ ፣ | ፳ |
| አንተ ፡ ታካች ፣ | ፳፪ |
| በስጦታ ፡ ላይ ፣ | ፳፪ |
| ቸር ፡ ጠባቂ ፣ | ፳፫ |
| ነብርና ፡ ድኩላ ፣ | ፳፬ |
| ጉጉት ፣ | ፳፭ |
| አበበችና ፡ እንጂት ፡ ለማዳ ፡ ወፍ ፣ | ፳፭ |
| ገበሬና ፡ ታማኝ ፡ ውሻው ፣ | ፳፮ |
| የማታለል ፡ ቃል ፣ | ፳፱ |
| ጠሎሽ ፣ | ፴ |

## ማውጫ ።


አርእስት ፡ ... ገጽ

ለመስረቅ ፡ መጣጣር ። ... ፴፩
እንዲት ፡ እስተዋይ ፡ ሽረሪት ። ... ፴፪
ላይና ፡ ታች ። ... ፴፪
የንብና ፡ የድንጉል ፡ መፈካከር ። ... ፴፫
አንበሳ ። ... ፴፬
የሚዳ ፡ አህያ ። ... ፴፮
የአሜሪካ ፡ ነብር ። ... ፴፯
ፈረስ ። ... ፴፯
ዐዋቂ ፡ ሰው ። ... ፴፯
መልካሚቱ ፡ ትንሽ ፡ ልጃገረድ ። ... ፴፰
መንገደኛውና ፡ አንበሳው ። ... ፴፱
ነብር ። ... ፵
በመጨረሻ ፡ የቁጣ ፡ ቃል ። ... ፵፩
ዳቦ ፡ ጋጋሪና ፡ እንጨት ፡ አመላላሽ ። ... ፵፪
ልጆችና ፡ እንቁራሪቶች ። ... ፵፫
ፀሐይ ። ... ፵፬
ወደ ፡ ባለእጅ ፡ ቤት ፡ መሄድ ። ... ፵፬
አንድ ፡ ልጅና ፡ የሚበላ ፡ ፍሬ ። ... ፵፮
ማመልከቻ ፡ ... ፵፯
ሦስት ፡ አታላዮች ። ... ፵፯
የምድር ፡ ማዕድኖች ። ... ፵፰
ዕውር ። ... ፵፱
ሦስት ፡ የሊቀ ፡ መኳስ ፡ ልጆች ። ... ፶
የሦስት ፡ ክፍል ፡ መንግሥት ፡ ፍጥረቶች ። ... ፶፪
ገንዘብ ። ... ፶፫
ዝንጋዔ ። ... ፶፬
ቀርብና ፡ ንብ ። ... ፶፮
በባላገር ፡ ቤት ። ... ፶፯
የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ይበልጣል ። ... ፶፯


## ማውጫ ።


አርእስት ፡ ... ገጽ

ጅብና ፡ አንበሳ ። ... ፶፰
የልጆች ፡ ጨዋታ ። ... ፷
ስለ ፡ ትምህርት ። ... ፷፩
የትምህርት ፡ ፍቅር ። ... ፷፫
የመልካም ፡ አባት ፡ ኑዛዜ ። ... ፷፮
ፍቅር ። ተከከርን ፡ ትምክሕትን ፡ ታሸንፋለች ። ... ፷፯
የአንበሳና ፡ የጅብ ፡ ወዳጅነት ። ... ፷፯
አይጥና ፡ ድመት ። ... ፷፱
የቆጡን ፡ አወርድ ፡ ብላ ፡ የብብቷን ፡ ጣለች ። ... ፸
ምስክር ። ... ፸፪
ጣዖት ። ... ፸፫
ብልጠት ። ... ፸፮

## በአንድ ጊዜ አንድ ነገር

ስትሠራ ፡ ሥራ ፡ ስትጫወትም ፡ ተጫወት ፣ የተድላና ፡ የደስታ ፡ መንገድ ፡ ይህ ፡ ነው ።

የምታደርገውን ፡ ሁሉ ፡ አስተውለህ ፡ አድርግ ። በችኰላ ፡ የተደረገ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከቶ ፡ በትክክል ፡ አይሠራም ።

## ባንድ ጊዜ አንድ ነገር ።

ያም ፡ ቢሆን ፡ ደኅና ፡ ሆኖ ፡ ይደረግ ። ብዙዎች ፡ ሊመሰክሩለት ፡ የሚችሉ ፡ መልካም ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

ጊዜ ፡ አይታመንም ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል ፣ እንግዲያስ ፡ ስትሠራ ፡ ሥራ ፣ ስትጫወትም ፡ ተጫወት ፣ ጊዜው ፡ ይበራል ፣ ደቂቃውም ፡ ያልፋል አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሆነ ።

ቀኑ ፡ በረረ ፣ ሌሊቱም ፡ ቀረበ ፣ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሄደ ፣ ወሩም ፡ ዓመቱም ፡ አለፈ ።

ዘመኔ ፡ ከሚርጥ ፡ ሰው ፡ ይፈጥናል ። ንስር ፡ የሚበላውን ፡ አይቶ ፡ እንደሚበር ፡ እንደምትፈጥንም ፡ መርከብ ፡ አለፈ ፣ ኰበለለ ፡ መልካም ፡ ነገርም ፡ አላየም ።

## ጨዋታ የሚወድ ልጅ ።

ብራ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የበጋ ፡ ቀን ፡ ነበርና ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ በናቱ ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ተልኮ ፡ ሄደ ። እርስዋ ፡ ግን ፡ ጨዋታ ፡ እንዲወድ ፡ አላወቀችምና ፡ እኅቱ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ እንድ ትሄድ ፡ አዘዘች ።

ቀንም ፡ ሙቀት ፡ ነበርና ፡ ልጁ ፡ እንሥቶ ፡ እኅቱን ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ከመሄድ ፡ ይልቅ ፡ ብንጫወት ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ አላት ። እርስዋ ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ አይደለም ፣ አሁን ፡ ለጨዋታ ፡ ጊዜ ፡ የለኝምና ፡ አንተን ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ካደረስኩኽ ፡ በኋላ ፡ ጥጥ ፡ ሐርና ፡ መርፌ ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ለናታችን ፡ እንድገዛላት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ እሻገራለሁ ። ምግብ ፡ ለማግኘትም ፡ ገንዘብ ፡ እንድናገኝ ፡ ግድ ፡ ሥራዬን ፡ እሠራለሁ ፡ አለችው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይኸው ፡ ልጅ ፡ አንዲት ፡ ንብ ፡ ከአበባ ፡ ወደ ፡ አበባ ፡ ስትበር ፡ አየና ፡ ንብ ፡ ለመሆን ፡ እወዳለሁ ፡ እርሷ ፡ ሥራ ፡ የላትም ፡ እኔም ፡ ሥራ ፡ የለኝም ፡ አለ ። እኅቱ ፡ ግን ፡ ዋይ ፡ ብላ ፡ ንቢቱ ፡ እኮ ፡ ሰነፍ ፡ አትምሰልህ ፡ ማር ፡ ታገኛለች ፣ አበባም ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ለክረምት ፡ እንዲሆናት ፡ ትሰበስባለች ። ንቢቱ ፡ አውላዋን ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ቀፎዋ ፡ ትመለሳለች ፡ አለችው ። ወዲያውም ፡ አንድ ፡ ወፍ ፡ ስትዘፍን ፡ ሰማና ፡ ይህች ፡ ወፍ ፡ በርግጥ ፡ አሁን ፡ ሥራ ፡ የላትም ። ቀኑንም ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ዘፈን ፡ ትዘፍናለችና ፡ ቢዛፉ ፡ ሥር ፡ ተቀምጠን ፡ እርስዋን ፡ ብንሰማ ፡ እወዳለሁ ፡ አለ ። እኅቱም ፡ መልሳ ፡ ወፊቱ ፡ ትበርራለች ፣ ገለባውንም ፡ ሰብስባ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ጎጆዋ ፡ ትወስዳለች ። በላባና ፡ በገለባ ፡ በቅርንጫፍም ፡ ጐጆዋን ፡ ትሠራለች ፣ ስለዚህ ፡ ለመስነፍ ፡ ጊዜ ፡ የላትም ፡ አለች ።

ሄደውም ፡ ሳይጨርሱ ፡ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ውሻ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ውሻ ፡ የሚያደርገው ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ፣ ስለዚህ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ለመጫወት ፡ አይፈቀድልኝምን ፡ እያለ ፡ ሲነጋገር ፡ ወዲያው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አፏጨ ። ውሻውም ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሣና ፡ በጎቹን ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ሊወስድ ፡ የሚነዳውን ፡ ሰውዮ ፡ ለመርዳት ፡ ሄደ ።

እንደ ፡ ገናም ፡ ልጁ ፡ እልፍ ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ፈረስ ፡ በመስክ ፡ ሲግጥ ፡ አየና ፡ ይህ ፡ ፈረስ ፡ የሚያደርገው ፡ የለውምና ፡ ስለዚህ ፡ ሄጄ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እጫወታለሁ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ወደፊት ፡ እንደ ፡ ተራመደ ፡ ሰውዮው ፡ ልባብ ፡ ይዞ ፡ ቀረበና ፡ ፈረሱን ፡ ለበበው ።

እንዲህም ፡ እንዳደረገ ፡ ልጁን ፡ ጠራና ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ፈረሴ ፡ ያርሳል ፣ ይተልማልም ፣ ገንዘብም ፡ እንዳገኝ ፡ ገረግ ፡ ንብስ ፡ ስንዴ ፡ ፈጭቶ ፡ ለመሸጥ ፡ ግድ ፡ ያስፈልገናል ፣ ብሎ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።



ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ ንብ ፣ ወፍና ፡ እንስሳ ፡ ሥራ ፡ እንዳላቸው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እኅቱን ፡ እንዲህ ፡ አላት ፣ እኅቴ ፡ ሆይ ፡ እንዲህስ ፡ ከሆነ ፡ እኔም ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሄጄ ፡ ትምርቴን ፡ አጠናለሁ ፣ ወደ ፡ ቤቴም ፡ ስመለስ ፡ ሳልተኛ ፡ ረጂርም ፡ ጊዜ ፡ ከባልንጀሮቼ ፡ ጋራ ፡ ለመጫዎት ፡ እናቴ ፡ ትፈቅድልኛለች ።

እንዲህም ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ሮጠ ። እኅቱም ፡ ከርሱ ፡ ስለ ፡ ተለየች ፡ መልከትዋን ፡ ለማድረስ ፡ ደስ ፡ እያላት ፡ ሄደች ።

ሰነፍን ፡ የሚወልድ ፡ ኀዘን ፡ ይሆንበታል ።

## ይቅርታ ::

በከፉ ፡ ጠባይህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ በደልህ ፡ አስብ ፣ ሌላውን ፡ ይቅር ፡ ካላልክ ፣ ኃጢአትህን ፡ ይቅር ፡ እንዲልህ ፡ ልትለምነው ፡ እንዴት ፡ ይቻልሃል ?

ይቅር ፡ እንዲሉህ ፡ ይቅር ፡ በል ።

ንቢቱ ፡ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ ስትሠራ ፡ ስትደክም ፣
ውሻው ፡ ጌታውን ፡ ሲያገለግል ፣
ሌላውም ፡ እንስሳ ፡ ሰውን ፡ ሲረዳ ፡ ታያለህ ፣
አንተስ ፡ ለናትህና ፡ ለእህቶችህ ፡ ምን ፡ ልታደርግላቸው ፡ ታስባለህ ?

## የፀዱኛ መስወጥ ::

አንድ ፡ የምሥራቅ ፡ ጦረኛ ፡ ጐበዝ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፣ ብዙ ፡ አገርም ፡ አሸንፎ ፣ አስገብሮ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ፍዳ ፡ አይቀርምና ፡ በመጨረሻው ፡ ባንዲት ፡ ትንሽ ፡ ጦርነት ፡ ተሸንፎ ፡ ድል ፡ ሁኖ ፡ ተማረከ ።

እዚያው ፡ ከተማረከበት ፡ ቦታ ፡ ሁኖ ፡ ረኃብ ፡ ይዞት ፡ ነበር ። ረኃቡንም ፡ ሊያበርድለት ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ የተራ ፡ ወታደር ፡

ምግብ ፡ ሲያሰናዳለት ፡ ሳለ ፡ መቀመጫውን ፡ አቧራ ፡ ላይ ፡ አድር ገው ፡ አግድም ፡ አስቀመጡት ።

ምግቡም ፡ የፈረስ ፡ ሥጋ ፡ በሚቀቀልበት ፡ ባንድ ፡ ማሰሮ ፡ ውስጥ ፡ ሲቀቀልና ፡ ሲፈላ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ውሻ ፡ መጣና ፡ ይህን ፡ ሥጋ ለመውሰድ ፡ አንገቱን ፡ በማሰሮው ፡ ውስጥ ፡ አስገባው ።

የማሰሮውም ፡ አንገት ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ራሱን ፡ ለማውጣት ፡ አልቻለም ፡ ነበርና ፡ ሥጋውን ፡ እንዳለ ፡ ከነማሰሮው ፡ ይዞት ፡ በረረ ።

ይኸውም ፡ ታስሮ ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ይህነን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ገርሞት ፡ ተደነቀ ፣ ከልቡም ፡ ሣቀ ። እርሱንም ፡ ከሚጠብቁት ፡ ዘበኞች ፡ ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ ዘበኛ ፡ ምን ፡ ያሥቅሃል ? ምን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ አለ ? በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ ውስጥ ያለ ፡ ሰው ፡ ሊሥቅ ፡ ይገባልን ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ንጉሡም ፡ አሁን ፡ የምስቀው ፡ ዛሬ ፡ ጥዋት ፡ አንድ ፡ ውሻ ፡ መጥቶ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ግመሎች ፡ እንኳ ፡ ቢመጡ ፡ የማያነሡትን ፡ የቤት ፡ ዕቃዬን ፣ መብሉን ፡ ከነማሰሮው ፡ ይዞት ፡ በረረ ፡ ብሎ ፡ ከእልፍኝ ፡ አሽከሮቹ ፡ አንደኛው ፡ አሰቃ ፡ ስለነገረኝ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ሰጠው ።

ለዘበኛው ፡ ጥያቄ ፡
ንጉሡ ፡ የመለሰው ፡ ምንድን ፡ ይሆን ?

## ሕልምና ማድረግ ::

አንድ ፡ የማይረባ ፡ ሰነፍ ፡ ልጅ ፡ ወጥቼ ፡ ልጫወትን ፡ ብሎ ፡ እናቱን ፡ ጠየቃት ።

እናቱም ፡ ትምህርትህን ፡ አጥንተሃልን ? ብላ ፡ መልሳ ፡ ብትጠይቀው ፡ እንኳን ፡ እናቴ ፡ ሆይ ፡ ተኝቼ ፡ ነበርና ፡ ትምህርቴን ፡ እንደ ፡ ጨረስኩ ፡ አለምሁት ፡ እንጂ ፡ አላጠናሁትም ፡ ብሎ ፡ ነገራት ።

እርሷም ፡ እንግዲያስ ፡ ጨዋታህን ፡ በሕልምህ ፡ ጨርስና ፡ ወደ ፡ ትምህርትህ ፡ ተመለስ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ፡ ይባላል ።



ሕልም ፡ የማይጠቅም ፡ ተስፋ ፡ ነው ። እንዲሁም ፥ አሳቡ ፡ ያልተፈጸመለት ፡ ሰው ፡ የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ሆነብኝ ፡ ይላል ።

ሕልምን ፡ አምኖ ፡ የሚሠራ ፡
ምን ፡ ማግኘት ፡ ይችላል ?

## ድመትና ግልገሎቿ ::

ድመቲቱን ፡ ከግልገሎቿ ፡ ጋራ ፡ ታያታለህን ? ለእሷ ፡ አራት ፡ እግሮችና ፡ ለስላሶች ፡ መዳፎች ፡ አሉዋት ። ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ ስትመላለስ ፡ አትሰማም ፣ ንጹሕ ፡ መሆንን ፡ ትወዳለች ። በምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ትቀመጣለች ። በምላሷ ፡ መዳፏን ፡ ትልሳለች ፣ በርሱም ፡ ፊቷን ፡ ታወዛለች ።

የድመቲቱን ፡ መዳፍ ፡ አስተውል ፣ ለስላሳ ፡ ነው ፣ ግን ፡ በዚያው ፡ በመዳፏ ፡ ውስጥ ፡ ስለታሞች ፡ ጥፍሮች ፡ ተደብቀው ፡ አሉ ። ድመቲቱ ፡ ልትጐዳህ ፡ ብታስብ ፡ በጥፍሮቿ ፡ ትጓጒርሃለች ።

አይጦችንና ፡ ወፎችንም ፡ መያዝ ፡ ትወዳለች ።

አንተ ፡ ግን ፡ ወፎችን ፡ ማርባት ፡ ብትወድ ፡ ድመቲቱ ፡ ወደ ፡ ወፎቹ ፡ እንዳትቀርብ ፡ ተጠንቀቀህ ፡ ኑር ፣ ድመቲቱ ፡ ወፎቹን ፡ ብትይዝ ፡ እንድትጎዳቸው ፡ አስብ ፣ ገድላም ፡ ትበላቸዋለች ።

የድመት ፡ ግልገሎች ፡ እየቦረቁና ፡ እየዘለሉ ፡ ይጫወታሉ ። ከኳሱ ፡ በኋላም ፡ እየሮጡና ፡ እየተሽቀዳደሙ ፡ በደስታ ፡ ይፈንጥዛሉ ።

ድመቲቱን ፡ አይተህ ፡
ምን ፡ መሆን ፡ ትመኛለህ ?

## ምድር ::

እኔ ፡ በቤቴ ፡ እኖራለሁ ፣ ቤቴም ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ነው ፣ መንገዱም ፡ ያንድ ፡ መንደር ፡ ክፍል ፡ ነው ፣ በመንገዱም ፡ አጠገብ ፡ መስክ ፡ አለ ፣ ከመስኩም ፡ ትይዩ ፡ ብዙ ፡ መንደሮች ፡ አሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ ጫካና ፡ ኮረብቶች ፡ ይገኛሉ ። በሌላውም ፡ ስፍራ ፡ ሐይቆችና ፡ ወንዞች ፡ አሉ ፥ ራቅ ፡ ብንልም ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ እንደርሳለን ።

መንደሩና ፡ ሜዳው ፥ ጫካውና ፡ ኮረብታው ፥ ሐይቁና ፡ ወንዙ ባሕሩም ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ መሬት ፡ ናቸው ።

ምድር ፡ እንዳንድ ፡ ትልቅ ፡ ኳስ ፡ ክብ ፡ ሆና ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ናት ፥ ሰው ፡ ምድርን ፡ ለመዞር ፡ ቢፈልግ ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ይወስድበታል ።

አንዳንዱ ፡ አገር ፡ እጅግ ፡ ሙቀታም ፡ ነው ፥ ሌላውም ፡ እጅግ ብርዳም ፡ ነው ፡ አንደኛው ፡ እጅግ ፡ ድርቅ ፡ ይገኝበታል ፥ ሁለተኛውም ፡ እጅግ ፡ ዝናም ፡ ይበዛበታል ።

እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ ፈጠረ ። ደግሞ ፡ ዝናምን ፡ ያዘንማል ፥ ፀሐይንም ፡ ያወጣል ።

እግዚአብሔር ፡ ለዓለምና ፡ በርሱዋ ፡ ለሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ይጠነቀቅላቸዋል ። እርሱ ፡ ለመልካሞችና ፡ ለክፉዎች ፡ ፀሐይን ፡ ያወጣል ። በጻድቃንና ፡ በኃጥአንም ፡ ላይ ፡ ዝናሙን ፡ ያዘንማል ።

ምድር ፡ መላዋ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ናት ።
በዚህች ፡ ባጭር ፡ ትምህርት ፡ ስንት ፡ ሥነ ፡
ፍጥረት ፡ እንዳለ ፡ ታውቃለህን ?

## የአካል ስሞች ::

እኔ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ። የማስብበት ፡ ራስ ፡ አለኝ ። የማይባቸው ፡ ሁለት ፡ ዐይኖች ፡ የምሰማባቸው ፡ ሁለት ፡ ጆሮዎች ፥ የማሸትበት ፡ አፍንጫ ፥ የምበላበት ፡ አፍ ፡ አሉኝ ።

ባፌ ፡ ውስጥ ፡ የምናገርበት ፡ ምላስ ፥ የምነክስበት ፡ ጥርስ ፡ አፌንም ፡ የምዘጋባቸው ፡ ከንፈሮች ፡ አሉኝ ።

በራሴ ፡ ጠጉር ፡ ይበቅላል ። ሁለት ፡ ክንዶች ፡ አሉኝ ። በክንዶቼም ፡ ጫፍ ፡ እጅ ፥ በእጄም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ (መንኰብ ፡) አውራ ፡ ጣት ፡ አራት ፡ ጣቶች ፥ በጣቶችም ፡ ጫፍ ፡ ጥፍር ፡ አለ ።



በእጆቼም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ እችላለሁ ። ደግሞ ፡ ለመራመድና ፡ ለመዝለል ፡ ሁለት ፡ ቅልጥሞችና ፡ ሁለት ፡ እግሮች ፡ አሉኝ ፥ በያንዳንዱ ፡ እግር ፡ አምስት ፡ ጣቶች ፥ በያንዳንዱም ፡ ጣት አንዳንድ ፡ ጥፍሮች ፡ አሉ ።

ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ እችልባቸዋለሁ ፡ እንጂ ፡ የብልቶችንና ፡ የአከላትን ፡ ስም ፡ መናገር ፡ አልችልም ። እግዚአብሔር ፡ እንዲጠቅሙኝ ፡ ብሎ ፡ አካላትን ፡ ሰጥቶኛልና ፡ ሰውነቴን ፡ ንጹሕ ፡ ማድረግ ፡ ይገባኛል ።

ቁርበትና ፡ ሥጋም ፡ አለበሰኸኝ ፥ ባጥንትና ፡ በጅማትም ፡ አጸናኸኝ ።

አንተ ፡ ምንድን ፡ ነህ ?
እንዴትስ ፡ ሆነህ ፡ ተፈጥረሃል ?

## አንበሳና ቀበሮ ::

ቀበሮ ፡ አንበሳን ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሁነን ፡ ብናድን ፡ ምን ፡ አለብን ፡ ብሎ ፡ ጥያቄውን ፡ አቀረበ ። አንበሳውም ፡ ፈቃዱ ፡ ሆነና ፡ ይሁን ፡ አለ ። ቀበሮውም ፡ ወዲያው ፡ በአንበሳው ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ሊሄድ ፡ ጀመረ ። አንበሳውም ፡ በቍጣ ፡ አንተ ፡ የኔ ፡ ጓደኛ ፡ ነህን ? አለ ።

ቀበሮውም ፡ ፍርሃት ፡ ወደቀበትና ፡ እንኳን ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አገልጋይዎ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ጓደኛዎስ ፡ አይደለሁም ፡ አለ ።

እንግዲያስ ፡ በፊት ፡ በፊቴ ፡ ሂድና ፡ ምግቤን ፡ ፈልገህ ፡ ቆየኝ ባገኘኸም ፡ ጊዜ ፡ እስከበላ ፡ ድረስ ፡ ባጠገቤ ፡ እንዳትቆም ፥ ወይም እንዳትቀመጥ ፥ ብቻዬን ፡ እሆናለሁ ፡ እንጂ ፡ ወዳጅ ፡ አያስፈልገኝም ፡ ብሎ ፡ አንበሳው ፡ ለቀበሮው ፡ በኀይለ ፡ ቃል ፡ መለሰለት ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ! ከኀይለኞች ፡ ጋራ ፡ ጓደኝነት ፡ ይቅርባችሁ ፥ ያንድ ፡ ቀን ፡ ምርኮ ፡ እንዳያደርጓችሁ ፡ ዐቅሙን ፡ አያውቅ ፡ የሚሉት ፡ ተረት ፡ በዚህ ፡ ቀበሮ ፡ እንደ ፡ ደረሰበት ፡ ተመልከቱ ።

አንበሳ ፡ ማነው ?
ቀበሮስ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

## ብልህ ተኩላ ።

አንድ ፡ ተኩላ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠራና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አዳኞች ፡ ሲያ ድኑት ፡ እንዲት ፡ ዝዬ ፡ ቀምቶት ፡ ወደነበረው ፡ ቀበሮ ፡ ጕድጓድ፡ ለመጠጋትና ፡ በዚያም ፡ ለመደበቅ ፡ ሩጦ ፡ ገባ ።

ቀበሮውም፡ ይህ ፡ የኔ ፡ ጕድጓድ ፡ ነውና ፡ ተሳስተሃል ፡ አለ ው ። ተኩላውም ፡ የመጣሁት ፡ በጠላቶቼ ፡ ስለምታደን ፡ ጥግ ፡ ለመፈለግ ፡ በወዳጅነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተሳስቼ ፡ አይደለም ፡ አለ ።

ቀበሮውም ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ያዳኞች ፡ አመ ጣጥ ፡ ይሰማኛልና ፡ ወጥቼ ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡ እንደሌለህ ፡ እነግራ ቸዋለሁ ፡ አለው ።

ተኩላውም ፡ ቀበሮው ፡ አዳኞችን ፡ ጠርቶ ፡ ያስገድለኛል ፡ ብሎ ፡ ጠረጠረና ፡ እንኳን ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ አንተን ፡ አዳኞች ፡ ቢገ ድሉህ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ አንተ ፡ ብቻዬን ፡ መኖር ፡ እንደማልችል ፡ ይታ የኛልና ፡ አዳኞቹ ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡ በዚሁ ፡ ልትቀመጥ ፡ ይገ ባሃል ፡ ብሎ ፡ በማታለል ፡ መክሮ ፡ አስቀረው ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ! ከአታላዮች ፡ ምላስ ፡ እንድትጠበቁ ፡ ያስፈልጋችኋል ።

## ግመል ።

ግመል ፡ ከፈረስ ፡ ይበልጣል ፣ በአካሉም ፡ ከሌሎቹ ፡ እንስሳት ፡ የተለየ ፡ ረጅም ፡ ነው ። ሲጫንና ፡ ሲራገፍ ፣ ሰው ፡ ሲወጣበትም ፡ ሳለ ፡ ሲወርድም ፡ ይንበረከካል ። ሊቆምም ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፡ መዠመ ሪያ ፡ የኋላ ፡ እግሮቹን ፡ ያነሣል ። ሰው ፡ ተቀምጦበትም ፡ ሲነሣ ፡ አጥብቆ ፡ ያልያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰውዬው ፡ ወደ ፡ ግመሉ ፡ ራስ ፡ ይወረወራል ። ግመል ፡ ብርቱ ፡ ነው ፣ ከባድ ፡ ዕቃም ፡ ለመሸከም ፡ ይችላል ።

በሰሜን ፡ ሕንድ ፣ በዐረብ ፡ አገርም ፣ በአፍሪቃ ፡ በረሃዎችም ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ። ውሃ ፡ ሳይጠጣም ፡ ብዙ ፡ ርቆ ፡ ይሄዳል ፣ ውሃ ም ፡ በሌለበት ፡ አሸዋ ፡ በሆነ ፡ ስፍራ ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡



ለመዝለቅ ፡ የተደራጀ ፡ ነው ። አራት ፡ አምስት ፡ ቀንም ፡ ያህል ፡ ውሃ ፡ ሳይጠጣ ፡ ለመሄድ ፡ ይችላል ።

አንዳንድ ፡ ግመሎች ፡ በጀርባቸው ፡ አንድ ፣ እኩሌቶቹም ፡ ሁለት ፡ ሻኛ ፡ አላቸው ። ሻኛቸውም ፡ የሰባ ፡ ነው ። ግመሉ ፡ ሳይ በላ ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ሻኛው ፡ እየሟሸሸ ፡ ይሄዳል ባይበላም ፡ እንኳ ፡ ሻኛው ፡ ጕልበት ፡ ይሆነዋል ።

የግመሉ ፡ እግሮች ፡ ትልልቅ ፡ ሰፊና ፡ ለስላሳ ፡ በወፍራም ፡ ቆዳ ፡ የተያያዙ ፡ ናቸው ። በበረሃ ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ በሞቀ ፡ አሸዋ ፡ ላይ ፡ በቀላል ፡ አካሄድ ፡ መራመድ ፡ ይችላሉ ። ግመል ፡ ሲሄድ ፡ በጸጥታ ፡ ነውና ፡ ባጠገብህ ፡ ሲያልፍ ፡ አትሰማውም ።

የግመሉ ፡ አፍንጫ ፡ ጠባብ ፡ ሥንጣቂ ፡ ያለው ፡ መዘጋት ፡ መከፈት ፡ የሚችል ፡ ነው ። አሸዋው ፡ በነፋስ ፡ በተበተነ ፡ ጊዜ ፡ ግመሉ ፡ ይተኛና ፡ አፍንጫውን ፡ ዘግቶ ፡ ራሱን ፡ በአሸዋ ፡ ይቀብ ረዋል ። ከሩቅም ፡ የውሃ ፡ ሽታ ፡ ይሰባል ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ መንገድ ፡ አሳብሮ ፡ በቀጥታ ፡ ይሄድና ፡ ወደ ውሃ ፡ ይደርሳል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ብዙዎችን ፡ መንገደኞች ፡ ውሃ ፡ ካለበት ፡ ያደርሳቸውና ፡ ከውሃ ፡ ጥም ፡ ያድናቸዋል ።

ነጋዴዎች ፡ በግመል ፡ ዕቃቸውን ፡ ይጭናሉ ፣ ግመሎችም ፡ ጅምላ ፡ ሁነው ፡ ይጓዛሉ ። ጕዞውም ፡ እስከ ፡ ሰባና ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ይደርሳል ።

አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በተርታ ፡ ተቀጣጥለው ፡ ይሄዳሉ ፣ አንዳ ንዶችም ፡ ግመሎች ፡ ጠያሮች ፡ ናቸው ። ባንድ ፡ ቀን ፡ ከመቶ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ የሚበልጥ ፡ መንገድ ፡ መሄድ ፡ ይችላል ።

ግመል ፡ ከሌሎች ፡ እንሰሳ ፡ ተለይቶ ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ የሚች ልበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው ?

## ደግ ሥራ ።

ከዕድሜው ፡ ገፋ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰብስቦ ፡ ነበርና ፡ የሞት ፡ ቀኑ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ዐውቆት ፡ ያለ ፡ ገንዘቡን ፡ ለሦ ስት ፡ ወንዶች ፡ ልጆቹ ፡ አካፈላቸው ። ገንዘቡንና ፡ ርስቱን ፡ ካካፈ

ላቸው ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዕንቍ ፡ ሲቀረው ፡ አንሥቶ ፡ በዚህ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ለሠራው ፡ ልጅ ፡ ይኸን ፡ ዕንቍ ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ሲል ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ አስቀመጠው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታላቁ ፡ ልጅ ፡ ተነሣና ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ዕውቀት ፡ እንኳን ፡ ሳይኖረን ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አምና ፡ አደራ ፡ አስቀመጠብኝ ፤ ሳስቀምጥለትም ፡ የደረሰኝ ፡ ፊርማዬን ፡ አልሰጠሁትም ። ምንም ፡ ዕውቀት ፡ የለኝም ፡ ነበር ። እኔም ፡ ከገንዘቡ ፡ ምንም ፡ ሳልነካበት ፡ በጥንቃቄ ፡ ጠብቄ ፡ አስቀመጥሁለት ። እርሱም ፡ መጥቶ ፡ ለመውሰድ ፡ በጠየቀኝ ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡን ፡ በመላው ፡ መልሼ ፡ ሰጠሁት ። ስላስቀመጥሁለትም ፡ የእምነቴን ፡ ዋጋ ፡ ቢሰጠኝ ፡ አልቀበልም ፡ ብዬ ፡ መለስሁለት ፡ ይህ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ አይደለምን ? አለ ።

አባትዮውም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ! ይህ ፡ ያንተው ፡ የሐቀኝነት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይበቃም ፡ አለው ። ደግሞ ፡ ሁለተኛው ፡ ታናሹ ፡ ልጅ ፡ ተነሣና ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በኩሬ ፡ ዳርዳሩን ፡ ስሄድ ፡ ሳለሁ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ እኩሬው ፡ ውስጥ ፡ ወድቆ ፡ ነበርና ፡ እኔም ፡ ለነፍሴ ፡ ሳልሳሳ ፡ በድፍረት ፡ ዘልዬ ፡ እኩሬው ፡ ውስጥ ፡ ገባሁና ፡ ልጁን ፡ በደኅና ፡ አውጥቼ ፡ ለተጨነቀችው ፡ እናቱ ፡ ሰጠኋት ። ይህ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ አይባልምን ? አለ ።

አባትዮውም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ የልማድ ፡ ርኅራኄ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ብቻውን ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይበቃም ፡ አለው ።

ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ ታናሽ ፡ ልጁ ፡ ተነሣና ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጨለማ ፡ ሌሊት ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ በጣም ፡ ደመኛ ፡ የሆነኝ ፡ ጠላቴ ፡ በገደል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ አገኘሁትና ፡ ደንግጦ ፡ ባኖ ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ እንዳይወድቅ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ ተንፏቅቄ ፡ ሄድሁና ፡ በጠላትነት ፡ መንገድ ፡ ሳይሆን ፡ ቀስቅሼ ፡ ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ አስነሥቼ ፡ ወደ ፡ ደኅና ፡ ስፍራ ፡ አምጥቼ ፡ አስተኛሁት ። ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ በጠላትነት ፡ መንገድ ፡ ሄጄ ፡ ደንግጦ ፡ ቢባንንና ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ ቢወድቅ ፡ ኑሮ ፡ በዚያ ፡ በትልቁ ፡ ገደል ፡ ገብቶ ፡ ለመሞት ፡ አይዘገይም ፡ ነበር ። ይህስ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ አይባልምን ? አለው ።



ከዚህም ፡ ወዲህ ፡ አባትዮው ፡ በዚሁ ፡ በትንሹ ፡ ልጁ ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ውድ ፡ ልጄ ፡ ከዚህስ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ አለ ፡ አለና ፡ እየሳመ ፡ ይህ ፡ ዕንቍ ፡ ላንተ ፡ ነው ፡ የሚገባው ፡ ብሎ ፡ ሰጠው ።

እንግዴህ ፡ ጠላትን ፡ መውደድ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ሥራ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

## የንጉሡ የካህን ግራ ዐይን ::

በመስኮብ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ባለጸጋ ፡ ነበር ። ሦስት ፡ ልጃገረዶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። ከነርሱም ፡ ልጆቹ ፡ ውስጥ ፡ አንደኛዪቱ ፡ ልጃገረድ ፡ ትንሹዋ ፡ ከታራዶን ፡ የምትባለዋ ፡ ድንቅ ፡ የሆነች ፡ ብልሃተኛ ፡ ቆንጆ ፡ ነበረችና ፡ በዚሁ ፡ በሚያስደንቀው ፡ ብልሃቷና ፡ ቍንጅናዋ ፡ በጣም ፡ ትከበር ፡ ነበረች ። አባታቸው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ከብት ፡ ለመሸጥ ፡ ሊሄድ ፡ ተሰናድቶ ፡ ነበርና ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ! ስመለስ ፡ ምን ፡ ገዝቼላችሁ ፡ ልምጣ ፡ ብሎ ፡ ሦስቱን ፡ ልጆቹን ፡ ጠየቃቸው ።

ታላላቆቹም ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ጉትቻ ፡ እንዲገዛላቸው ፡ ተናገሩት ። ግን ፡ ትንሽቱ ፡ ቆንጆዋ ፡ ልጅ ፡ ለርሱ ፡ የሚያስፈራውንና ፡ የሚያስቸግረውን ፡ ነገር ፡ ግዛልኝና ፡ ና ፡ ስትል ፡ ለመነችው ።

አባትዮውም ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ለመነችው ፡ ሊያደርግላት ፡ ፈቀደላትና ፤ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ከመጋላው ፡ በሬ ፡ በተቀር ፡ የቀሩትን ፡ ከብቶች ፡ በተገኘው ፡ ዋጋ ፡ ሽጣቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ መጋላውን ፡ የጠየቁህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የካህንን ፡ የንጉሡን ፡ ግራ ፡ ዐይን ፡ አምጡና ፡ እሸጥላችኋለሁ ፡ ያለዚያ ፡ አይሸጥም ፡ በላቸው ፡ አለችው ።

ይህም ፡ አባትዮውን ፡ በጣም ፡ አስደነቀው ። ነገር ፡ ግን ፡ የልጁን ፡ ብልህ ፡ መሆን ፡ በጣም ፡ ያውቃልና ፡ እርሱም ፡ እርሷ ፡ እንደ ፡ ነገረችው ፡ ጥያቄ ፡ ለገበያተኞች ፡ ሲመልስላቸው ፡ ዋለ ፤ ይህንም ፡ የሱን ፡ ጥያቄ ፡ የገበያው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ በማለቱ ፡ ሁሉም ፡ ደንግጠው ፡ እየሮጡ ፡ ከበው ፡ ያዙትና ፡ እንደ

ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ተሽከመው ፡ እንክብክበው ፡ እንጉሡ ፡ እካህን ፡ ፊት ፡ አቀረቡት ።

ይህም ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ በድንቁርናው ፡ ልጁ ፡ በነገረችው ፡ ጥፋት ፡ ተከትሎ ፡ ለበሬው ፡ ዋጋ ፡ ሲጠይቁት ፡ በመለሰላቸው ፡ አድራጎት ፡ ደንግጦ ፡ ሄደ ። በንጉሡ ፡ እግሮች ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሥራውን ፡ ይናገር ፡ ጀመር ። ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ ያለበትን ፡ ጥያቄ ፡ ተጠራጥሮ ፡ ይህ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄዶ ፡ ያችን ፡ ልጁን ፡ ይዞ ፡ እንዲያመጣና ፡ እንድትመረመር ፡ አሰናብቶት ፡ ሄደ ።

እርሱም ፡ ሄደና ፡ ልጁን ፡ እፊቱ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደታዘዘው ፡ ተከታትሏት ፡ በጥቂት ፡ ሰዓት ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ አቀረባት ። እርሷም ፡ እንደ ፡ ቀረበች ፡ የንጉሡን ፡ የካህንን ፡ ግራ ፡ ዐይን ፡ በመጋላው ፡ በሬ ፡ እንዲሸጥ ፡ የተመኘችበትን ፡ ነገርና ፡ ምክንያት ፡ ላባቷ ፡ ስለ ፡ መከረችው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ሰጠች ። እንዲህ ፡ ስትል ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ የሚገርምዎት ፡ አሳብ ፡ ባገኝዎት ፡ ጊዜ ፡ ወደኔ ፡ እንዲልኩልኝና ፡ ለርስዎም ፡ ለሕዝብዎም ፡ የሚሆነውን ፡ ዋና ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለውን ፡ አሳብ ፡ እንድነግርዎት ፡ ምኞት ፡ ነበረኝ ፡ ስትል ፡ መልስ ፡ ሰጠች ።

ንጉሡም ፡ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ምንድነው ፡ እስኪ ፡ ንገሪኝ ፡ አላት እርሷም ፡ እንደሚከተለው ፡ ተናገረች ። ሁለት ፡ ባላጋራዎች ፡ ባለ ፡ ጸጋና ፡ ድኃ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ይቆማሉ ፤ ባለጸጋው ፡ በስተቀኝ ፡ ሲቆም ፡ ድኃው ፡ በስተግራ ፡ በኩል ፡ ይቆማል ። ባለጸጋው ፡ ሲደላለት ድኃው ፡ ይደላበታል ። ደግሞ ፡ ባለጸጋውን ፡ ሲያፈቅሩት ፡ ድኃውን ፡ ሲጠሉት ፡ እየሰማሁ ፡ ስለዚህ ፡ ግራ ፡ ዐይንዎ ፡ ድኃን ፡ ካላየና ፡ ካልተመለከተ ፡ ምንም ፡ አይጠቅምዎትም ፡ በማለት ፡ አባቴ ፡ ገዝቶ ፡ እንዲያመጣልኝ ፡ አፋጥኘ ፡ ሰደድኩት ፡ ስትል ፡ መልስ ፡ ሰጠች ።

ንጉሡም ፡ ካታራደን ፡ በተናገረችው ፡ አሳብ ፡ ተቆጭቶ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህም ፡ የከፉ ፡ አሳብ ፤ ወይም ፡ የጥበብ ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊመክርበትና ፡ ሊመረምረው ፡ አሰበ ። እርሱም ፡ በፍጹም ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ በሚያስቸግሩ ፡ ነገሮች ፡ ፈተናት ። ለዚሁ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ለሆኑት ፡ ጥያቄዎችና ፡ ፈተናዎች ፡ መልስ ፡ በመስጠቷ ፡ በጣም ፡ ተደነቀ ። ያልሆነ ፡ ጥያቄ ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ መጣ



ችም ፡ በጣም ፡ ይቆጣ ፡ ጀመረ ። ካንድም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ እያመጣ ፡ ሊያሳምናት ፡ ጀመረ ።

ዳግም ፡ የገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ቍጥር ፡ እንድትነግረው ፡ ፈቃድ ፡ አደረገ ። እርሷም ፡ በትክክል ፡ የመለሰች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለንጉሡ ፡ አማካሪ ፡ የምትሆን ፡ ብልህ ፡ ሴት ፡ ነችና ፡ በነጻ ፡ ተቀመጭ ፡ ልትባል ፡ ታሰበች ። እርሷም ፡ ለሦስት ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ የሰጠችውን ፡ ጥያቄ ፡ እንዲቀበላት ፡ ተስማሙ ። ይህንም ፡ እሺ ፡ እሺ ፡ ሲባባሉ ፡ ያንን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ምንም ፡ ምግብ ፡ እንዳይቀምስ ፡ እዘዘችው ። በመጨረሻውም ፡ ይህም ፡ ውላቸው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ብልት ፡ ሥጋ ፡ በጣህን ፡ አድርጋ ፡ አቀረበችለትና ፡ ገንዙበህ ፡ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ብልት ፡ ሥጋ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አያወጣልህምና ፡ ተናዘዝ ፡ አለችው ።

ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ እርሱ ፡ በዚህ ፡ በበለጠ ፡ ዕውቀቷ ፡ ከርስዋም ፡ ያገኘው ፡ ምክርና ፡ ሐቀኝነት ፡ በእውነት ፡ አስደንቆት ፡ ሁል ጊዜ ፡ ይህን ፡ ግራ ፡ ዐይኔን ፡ የምሠራበትንና ፡ የምጠቅምበትን ፡ እንድታስታውሺኝ ፡ ብሎ ፡ ልጁን ፡ አጋብቶ ፡ አስቀመጣት ።

ይች ፡ የመስኮብ ፡ ልጃገረድ ፡ እንዲህ ፡ አድርጋ ፡ ጥበበኛ ፡ መሆንዋ ፡ ምን ፡ ብታደርግ ፡ ነው ?

## ሁለት ፍየሎች ::

ሁለት ፡ ፍየሎች ፡ ምናምን ፡ በሌለበት ፡ ስፍራ ፡ ባንድ ፡ ተራራ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ተገናኙ ። እርሱም ፡ ጠባብ ፡ ነበርና ፡ ለያንዳንዱ ፡ መተላለፊያ ፡ ስፍራ ፡ አልተገኘላቸውም ። ዙረውም ፡ ለመመለስ ፡ ቢያስቡ ፡ ሳይሆንላቸው ፡ ቀረና ፡ አጥብቀው ፡ ተቸገሩ ።

ወደ ፡ ላይም ፡ እንዳይወጡ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ተራራ ፡ ሆነባቸው ፡ ወደታችም ፡ እንዳይወርዱ ፡ ጅው ፡ ያለ ፡ ዓዘቅት ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ።

እንግዲህ ፡ እኒህ ፡ ሁለት ፡ ፍየሎች ፡ ምን ፡ ያደርጉ ፡ ይመስልሃል ? አንደኛው ፡ ቀስ ፡ አለና ፡ በጠባቡ ፡ ተረተር ፡ ላይ ፡ ተጠግቶ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ አድርጎ ፡ ተጋደመ ። ሁለተኛውም ፡ በዕርጋታና ፡ በጸጥታ ፡ ሁኖ ፡ በወዳጁ ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ በቀላሉ ፡ ተራምዶ ፡ ሄደ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ተራምዶ ፡ የነበረው ፡ ፍየል ፡ ከነበረበት ፡ ስፍራ ፡ ብድግ ፡ አለና ፡ ምንም ፡ እንዳች ፡ ሳይሆን ፡ ካንዱ ፡ ቋጥኝ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቋጥኝ ፡ መዝለል ፡ ቻለ ። ወደ ፡ ኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ደርሶ ፡ ሣሩን ፡ ለመንጨት ፡ በቃ ።

ሁለት ፡ ሌሎች ፡ ፍየሎች ፡ ግን ፡ ሸለቆውን ፡ ትተው ፡ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ ወጡና ፡ በወንዙ ፡ አፋፍ ፡ ተገናኙ ። በዚያም ፡ ካንዱ ፡ ወገን ፡ ወደሌላው ፡ የማያራምድ ፡ ግንድ ፡ ተጋድሞበት ፡ ነበር ።

ትዕቢተኞቹ ፡ ፍየሎች ፡ እኔ ፡ ልቅደም ፡ እኔ ፡ ልቅደም ፡ በመባባል ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩ ። አንዱም ፡ አንዱን ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ይመለሳል ፡ ሲባባሉ ፡ በያንዳንዱ ፡ እግራቸው ፡ ዛፉን ፡ ረገጡና ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆመው ፡ ተፋጠጡ ።

ግን ፡ ከርሳቸው ፡ ምንም ፡ መንገድ ፡ የሰጠ ፡ የለምና ፡ በመጨረሻ ፡ በጠባቡ ፡ ድልድይ ፡ መካከል ፡ ተገናኙ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እግራቸው ፡ ተሰናከሉ ፡ ወደ ፡ ዓዘቅቱ ፡ ወደቁ ። እስኪጠፉ ፡ ድረስ መጋፋትንና ፡ በቀንዳቸው ፡ መዋጋትን ፡ ጀመሩ ።

በጊዜው ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ መንገድ ፡ ለቆለት ፡ ቢሆን ፡ ሁለቱም ፡ ይድኑ ፡ ነበር ። በልቡ ፡ የታበየ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ፍየሎቹን ፡ የሚመስሉ ፡ እነማን ፡ ናቸው ?
ልታውቁ ፡ ትችላላችሁን ?

## አሁን አርጅቻለሁ ፡፡

እኔ ፡ ሽማግሌ ፡ ውሻ ፡ ነኝና ፡ የምጠቅም ፡ አይደለሁም ። ቢሆንም ፡ ገና ፡ ጐበዝ ፡ ሳለሁ ፡ ከሙሉ ፡ ልቤ ፡ እንዳገለገልሁት ፡ ያውቃልና፡ ጌታዬ ፡ ይወደኛል ።

ጌታዬ ፡ ገና ፡ ጐበዝ ፡ ልጅ ፡ ሳለ ፡ አብረን ፡ በመስኩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንድንጫወት ፤ በሜዳውም ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ እሽቅድምድም ፡ እናደርግ ፡ እንደ ፡ ነበርን ፡ ዐውቃለሁ ።



ሁልጊዜ ፡ ያዝንልኝ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ አይመታኝም ፡ ነበር ። ጌታዬ ፡ ይፈልገው ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ የተዘጋጀሁ ፡ ነኝና ፡ መመታት ፡ እንደማይገባኝ ፡ እርሱ ፡ ያውቃል ።

ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ባስተማረኝ ፡ ጊዜ ፡ ያቅሜን ፡ ያህል ፡ ለማወቅ ፡ ተጣጣርሁ ። ጌታዬ ፡ ሊያደርገው ፡ ከኔ ፡ የሚፈልገውን ፡ እንደ ፡ ምችለው ፡ ያህል ፡ ሞከርሁ ። አንድ ፡ ጊዜም ፡ ካወቅሁ ፡ በኋላ ፡ ከቶ ፡ አልረሳውም ።

ከርሱ ፡ ጋራም ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንሄድና ፡ በሩጫ ፡ ወደ ቤት ፡ እመለሳለሁ ። አሁን ፡ እርሱ ፡ ትልቅ ፡ ልጅ ፡ ሆኗል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሲመጣ ፡ ባየሁት ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ሩጬ ፡ እንደምቀበለው ፡ ያውቃል ፡ ለማለት ፡ እደፍራለሁ ።

በርሱ ፡ ፊንታም ፡ እንድሸከም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የመጽሐፉን ፡ ኰሮጆ ፡ ይሰጠኛል ፤ መንገዱንም ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ ተሸክሜ ፡ በጎን ፡ በጎኑ ፡ ስሄድ ፡ እጅግ ፡ እኰራለሁ ።

ለጌታዬ ፡ ለወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተስፋዬ ፡ የምትባል ፡ እኅት ፡ ነበረችው ። አንድ ፡ ቀን ፡ በሣሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ በእጅዋ ፡ ብስኩት ፡ ይዛ ፡ ነበረ ።

አንድ ፡ ራብተኛ ፡ ውሻ ፡ አያትና ፡ የያዘችውን ፡ ብስኩት ፡ ለመንጠቅ ፡ ወያርሷ ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ። በተስፋዬ ፡ አቅራቢያ ፡ ከቍጥቋጦው ፡ በኋላ ፡ ተጋድሜ ፡ ነበርና ፡ እንግዳው ፡ ውሻ ፡ ሲመጣ ፡ ባየሁት ፡ ጊዜ ፡ እርሷን ፡ ለማስጣል ፡ ዘለልሁ ።

ወደ ፡ ተስፋዬም ፡ በረረና ፡ ብስኩቱን ፡ ለመንጠቅ ፡ ሞከረ ፡ ግን ፡ አንገቱን ፡ ይዤ ፡ ጐተትሁት ። በብርቱም ፡ ታገልን ፤ በመጨረሻውም ፡ አሸነፍሁት ።

በተስፋዬም ፡ ጩኸት ፡ እናቲቱ ፡ ፈጥና ፡ መጣች ። ትንሽቱንም ፡ ልጅዋን ፡ ከጉዳት ፡ እንዳዳንኋት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላት ።

ጌታዬ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ ነገረችውና ፡ ከድሮው ፡ ይልቅ ፡ አብልጦ ፡ ወደደኝ ፡ ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከጌታዬ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ የደስታ ፡ ዓመት ፡ ነበረኝ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ እንግዲህ ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝና ፡ አደርገው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ላገለግለው ፡ አልችልም ። ለወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የኔ ፡

ሥዕል ፡ አለው ። በቤቱም ፡ ክፍል ፡ ተንጠልጥሏል ፤ ጐበዝ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እታይ ፡ እንደ ፡ ነበርሁ ፡ በዚህ ፡ ታዩ ታላችሁ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ የምጠቅም ፡ ውሻ ፡ ነበርሁ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ አይተኸኝ ፡ እንኳ ፡ ብትሆን ፡ ዛሬ ፡ አታውቀኝም ።

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ነበረኝ ፡ ላመሰግን ፡ ይገባኛል ። የኔን ፡ ጌታ ፡ የሚመስሉ ፡ ብዙ ፡ ጌቶች ፡ ቢኖሩ ፡ መልካም ፡ ነበር ። እንደኔ ፡ ያለ ፡ ሽማግሌ ፡ የታመነ ፡ አገልጋይ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ውሻ ቢሆን ፡ ከቶ ፡ አይረሳም ።

በሬ ፡ የገዛውን ፡ ዐወቀ ፤ አህያም ፡ የጌታውን ፡ ጋጥ ።
እስራኤል ፡ ግን ፡ አላወቀም ፤ ሕዝቤም ፡ አላስተዋለም ።

## ነብርን የሚመስል አውሬ ።

ይህ ፡ አውሬ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ የድመት ፡ አምሳያ ፡ እንስሳ ፡ ነው ። የሚገኘውም ፡ በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ ነው ። ቁመናው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፤ ብጫነቱም ፡ በጥቁረት ፡ የተዥጐረጐረ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ዝብርቅርቅ ፡ አይደለም ።

ከቅርንጫፍ ፡ ወደ ፡ ቅርንጫፍ ፡ እየተራመደ ፡ እንደ ፡ ድመት ፡ ይዘላልና ፤ ስለዚህ ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ የዛፍ ፡ ነብር ፡ ይባላል ። አንብሳና ፡ ነብር ፡ ሊደርሱበት ፡ የማይችሉትን ፡ ማናቸውንም ፡ ፍጥረት ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል ። በታደነም ፡ ጊዜ ፡ እንደሚችል ፡ አድርጎ ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ይሸሸጋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ውሾቹ ፡ እየሮጡ ፡ ቀስቅሰው ፡ ያገኙታል ። ከጫካውም ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ ሊያድን ፡ ወደ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ይወጣል ። ስለ ፡ ሆነ ፡ ከውሾቹ ፡ ያመልጣል ፡ እንጂ ፡ ከአዳኞቹ ፡ ጥይት ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም ። ደግሞ ፡ አዳኞቹ ፡ እንኳ ፡ ቢሆኑ ፡ ደፍረው ፡ አይቀርቡትም ። ተወርውሮ ፡ እንዳይነጥቃቸው ፡ ርቀው በጥንቃቄ ፡ ይቆያሉ ፡ እንጂ ፡ አይቀርቡትም ። የቆሰለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ወደርሳቸው ፡ ይዘላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ጥይት ፡ ያስቀሩታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ አዳኞች ፡ በቆሰለው ፡ ነብር ፡ የተጐዱ ፡ ይገኛሉ ።



ይህ ፡ አውሬ ፡ እንደ ፡ ቀበሮዎች ፡ ጫጩቶችን ፡ ይወዳል ። ሌሊትም ፡ ሲሆን ፡ ዶሮዎች ፡ ወዳሉበት ፡ እየመለገ ፡ ይገባል ። የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ግን ፡ የነብር ፡ እንግዳ ፡ መጥቶበት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ማልዶ ፡ ያውቀዋል ፤ ነብሩም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ዶሮዎችን ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ይረዳዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ይህ ፡ አውሬ ፡ ለማዳ ፡ ይሆንና ፡ ባኳኋኑ ፡ ተጫዋችና ፡ ገር ፡ ይመስላል ። ግልገሎቹም ፡ የሚያምሩና ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ እንስሶች ፡ ይሆናሉ ። እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ እንደ ፡ ቡችሎች ፡ እየዘለሉ ፡ ሲጫወቱ ፡ ይታያሉ ።

## ጧትና ማታ ።

እንዴት ፡ እንደ ፡ በራ ፡ ተመልከት ፤ ፀሐይም ፡ ወጣ ፤ ወፎችም ፡ ተንጫጩ ። ሲዘፍኑ ፡ ትሰማለህን ? ንቦችም ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ከወጡም ፡ ቆይተዋል ። በቀፎው ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠን ፡ እንድናያቸው ፡ ፈጥነን ፡ እንሂድ ።

ፀሐይ ፡ ሲወጣ ፡ ሳለ ፡ ከወፎችና ፡ ከንቦች ፡ ጋራ ፡ አብረን ፡ ብንነሣ ፡ ላንተና ፡ ለኔ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ጠብቆሃልና ፡ አሁን ፡ ተንበርክከህ ፡ እመስግን ። እንዲባርክህና ፡ እንዲጠብቅህም ፡ እርሱን ፡ ለምን ።

ፀሐዩ ፡ እንደ ፡ ተቀለቀለ ፤ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ ሰማዩ ፡ እንደ ፡ ቀላ ፤ ፈጥኖም ፡ እንዲጨልም ፡ እይ ።

ወፎችም ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ ሰፍረዋል ። በያንዳንዱም ፡ በክንፉ ፡ ራሱን ፡ እንዲሸፍን ፡ እይ ።

ደግሞም ፡ አንተ ፡ ደኅና ፡ እደሩ ፡ ብለህ ፡ ወደ ፡ መኝታህ ፡ ለመሄድ ፡ ጊዜህ ፡ ነው ። ግን ፡ ስለ ፡ ፍቅሩና ፡ ስለ ፡ ጥበቃው ፡ ብዛት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እስከታመሰግን ፡ ተንበርክከህም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እስከትለምን ፡ ድረስ ፡ አትረፍ ።

በሌሊትም ፡ እንዲጠብቅህ ፡ ብትለምነው ፡ ይሰማሃል ። ከማናቸውም ፡ አደጋ ፡ ይጠብቅሃል ። እግዚአብሔር ፡ እንዲጠብቅህ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገባሃል ?

አልፈራም ፣ እግዚአብሔር ፡ ቅርብ ፡ ነው ።
በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሌሊቱ ፡ እንደ ፡ ቀን ፡ ነው ።
ባንቀላፋም ፡ በረድኤቱ ፡ እጠበቃለሁ ።
እግዚአብሔር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፣ ለምን ፡ እፈራለሁ ?

## የሕንድ ሰውና የእስፓንያ ሰው ።

አንድ ፡ የእስፓንያ ፡ ሰው ፡ መንገደኛ ፡ በበረሃ ፡ ውስጥ ፡ ሲሄድ ፡ ሳለ ፡ በበረሃ ፡ መካከል ፡ ሕንዳዊ ፡ ከሆነ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ። ሁለቱም ፡ በፈረስ ፡ በፈረስ ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ የእስፓንያው ፡ ሰው ፡ ፈረሱ ፡ አንካሳ ፡ ስለ ፡ ሆነበት ፡ ይዞኝ ፡ አይዘልቅም ፡ በማለት ፡ ፈርቶት ፡ ነበር ።

እርሱም ፡ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ ጠንካራና ፡ ልጅነት ፡ ያለውን ፡ የሕንዱን ፡ ሰው ፡ ፈረስ ፡ በርሱ ፡ ፈረስ ፡ እንዲለውጠው ፡ ሕንዱን ፡ ጠየቀው ።

ሕንዳዊውም ፡ ሰው ፡ ይህነን ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ ጥያቄውን ፡ ሊቀበለውና ፡ ሊፈጽምለት ፡ እንቢ ፡ አለው ። ይህም ፡ የእስፖንያው ሰው ፡ ጠብ ፡ ለማንሣት ፡ ሞከረ ። አንድ ፡ ሁለት ፡ ሲሉ ፡ ጠቡን ፡ አጋነኑትና ፡ በፍጥነት ፡ ይማቱ ፡ ጀመር ።

የእስፓንያው ፡ ሰው ፡ ለጠብ ፡ በጣም ፡ የተሰናዳ ፡ ሰው ፡ ስለ ሆነ ፣ የሕንዱን ፡ ሰው ፡ አሸነፈና ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ የሆነውን ፡ ፈረሱን ፡ ቀምቶት ፡ መንገዱን ፡ ይጓዝ ፡ ጀመረ ። ሕንዳዊውም ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ቅርቡ ፡ ከተማ ፡ ተከታተለውና ፡ ፈረሱን ፡ በዳኛ ፊት ፡ ይዞለት ፡ እንዲቀርብ ፡ ይህን ፡ ወንበዴ ፡ ከሰሰው ። የእስፓንያውም ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ የሕንዱ ፡ ሰው ፡ የከሰሰኝ ፡ በውሸት ፡ ነው ፣ ፈረሱንም ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ነኝ ፡ ያሳደግሁት ፡ የራሴ ፡ ከብት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ማለ ።

ዳኛውም ፡ በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ የሚገልጽለት ፡ አንዳች ፡ ምክንያት ፡ ስላጣ ፡ ነገሩን ፡ ለማቃለል ፡ አሰበ ፡ ነበር ። ይህም ፡ የሕንድ ፡ ሰው ፡ ፈረሱ ፡ የኔ ፡ የራሴ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ጮኸበት ።



ከዚህም ፡ ወዲህ ፡ የሕንዱ ፡ ሰው ፡ በርኖሱን ፡ በፈረሱ ፡ ራስ ላይ ፡ ሸፈነው ።

ዳኛውም ፡ ይህን ፡ የእስፓንያ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ የሕንድ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ፈረስ ፡ ከልጅነቱ ፡ ጀምሬ ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ነኝ ፡ ያሳደግሁት ፣ የኔው ፡ የራሴ ፡ ነው ፡ ይላል ። ያንተ ፡ ከሆነ ፡ ማናቸው ፡ ዐይኑ ፡ ነው ፡ ዕውር ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ይህም ፡ የእስፓንያ ፡ ሰው ፡ እንደ ዚህ ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ ያመጣብኛል ፡ አልመሰለውም ፡ ነበርና ፡ በነገሩ ፡ ሳይጠራጠር ፡ ቀኙ ፡ ዐይኑ ፡ ነው ፡ አለ ።

የሕንዱ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ከፈረሱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ በርኖሱን ፡ አነሣና ፡ የቀኙም ፣ የግራውም ፡ ዐይኑ ፡ ምንም ፡ ዕውርነት ፡ የለበትም ፡ አለ ።

ዳኛውም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በእውነት ፡ ተረዳውና ፡ እንደዚሁ ፡ ለዚህ ፡ ጠንካራና ፡ ብልህ ፡ ለሆነ ፡ ለሕንድ ፡ ሰው ፡ ፈረሱን ፡ እንዲመልስለት ፡ አዘዘለትና ፡ ነገሩ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተፈጸመ ።

እንደ ፡ ሕንዱ ፡ ሰው ፡ ጠላትን ፡ ተከታትሎ ፡ መያዝ ፡
የሚገባ ፡ መስሎ ፡ ይታይሀልን ? ወይስ ፣ ፈረሱን ፡
ትተኸ ፡ መንገድኸን ፡ ልትቀጥል ፡ ትወዳለህ ?
የምትመርጠው ፡ ማናቸውን ፡ ነው ?

## ዕድልና ለማኝ ።

አንድ ፡ ለማኝ ፡ በመልካም ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ሲመላለስ ፡ ሳለ ፡ ሀብታሞች ፡ ሰዎች ፡ ከቶ ፡ እንዴት ፡ እብዶች ፡ ናቸው ። ብዙ ገንዘብ ፡ እያላቸው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በቃን ፡ አይሉም ። እንደ ፡ ገናም ፡ ይፈልጋሉ ፣ ለኔ ፡ እኮ ፡ አሁን ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ወርቅ ፡ ቢኖረኝ ፡ ይበቃኝ ፡ ነበር ፡ እያለ ፡ ያጉረመርም ፡ ጀመረ ። እንዲህም ፡ እያለ ፡ ሲናገር ፡ ወዲያው ፡ አንዲት ፡ የተዋበች ፡ መልካም ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ታየችውና ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ተናገረችው ።

እኔ ፡ ስሜ ፡ ዕድል ፡ ይባላል ፡ አሁን ፡ አንተን ፡ ላበለጽግ ፡ መጥቻለሁና ፡ ከረጢትህን ፡ ከፍተህ ፡ ያዝ ። ወርቅም ፡ እመላዋለሁ ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንድትጠነቀቅ ፡ አስታውቅሃ

ለሁ ። ከወርቁም ፡ ማናቸውም ፡ ሽራፊ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ቢወድቅ ፡ አፈር ፡ ሁኖ ፡ ይቀርብሃል ፡ አለችው ።

ለማኙም ፡ ከረጢቱን ፡ አቀረበና ፡ ዕድል ፡ ወርቁን ፡ እየዘገነች ፡ ትወረውርለት ፡ ጀመር ። ወዲያውም ፡ ምናልባት ፡ ከረጢትህ ፡ መልቶ ፡ የሚቀደድ ፡ ይመስለኛልና ፡ ይበቃሃል ፡ አለችው ።

ለማኙም ፡ እንኳን ፡ እንኳን ፡ እመቤት ፡ ሆይ ፡ ከረጢቱ ፡ ጠንካራ ፡ ነውና ፡ አይቀደድም ፡ አንድ ፡ እፍኝ ፡ ምሉ ፡ ይጨምሩልኝ ፡ አለ ። ዕድልም ፡ እርሱ ፡ እንዳላት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እፍኝ ፡ ምሉ ፡ ጨመረችለትና ፡ እኔስ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ሽራፊ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የሚችል ፡ አይመስለኝም ፡ አለችው ።

ለማኙ ፡ ግን ፡ ግድ ፡ የለም ፡ እመቤቴ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ይጨምሩልኝ ፡ አለ ። ዕድልም ፡ እንደገና ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ወርቅ ፡ ጨመረችለት ፣ ከረጢቱም ፡ ፈነዳ ፣ ወርቁም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ፈሰሰና ፡ አፈር ፡ መስሎ ፡ ቀረ ።

በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዕድልን ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ከዐይኑ ፡ ተሠወረችበት ። እርሱም ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ወደ ፡ ድኅነቱ ፡ ተመልሶ ፡ ይኖር ፡ ጀመር ።

ዕድልን ፡ እንዳታጣ ፡ ዕድለ ፡ ቢስም ፡ እንዳትሆን ፡ ምን ፡ ልትሠራ ፡ ይገባሃል ?

## የሚያስገርም ግብዣ ::

አንድ ፡ ቀን ፡ አጎታችን ፡ ወደኛ ፡ መጥቶ ፡ ለምሳ ፡ ጠራንና ፡ ከሺሕ ፡ የሚበልጡ ፡ ሠራተኞች ፡ የሚያስፈልግ ፡ ግብዣ ፡ አቀርብላችኋለሁ ፣ አለ ። ከሺህ ፡ ሰው ፡ የሚበልጥ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ነው ። እንግዲያስ ፡ እንዳንድ ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሆናል ፡ ብንለው ፣

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ የሆነ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ነገ ፡ በምሳ ፡ ጊዜ ፡ ታዩታላችሁ ፡ ብሎን ፡ ሄደ ። በነጋታውም ፡ ገና ፡ ቍርሳችንን ፡ ሳንበላ ፡ ወደ ፡ አጎታችን ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ ተደራጅተን ፡ ነበርና ፡ ከዚያው ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ እንደቀድሞው ፡ ሁኖ ፡ ሳይለወጥ ፡ ብናይ ፡ ተደነቅን ።



ወዲያውም ፡ በገበታው ፡ ተቀምጠን ፡ ተበላና ፡ የመዠመሪያው ፡ ሣህን ፡ ተነሣ ። ደግሞም ፡ ዐይናችን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ መዝጊያው ፡ ሲመለከት ፡ ያ ፡ ጣፋጭ ፡ ምግብ ፡ መጣ ። አሁንም ፡ ያው ፡ የወትሮው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አልተጨመረም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወንድሜ ፡ እንሥቶ ፡ አጎታችን ፡ ተስፋ ፡ ካደረገልን ፡ ግብዣ ፡ ይህ ፡ ምንም ፡ አይደለም ፡ አለ ። አጎታቸውም ፡ መልሶ ፡ በርግጥ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ አላቸው ። ያም ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መለሰና ፡ አሁን ፡ በእውነት ፡ ይህን ፡ ትንሹን ፡ ምግብ ፡ ከሺህ ፡ ሰው ፡ የሚበልጥ ፡ ሠርቶታል ፡ ትላለህን ፡ አለ ። ልጄ ፡ ሆይ ፡ እስኪ ፡ ከዚህ ፡ መዠመሪያ ፡ ቅመስለትና ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ጽላቱንና ፡ እርሳሱን ፡ አንሥተህ ፡ ሠራተኞቹን ፡ እንድትቆጥር ፡ ርዳኝ ፡ መጀመሪያ ፡ ይህን ፡ ዱቄት ፡ ለመሥራት ፡ ስንት ፡ ሠራተኞች ፡ ያስፈልጋል ?

አስቀድሞ ፡ መሬቱ ፡ ይታረስና ፡ ይዘራል ፣ ቦይም ፡ ይተለማል ይታረማል ። ቀጥሎም ፡ ይታጨዳል ። ከዚህ ፡ በፊትም ፡ መሣሪያ ፡ ለመሥራት ፡ ብረት ፡ አውጪዎች ፣ አፍላሾች ፡ ቀጥቃጮች ፣ ዕንጨት ፡ የሚቆርጡ ፣ በመጋዝ ፡ የሚሠነጥቁ ፡ አናጢዎችም ፡ አሉበት ። ቀጥሎም ፡ ለቆዳ ፡ ፋቂዎች ፣ ለወፍጮ ፡ ወቃሪዎች ፣ ለፋብሪካ ፡ ሠሪዎች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ዐስብ ። የሚያስፈልገውን ፡ ቅመማቅመም ፡ ሎሚ ፣ ሱካር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ተከፍሎም ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ የሚመጣ ፡ አለ ። መርከብ ፡ ሠሪዎች ፣ መርከብ ፡ ሠራተኞች ፣ የነፋስ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ መርከበኞች ፣ ነጋዴዎችና ፡ ቸርቻሪዎች ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ አሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዕንቍላልና ፡ ወተት ፣ ቅባትም ፡ እንጨምራለን ። አጎቴ ፡ ይበቃል ፣ ይበቃል ፣ አለና ፡ ጮኸ ። በርግጥ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ድረስ ፡ ቆጥረሃል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ልጄ ፡ ሆይ ፡ ሁሉንም ፡ አልቆጠርሁልህምና ፡ ቆይ ፡ አለ ። እኛ ፡ ምግቡን ፡ ማብሰል ፡ ያስፈልገናል ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንቆጥራለን ።

ማዕድን ፡ ቆፋሪዎችንና ፡ ከሰል ፡ አከሳዮችን ፣ ብረታ ፡ ብረቱን ፡ ለመሥራት ፡ ደግሞም ፡ ተጠቅልሎበት ፡ የነበረውን ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቁን ፣ ደግሞም ፡ ጥጡን ፡ የሚያበቅሉ ፡ የሚሰበስቡ ፣ የሚዳምጡ ፡ የሚፈትሉ ፣ የሚነድፉ ፣ የሚያጠነጥኑ ፡ የሸማኔ ፡ ዕቃው

ንም ፡ የሚያዘጋጁ ፡ አሉ ፡ አለው ። ልጁ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አሁን ፡ ከሺህ ፡ የሚበልጡ ፡ ሠራተኞች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ተመሰከረ ።

ሠራተኞቹን ፡ ልንመስል ፡ ይገባናል ?
ወይስ ፡ ምሳ ፡ የሚጋበዘውን ፡ ጸሐፊውን ?
ማናቸውን ፡ ልንመስል ፡ ይገባናል ?

## አንተ ታካች ፡፡

አንተ ፡ ታካች ፡ ወደ ፡ ገብረ ፡ ጉንዳን ፡ ሂድና ፡ መንገዷን ፡ ተመልከተህ ፡ ጠቢብ ፡ ሁን ። አለቃ ፤ አዛዥና ፡ ገዢ ፡ ሳይኖራት ፡ መብሏን ፡ በበጋ ፡ ታሰናዳለች ። የምትባላውንም ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ ትሰበስባለች ።

አንተ ፡ ታካች ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትተኛለህ ? ከመኝታህስ ፡ መቼ ፡ ትነሣለህ ? ጥቂት ፡ ትተኛለህ ። ጥቂትም ፡ ታንቀላፋለህ ። ትተኛም ፡ ዘንድ ፡ እጅህን ፡ ታስተላልፋለህ ።

ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ድኅነት ፡ እንደ ፡ ፈጣን ፡ መንገደኛ ፤ ችጋርም ፡ ስለት ፡ እንደ ፡ ታጠቀ ፡ ሰው ፡ ይመጣብሃል ።

## በስጦታ ሳይ ፡፡

ለወፍ ፡ ከጸጉር ፤ ከላባ ፤ ከሣር ፤ ከቅርንጫፍ ፤ አሻሽላ ፡ ቤት ፡ እንድትሠራ ፤ ቅርንጫፎቹንስ ፡ ደርድራ ፡ እንድትታታቸው ፡ ማን ፡ አስተማራት ?

ጠባቡን ፡ ጉድጓዳቸውን ፡ እንዲፈለፍሉና ፡ ባማረው ፡ በበጋ ፡ ጊዜ ፡ ሰብላቸውን ፡ ሰብስበው ፡ በክረምት ፡ ጊዜ ፡ እንዲበሉ ፡ ለቊጫጮች ፡ ዕውቀትን ፡ ማን ፡ ሰጠ ?

ከድሮ ፡ ጀምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተማራቸው ፤ ዕውቀትንም ፡ ሰጣቸው ፡ እንዲሁም ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃዱን ፡ ለማድረግ ፡ በጸለዩ ፡ ጊዜ ፡ ልጆችን ፡ ያስተምራል ።

ማነው ፡ ያስተማረ ፡ ቤት ፡ መሥራትን ፡ ለወፍ ፤
ከጸጉርና ፡ ከሣር ፡ ደግሞ ፡ ከቅርንጫፍ ?



ማለዳ ፡ ተነሥተው ፡ ንቦች ፡ እንዲበሩ ፤
ማን ፡ አዟቸው ፡ ኑሯል ፡ መልካም ፡ የሚሠሩ ።
ከዱሮ ፡ ጀምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስተምራል ፤
እንዲህም ፡ አድርጎ ፡ ዕውቀትን ፡ ይሰጣል ።
አንተም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃዱን ፡ ለምን ፤
እግዚአብሔር ፡ ይችላል ፡ ሊሰጥህ ፡ ሁሉን ።

ለሠራተኛውስ ፡ ንብ ፡ መዓዛ ፡ ባላቸው ፡ አበቦች ፡ መካከል ፡ እንዲበር ፡ በጕተራውም ፡ አጠገብ ፡ አውላውን ፡ እንዲያከማች ፡ ማን ፡ አስተማረው ?

## ችር ጠባቂ ፡፡

ጥያቄ ፡ የጠባቂው ፡ ሥራ ፡ ምንድንነው ?

የሚበሉት ፡ ሣር ፤ የሚጠጡት ፡ ውሃ ፡ እንዲያገኙ ፡ የበጎቹን ፡ መንጋ ፡ መመልከት ፡ ነው ። ቀበሮ ፡ ወይም ፡ ተኩላና ፡ ነብር ፡ ይዞአቸው ፡ እንዳይሄዱ ፡ መትጋት ፡ ነው ።

ጠባቂው ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ከበጎቹ ፡ ጋራ ፡ አብሩዋቸው ፡ ይውላል ። ሌሊትም ፡ በበረት ፡ ይዘጋባቸዋል ፡ ፀሐይም ፡ በገረረ ፡ ጊዜ ፡ በጎቹን ፡ በሜዳ ፡ አይተዋቸውም ። ያለዚያስ ፡ በጫካ ፡ ይበተናሉ ። ባውሬም ፡ ተበልተው ፡ ይቀራሉ ። ብርቱ ፡ ዝናም ፡ ቢጥልም ፡ አደጋ ፡ እንዳያገኛቸው ፡ አብሩዋቸው ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ።

በግ ፡ ሰውን ፡ የማይጐዳ ፡ እንስሳ ፡ ነው ። መቃወምም ፡ አይችልም ፤ ከውሻ ፤ ወይም ፡ ከቀበሮ ፤ ወይም ፡ ከነብር ፡ ራሱን ፡ ማዳን ፡ አይችልም ። በግ ፡ ሞኝ ፡ እንስሳ ፡ ነውና ፡ ከመንገድ ፡ የተሳሳተ ፡ እንደሆነ ፡ ፈልጎ ፡ ማግኘት ፡ አይቻልም ። የዱር ፡ አውሬ ፡ ቦጫጭቆት ፡ ይቀራል ፤ ወይም ፡ ጕርፍ ፡ ይወስደዋል ።

በጎቹንና ፡ ጠቦቶቹን ፡ ከእሾህና ፡ ከጐርፍ ፡ ለማዳን ፡ አውሬውንም ፡ ለማባረር ፡ እጅግ ፡ ንቅ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ለጠባቂው ፡ ያስፈልገዋል ። በጎችም ፡ አብዝተው ፡ እንዲመገቡ ፡ ጠቦቶቹንም ፡ በደከሙ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሸከማቸውና ፡ ለምለም ፡ ሣር ፡ ወደ ፡ በቀለ

በት ፡ ጥሩ ፡ ውሃ ፡ ወዳለበት ፡ እንዲመራቸው ፡ ርኅሩኅ ፡ መሆን ፡ ለጠባቂው ፡ ይገባዋል ።

ጠባቂው ፡ የጠፉትን ፡ በጎች ፡ ተከታትሎ ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ በረት እንዲመልሳቸው ፡ ታጋሽ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፤ ስለ ፡ በጎቹ ፡ የሚጠነቀቅ ፤ ነፍሱንም ፡ ስለርሳቸው ፡ የሚለውጥ ፡ እንዲሆን ፡ ይገባዋል ።

ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንም ፡ እንደ ፡ በጎችና ፡ እንደ ፡ ግልገሎቻቸው ፡ ናቸው ። በቅን ፡ የሚመራቸው ፤ ለክፉም ፡ የሚመክትላቸው ፡ የሚጠብቃቸውና ፡ የሚጠነቀቅላቸው ፡ እረኛ ፡ ግድ ፡ ያስፈልጋቸዋል ።

እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ የሚወስደንና ፡ ክፉም ፡ እንድናደርግ ፡ የሚፈትነን ፡ አንድ ፡ አባብ ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ እንዲያስተምረንና ፡ ከኃጢአትም ፡ እንዲያድነን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲመልሰን ፡ አንድ ፡ ጠባቂ ፡ ያስፈልገናል ።

ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ማነው ?

## ነብርና ድኩላ ።

ነብርና ፡ ድኩላ ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ድረስ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ፍቅር ፡ የሌላቸው ፡ ቂመኞች ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ ስምምነት ፡ ያላቸው ፡ አልነበሩም ።

እንዲህም ፡ ሁነው ፡ ተሸማምቀው ፡ ሲኖሩ ፡ ነብር ፡ እንሥቶ ፡ ድኩላን ፡ ሲመክረው ፡ አንተ ፡ ሆይ ፡ እኔና ፡ አንተ ፡ እንደዚህ ፡ ሁነን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ እንኖራለን ። አንተስ ፡ በየደረስኸበት ፡ እየዞርኽ፡ ስሜን ፡ ለምን ፡ ታጠፋለህ ፡ ዕድሜህንስ ፡ ሁሉ ፡ በየጥሻውና ፡ በየቍጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ እየተሹለከለክኽ ፡ በሥጋት ፡ ለምን ፡ ትኖራለህ ? ለኔም ፡ ላንተም ፡ ይሻለናልና ፡ ተማምለን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተጋብተን ፡ በፍቅር ፡ አብረን ፡ እንኑር ፡ አለው ።

ድኩላም ፡ ሳይመስለው ፡ ቃሉን ፡ ያስተሐቀርሁ ፡ ይመስለውና ይበቀለኛል ፡ ብሎ ፡ አይሆንም ፡ እንጂ ፡ ከሆነማ ፡ ምን ፡ ባሰኝ ፡



አለና ፡ ሲፈራ ፡ ሲቸር ፡ መሐላውን ፡ ተቀበለ ። ውልም ፡ ተዋዋሉና ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፡ ጀመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍቅር ፡ እየሰፋ ፡ ቂም ፡ እየጠፋ ፡ የሄደ ፡ መሰለውና ፡ የድኩላ ፡ ፊቱ ፡ እጅግ ፡ አወለወለ ፡ ገላውም ፡ አብረቀረቀ ፡

ነብርም ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ልቡን ፡ ሸፈጥ ፡ አደረገው ፡ መሐላውንም ፡ ሊያፈርስ ፡ ተቅበጠበጠ ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ ለሽርሽር ፡ ወጥተው ፡ እየተዝናኑ ፡ ሲጫወቱ ፡ ነብር ፡ ድኩላን ፡ እረ ፡ በል ፡ ድኩላ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ ድኩላም ፡ አቤት ፡ ጌታው ፡ ምን ፡ ይላሉ ፡ ብሎ ፡ ቀረብ ፡ አለ ፤ ነብርም ፡ መሐላ ፡ ያፈረሰ ፡ ወዳጅ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ እርሱም ፡ በልጁ ፡ በልጅ ልጁ ፡ ይደርስ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ አለው ።

ይህነንም ፡ ሲነጋገሩ ፡ ነብር ፡ ብድግ ፡ አለና ፡ እንግዲያስ ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ አንተን ፡ ልብላና ፡ መሐላው ፡ በልጄ ፡ ይድረስ ፡ ብሎ ፡ በድኩላው ፡ ራስ ፡ ተከመረበት ።

ድኩላውም ፡ አልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይ ፡ እንደሚሉ ፡ አመልጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲፈራገጥ ፡ የድኩላው ፡ ቀንድ ፡ በነብሩ ፡ ሆድ ፡ ዕቃ ፡ ጥልቅ ፡ አለና ፡ የነብሩን ፡ አንጀት ፡ ዘረገፈው ።

ነብርም ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ አይቶ ፡ ምነው ፡ ድኩላ ፡ መሐላ ፡ የሚደርስ ፡ በልጅ ፡ ነው ፡ ብለኸኝ ፡ አልነበረምን ፡ ቢለው ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ምናልባት ፡ አባትህ ፡ ምሎ ፡ ከድቶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ምን ፡ ዐውቅልሃለሁ ፡ አለውና ፡ ነገራቸውም ፡ በዚህ ፡ ተጨረሰ ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ከክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ አትዋዋሉ ፤ ዐመጸኞች ፡ ለክፉ ፡ ሥራ ፡ ይጥራሉና ፡ በወጥመዳቸው ፡ ተብትበው ፡ እንዳይጥሏችሁ ፡ ተጠበቁ ።

አእምሮ ፡ የጐደለው ፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ሁልጊዜ ፡ በክፉ ፡ ወጥመድ ፡ ይወድቃል ።

ለነብርና ፡ ለድኩላ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆኑ ፡
እነማን ፡ ይመስሉሃል ?

## ጉጉት ፡፡

ጉጉት ፡ የሌሊት ፡ አሞራ ፡ ይባላል ። የቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ብርቱና ፡ የሚያጥበረብር ፡ ስለሆነበት ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ በዛፎች ፡ ቅጠል ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በፉካ ፡ ተሸሽጎ ፡ ይውላል ። በጨለመም ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ ይወጣና ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይበርራል ። አይጦችንና ፡ ወፎችንም ፡ ይፈልጋል ።

ሲበርም ፡ ሳለ ፡ ክንፎቹ ፡ አይሰሙም ፣ ስለዚህ ፡ አይጦችና ፡ ወፎች ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪቀርባቸው ፡ አይሰሙትም ። ወፎች ፡ ሁሉ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ያውቁታልና ፡ አጥብቀው ፡ ይፈሩታል ።

ግን ፡ ቀን ፡ ለቀን ፡ ወጥቶ ፡ ያገኙት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ከበው ፡ ባለ ፡ ዐቅማቸው ፡ ይጠቀጥቁታል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እየተድበሰበሰ ፡ ይቀራል ፡ እንጂ ፡ እንደምንም ፡ ሆኖ ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም ።

እንዴት ፡ እንዳላገጡብህ ፡ አስተውል ።

ምስኪኑ ፡ ጉጉት ፡ መፍጠን ፡ እንደሚቻልህ ፡ ወደ ፡ ፉካህ ፡ ተመለስ ።

ጨለማን ፡ ታደርጋለህ ፣ ሌሊትም ፡ ይሆናል ። በርሱም ፡ የዱር አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ይንቀሳቀሳሉ ።

## አበበችና አንዲት ለማዳ ወፍ ፡፡

አበበች ፡ በወስከምት ፡ ተይዛ ፡ የተቀመጠች ፡ አንዲት ፡ ወፍ ፡ ነበረቻት ፣ ወፍዋም ፡ መጥታ ፡ ከአበበች ፡ እጅ ፡ ትመገብ ፡ ነበረች ፣ አበበችም ፡ ወፍዋን ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ እያወጣች ፡ ትለቃት ፡ ነበረች ። እርሷም ፡ በወስከምቱ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ ትቀመጥና ፡ ወይም ፡ በክፍሉ ፡ ዙሪያ ፡ ትበር ፡ ነበረች ።

ወፍዋንም ፡ የምትመግባት ፡ አበበች ፡ ራሷ ፡ ነበረች ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡ ከርስዋ ፡ በቀር ፡ ወፍዋን ፡ የሚመግብ ፡ አልነበረም ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አክስቲቱ ፡ የሚያማምሩ ፡ አዳዲስ ፡ ያሻንጉሊቶች ሣጥን ፡ ሠራችና ፡ ላበበች ፡ ላከችላት ፣ ባሻንጉሌቶቹም ፡ ስትጫወት ፡ ደስ ፡ አላትና ፡ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ ዋለች ። በዚያም ፡ ቀን ፡ አበበች ወፍዋን ፡ አልመገበቻትም ፣ በማግስቱም ፡ ደግሞ ፡ አበበችን ፡ ለማየት ፡ አንዲት ፡ ወዳጅዋ ፡ መጣችና ፡ የናፍቆታቸውን ፡ ሲጫወቱ ፡ ምስኪኒቱ ፡ ወፍ ፡ ምግብ ፡ ሳታገኝ ፡ ቀረች ።

አበበችም ፡ ከወዳጅዋ ፡ ጋራ ፡ ቀኑን ፡ በአሻንጉሊቶች ፡ ሣጥን ሲጫወቱ ፡ ዋሉ ። በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ አበበች ፡ አሻንጉሊቶቹን ፡ ሰልችታቸው ፡ ኑሮ ፡ ከወፊቱ ፡ ጋራ ፡ ልትጫወት ፡ ሄደች ፡ አንዳች ፡ ፍሬም ፡ ልትሰጣት ፡ ወደ ፡ ወስከምቱ ፡ ቀረበች ። ነገር ፡ ግን ፡ ያች ፡ ምስኪን ፡ ወፍ ፡ ሙታ ፡ በወስከምቱ ፡ ውስጥ ፡ ተጋድማ ፡ ተገኘች ። ምክንያቱም ፡ ምግብ ፡ ስለ ፡ አጣች ፡ ነው ።

ይህነን ፡ አይታ ፡ አበበች ፡ ምንኛ ፡ አዘነች ። ልጆችና ፡ ልጃገረዶች ፡ ይህን ፡ የሚያሳዝን ፡ ታሪክ ፡ በልባችሁ ፡ አኑሩት ፣ ለምትወዱትም ፡ እዘኑለት ፡

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጫካ ፡ ያለች ፡ ወፍ ፡ እንዲህ ፡ አለች ።

> የጌቶች ፡ አዳራሽ ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል ፣
> በጠባብ ፡ ጎጆዬ ፡ መኖር ፡ ይሻለኛል ።
> ከዚኽች ፡ ምሳሌ ፡ ምን ፡ ትማራለኽ ?



## ገበሬና ታማኝ ውሻው ፡፡

ባንድ ፡ መንደር ፡ ታማኝ ፡ ውሻ ፡ ያለው ፡ ገበሬ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፣ ውሻውም ፡ የጌታውን ፡ ቤት ፡ ተግቶ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ። አነር ፡ ወይም ፡ ሌባ ፡ ከቶ ፡ ወደዚያ ፡ ደፍሮ ፡ ሊገባ ፡ አልቻለም ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ገበሬውን ፡ ገንዘብ ፡ ቸገረውና ፡ ውሻውን ፡ አስከትሎ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያበድር ፡ ነጋዴ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መንደር ፡ ሄደ ።

እርሱም ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ተበደረና ፡ ብድሩን ፡ እስኪከፍል ፡ ድረስ ፡ ውሻውን ፡ ስለ ፡ ዕዳው ፡ እንደ ፡ ዋስ ፡ አሳልፎ ፡ አስያዘው ። ውሻውም ፡ የጌታውን ፡ አሳብ ፡ ያውቃልና ፡ የጌታውን ፡ ቤት ፡ እንደሚጠብቅ ፡ አድርጎ ፡ የነጋዴውን ፡ ቤት ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀንም ፡ የነጋዴው ፡ ልጅ ፡ ባልጋ ፡ ተኝቶ ፡ ውሻውም ፡ ሲጠብቅ ፡ ሳለ ፡ አልጋው ፡ በገመድ ፤ ከጣራው ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበርና ፡ እባቡ ፡ በገመዱ ፡ ላይ ፡ እየተሳበ ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ ቀረበ ። ታማኙ ፡ ውሻ ፡ ይኸን ፡ አየና ፡ ወደ ፡ እባቡ ፡ ተራመደ ፤ እባቡንም ፡ ይዞ ፡ ከሁለት ፡ ቆራርጦ ፡ ገደለው ።

ወደዚያውም ፡ እናቲቱ ፡ መጥታ ፡ የሞተውን ፡ እባብና ፡ በውሻው ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ደም ፡ አየች ። ውሻውም ፡ እባቡን ፡ ገድሎ ፡ የልጅዋን ፡ ነፍስ ፡ እንዳዳነ ፡ ዐወቀች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ውሻውን ፡ በጣም ፡ አመሰገነችና ፡ ባልዋ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ይህነን ፡ ታሪክ ፡ አጫወተችው ። ነጋዴውም ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለውና ፡ ውሻውን ፡ በፍቅር ፡ ይዞ ፡ ይህን ፡ ውሻ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ትቶለት ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ገበሬውን ፡ እጅግ ፡ አመስግኖ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ለገበሬው ፡ ሲጽፍ ፡ በወረቀቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ውሻህ ፡ የልጄን ፡ ሕይወት ፡ አዳነ ፤ ከተበደርኸኝ ፡ ገንዘብ ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጥ ፡ ተቀብያለሁና ፡ እንግዲህ ፡ እንተን ፡ ገንዘብ ፡ እምጣ ፡ ብዬ ፡ አልፈልግህም ። እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ውለታ ፡ የዋለልኝን ፡ ውሻህን ፡ መልሼልሃለሁ ፡ አለና ፡ ነጋዴው ፡ ወረቀቱን ፡ በውሻው ፡ አንገት ፡ አስሮ ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ መለሰው ።

በዚያም ፡ ቀን ፡ ገበሬው ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ነጋዴው ፡ ሲመለስ ፤ ውሻው ፡ በመንገድ ፡ እየሮጠ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሲመጣ ፡ አየና ፡ እጅግ ፡ ተቆጥቶ ፡ ውሻውን ፡ አለው ፤ እኔ ፡ ገንዘቡን ፡ ይዤ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ስሄድ ፡ አንተ ፡ ነጋዴውን ፡ አታለህ ፡ አምልጠህ ፡ መጣህን ? ብሎ ፡ ተናደደና ፡ በያዘው ፡ በትር ፡ ቢመታው ፡ ውሻው ፡ በእግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ያ ፡ ገበሬ ፡ በውሻው ፡ አንገት ፡ ታስሮ ፡ የነበረውን ፡ ደብዳቤ ፡ ፈታና ፡ እያነበበ ፡ ነገሩን ፡ በተረዳው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አጥብቆ ፡ አዘነና ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፤ አዬ ፡ አዬ ፡ ለካ ፡ ውሻው ፡ ነጋዴውን ፡ አልከዳውም ፡ ኑሯል ፤ ውሻው ፡ ወደኔ ፡ እንዲመጣ ፡ ነጋዴው ፡ አዞት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ውሻውን ፡ በቍጣዬ ፡ መምታቴ ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፤ እንግዲህ ፡ እኔንና ፡ በጎቹን ፡ የሚጠብቅ ፡ አሁን ፡ ማን ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ እያዘነና ፡ እየተጸጸተ ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ ተመለሰ ።



ወዳጆቼ ፡ ሆይ !

በተቆጣን ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ማስተዋል ፡ እንዳንሠራ ፡ ታሪኩ ፡ ያስጠንቅቀናል ፤ ሳናስብ ፡ ብንሠራ ፡ ግን ፡ በርግጥ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይደርስብናል ።

በተቆጣን ፡ ቀን ፡ ትዕግሥተኞች ፡ ለመሆን ፡ እንድናስብ ፡ ይገባናል ። የሰው ፡ ቍጣ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ አይሠራምና ፡ ከናንተ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለመስማት ፡ የፈጠነ ፤ ለመናገርና ፡ ለቍጣ ፡ የዘገየ ፡ ይሁን ።

ሰው ፡ ሊታገሥ ፡ የሚገባው ፡ ምን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነው ?

## የማታስል ቃል ::

አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ሰውዬ ፡ ዕንጨት ፡ ቍረጥ ፡ ብሎ ፡ ለልጁ ፡ መጋዝ ፡ ሰጠው ። ልጁ ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ሊሠራ ፡ አልወደደምና ፡ አባቱ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ መጋዙን ፡ ወረወረና ፡ ሰበረው ።

ልጁም ፡ እሱ ፡ ተሰበረ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አልሰበርሁትም ፡ እያለ በልቡ ፡ ያወጣና ፡ ያወርድ ፡ ጀመር ። በቃሉም ፡ ራሱን ፡ ሊያታልል ፈለገ ። ነገር ፡ ግን ፡ የውሸት ፡ ቃል ፡ መሆኑን ፡ ልቡ ፡ ያውቃልና ፡ አባቱን ፡ ለማየት ፡ ፈራ ።

አንድ ፡ ቀንም ፡ ከተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ እናቱ ፡ አሁን ፡ ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ሁኗል ፡ ተማሪ ፡ ቤትህ ፡ የሚዘጋው ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ነው ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ወዴት ፡ ኑረሃል ፡ አለችው ፤ ልጁም ፡ መልሶ ፡ እናቴ ፡ ሆይ ፡ ኳስ ፡ ስንጫወት ፡ ሌላውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ረሳነውና ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ የምንመለስበትን ፡ ጊዜ ፡ አላሰብነውም ። አሁን ፡ ይልቅ ፡ ቻይ ፡ ደርሰዋልን ? አላትና ፡ እናቱ ፡ ተታለለች ።

የልጅዋ ፡ አነጋገር ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ጋራ ፡ ይጫወት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሳሰባት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ትምህርቱን ፡ ሳያጠና ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ተዘግቶ ፡ ውሎ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ አይጫወትም ፡ ነበር ። ይህን ፡ ለናቱ ፡ ሊያስታውቃት ፡ አልወደደም ። እርሱ ፡ ይጫወት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ልታስብ ፡ ብቻ ፡ ነገሩን ፡ አደራጅቶ ፡ ነበር ።

በቻዩ ፣ ጠረጴዛ ፣ ላይ ፣ ሳለም ፣ እናትህን ፣ ለማታለል ፣ ስለ ፣ ፈተንህ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ውርደትና ፣ ኀጢአት ፣ ሠራህ ፣ የሚል ፣ በልጁ ፣ አሳብ ፣ ተነሣበት ።

ግድ ፣ የለም ፤ ግድ ፣ የለም ፣ ስጫወት ፣ ነበር ፣ አልሁ ፣ እንጂ ፣ ሐሰት ፣ አልተናገርሁም ፣ እያለ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ በልቡ ፣ ያወጣ ፣ ያወርድ ፣ ጀመር ። ለናትህ ፣ ስትጫወት ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ የሚያሳስብ ፣ ቃል ፣ ተናገርህ ፤ ይህም ፣ አንተ ፣ እንደምትለው ፣ ነው ፣ የሚል ፣ ድምጽ ፣ ከልቡ ፣ ሰማ ። አሁንም ፣ መልሶ ፣ እኔ ፣ ውሸት ፣ አልተናገርሁም ፣ አለ ።

አንባቢ ፣ ሆይ ፣ ምን ፣ ታስባለህ ?

ይህ ፣ ልጅ ፣ ውሸት ፣ ተናግርዋልን ? ወይስ ፣ አልተናገረም ? በእርግጥ ፣ አዎን ፣ ውሸት ፣ ተናግርዋል ፣ ትላለህ ።

የሚያታልል ፣ ቃል ፣ ብንናገር ፣ ውሸት ፣ መናገራችን ፣ ነው ፤ እውነት ፣ እያስመሰለ ፣ የሚናገረው ፣ የልጁ ፣ ውሸት ፣ እጅግ ፣ ክፉ ፣ ነው ፤ እውነት ፣ የሚመስል ፣ ውሸት ፣ ከሁሉ ፣ የባሰ ፣ ኀጢአት ፣ ነው ፤

ወዮላቸው ፣ ክፉውን ፣ መልካም ፤ መልካሙን ፣ ክፉ ፣ ለሚሉ ጨለማውን ፣ ብርሃን ፤ ብርሃኑንም ፣ ጨለማ ፣ ለሚያደርጉ ። ጣፋጩን ፣ መራራ ፤ መራራውንም ፣ ጣፋጭ ፣ ለሚያደርጉ ፣ ወዮላቸው ።

## ፩ ፥ ጢሎሽ ::

ተንጠልጥያለሁና ፣ ተመልከተኝ ፣ እይ ፣ እጆቼን ፣ እለቃለሁ ፣ እንጂ ፣ አልወድቅም ።

ሽቅቦሽ ።

ዮሐንስ ፣ አሁን ፣ ሞክር ፤ አንተ ፣ ሽቅብ ፣ ውጣ ፤ እኔ ፣ ቍልቍል ፣ እወርዳለሁ ፤ ተጠንቀቅ ፣ ወደ ፣ ላይም ፣ ስትወጣ ፣ አጥብቀህ ፣ ያዝ ።

ጢሎሽ ፣ ላይና ፣ ታች ።

በጢሎሽ ፣ ላይ ፣ መቀመጥ ፣ ትልቅ ፣ ደስ ፣ የሚያሰኝ ፣ ጨዋታ ፣ ነው ።



## ፪ ፥ ድመቲቱ በዛፍ ላይ ::

ድመቲቱ ፣ በዛፍ ፣ ላይ ፣ ወጥታ ፣ እንዳለች ፣ ተመልከት ፤ መልካሞች ፣ ድመቶች ፣ በቤት ፣ ውስጥ ፣ ይቀመጣሉ ።

አይጦችንና ፣ አይጠ ፣ መጎጦችን ፣ ይይዛሉ ። ድመቲቱ ፣ ወፎችን ፣ ለመያዝ ፣ ወደ ፣ ዛፍ ፣ ላይ ፣ ትወጣለች ፣ እየገደለችም ፣ ትበላለች ።

በጫካ ፣ የሚኖሩ ፣ እንደ ፣ አውሬ ፣ የሆኑ ፣ ድመቶች ፣ አሉ ፤ የሚበልጠውንም ፣ ጊዜ ፣ በዛፍ ፣ ላይ ፣ ይኖራሉ ።

ወፎችን ፣ እያጠቁ ፣ ቤቶቻቸውን ፣ ይቀምዋቸዋል ፤ ድመትም ከእነዚህ ፣ እንደ ፣ አንዱ ፣ ናት ።

## ፫ ፥ የወፍ ዘፈን ::

በኀጀው ፣ አቅራቢያ ፣ በዛፉ ፣ ቅርንጫፍ ፣ ላይ ፣ ተቀምጥዋልና ፣ ወፉን ፣ ተመልከተው ፤ ዘፈኑን ፣ ትሰማለህን ፣ እንዴት ፣ ያምራል ፣ ስማ ።

ቅርንጫፉ ፣ ላይ ፣ ላዩን ፣ ይወዛወዛል ፤ ወዲያና ፣ ወዲህም ፣ ይላል ። ነገር ፣ ግን ፣ ወፉ ፣ ዘፈኑን ፣ አላቋረጠም ፤ ክንፍ ፣ እንዳለው ዐውቋልና ፣ እወድቃለሁ ፣ ብሎ ፣ አልፈራም ።

ጢሎሽ ፤ ሽቅቦሽ ፤ ላይና ፣ ታች ፣ እያሉ ፣ ሰውነትን ፣ ማንቀሳቀስ ፣ ሰውን ፣ የሚጠቅም ፣ ሥራ ፣ መሆኑን ፣ ታውቀዋለኽን ?

## ስመስረቅ መጣጣር ::

አንድ ፣ ሌባ ፣ ሊሰርቅ ፣ ያንዱን ፣ ሰው ፣ ቤት ፣ መዝጊያ ፣ ሰብሮ ፣ ገባ ፤ ነገር ፣ ግን ፣ ያሰራረቁን ፣ ጊዜ ፣ ሳይመርጥና ፣ ሳያውቅ ፣ እንዲያው ፣ ሲንከረፈፍ ፣ ባለቤቱ ፣ መጣና ፣ ያዘው ።

ሌባውም ፡ እየኝ ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ አልሰረቅሁም ፣ እውነቱንም ፡ ስናገር ፡ ታየኛለህ ፡ ብሎ ፡ ተርገበገበ ፣ ባለቤቱ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ የያዝሁህ ፡ በመስረቅህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ለመስረቅ ፡ ስላሰብህ ፡ ልቀጣህ ፡ እመኛለሁ ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

አትመኝ ፡ ይላል ፣
ምኞትን ፡ መተው ፡ ይቻላልን ?

## ሸንዲት ሸስተዋይ ሸረሪት ::

ሸረሪቱ ፡ ክር ፡ ፈተለችና ፡ ካንድ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ላይ ፡ ጠምጥማ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ እስኪደርስ ፡ አንጠለጠለችው ።

ክሩን ፡ እንዲህ ፡ አድርገሽ ፡ የምትለቂው ፡ እስከዚህ ፡ ዕብድ ፡ ነሽን ፡ ብሎ ፡ የሐር ፡ ትል ፡ ሸረሪቷን ፡ ተናገራት ።

ሸረሪቷም ፡ መልሳ ፡ ዕብደትስ ፡ ነገሩን ፡ ሳያስቡ ፡ የሚናገሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ አለች ።

ነገር ፡ ግን ፡ ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፡ ክሩ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ ሲወዛወዝ ፡ በመጨረሻው ፡ በማዶ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ለሸረሪቷ ፡ መሻገሪያ ፡ ድልድይ ፡ ሆናት ።

አስተዋይቱ ፡ ሸረሪት ፡ ማን ፡ ናት ?
ልታውቃትስ ፡ ትችላለህን ?

## ሳይና ታች ::

አንድ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ እየተመለከተ ፡ አንድ ፡ ሜዳ ፡ አቋርጦ ፡ ሲሄድ ፡ ከወደላይ ፡ ድንጋይ ፡ ተወርውሮ ፡ ራሱን ፡ መታው ። ወደ ፡ መሬት ፡ እየተመለከትህ ፡ ባትሮጥ ፡ ኑሮ ፡ ድንጋይ ፡ ተወርውሮ ፡ ራስህን ፡ ባልመታህም ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ያረጀ ፡ ቁራ ፡ ተናገረው ።



የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቁራው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተናገረው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንጋጦ ፡ ሲሄድ ፡ ተሰናከለና ፡ ባንድ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ውሻ ፡ እየውና ፡ ልጂ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እኮ ፡ አንጋጠህ ፡ ባትሄድ ፡ እጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ባልገባህም ፡ ነበር ፡ አለው ።

ልጁም ፡ ከጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ተገርሞ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ተናገረ ። አሁንስ ፡ ሁሉንም ፡ አይቻለሁ ። እንግዴህስ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ እያየሁ ፡ መሄድ ፡ ይገባኛል ፡ አለ ።

የሰው ፡ አካሄድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከሰውስ ፡ መንገዱን ፡ የሚያስተውል ፡ ማነው ?

አንድ ፡ ዐይኑን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፣ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ዐይኑን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አድርጎ ፡ ማየት ፡ የሚችል ፡ እርሱ ፡ ማነው ?

## የንብና የድንጉል መፈካከር ::

እኔ ፡ካንተ ፡ ያማርሁና ፡ የበለጥሁ ፡ ነኝ ፡ አለና ፡ አንድ ፡ ድንጉል ፡ ባንድ ፡ ንብ ፡ ፈከረበት ። ንቡም ፡ ሲመልስ ፡ በርዝመትና ፡ በትልቅነት ፡ ካንተ ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ አንሳለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ካንተ ፡ ይልቅ ፡ ጠንክሬ ፡ እየሠራሁ ፣ ካንተ ፡ አብልጬ ፡ እጠቅማለሁ ። ስለ ሆነ ፡ በፍክራ ፡ ካንተ ፡ የማንስ ፡ መሆኔ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ አለ ።

በዓለም ፡ ላይ ፡ ካሉ ፡ ነገሮችሁሉ ፡ ሰነፍና ፡ ዝርክርክ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፣ እኔ ፡ ግን ፡ ጥንቁቅና ፡ ሠራተኛ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ያውቃሉ ፡ ብሎ ፡ ንብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለድንጉሉ ፡ መለሰ ።

ሰውነታችንን ፡ ለማኩራት ፡ አንደፍርም ፣ ሰውነታቸውንም ፡ ከሚያኩሩ ፡ ከነዚያ ፡ ጋራ ፡ ራሳችንን ፡ አናስተካክልም ። እርሳቸው ሰውነታቸውን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲመጥኑ ፣ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲያስተካክሉ ፡ አያስተውሉም ።

ነገር ፡ ግን ፡ የሚመካ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይመካ ፣ እግዚአብሔር ፡ ያከበረው ፡ ይከብራል ፡ እንጂ ፡ ራሱን ፡ የሚያከብር ፡ እርሱ ፡ የከበረ ፡ አይደለም ።

ትምክሕት ፡ ወዴት ፡ አለ ?

## አንበሳ ።

አንበሳ ፡ የአራዊት ፡ ንጉሥ ፡ ይባላል ። የሚያስፈራና ፡ ግርማ ፡ ያለው ፡ ኀይለኛም ፡ አውሬ ፡ ነው ። ብዙ ፡ አንበሶች ፡ የሚገኙበት ፡ ስፍራ ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ በሰፊው ፡ ሜዳና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ራቅ ፡ ብሰው ፡ ነው ። በእስያም ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አፍሪቃ ፡ አንበሶች ፡ ብርታትና ፡ ትልቅነት ፡ የላቸውም ።

አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ቀን ፡ ለቀን ፡ ሲሄዱ ፡ ይታያሉ ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አንበሳ ፡ ፀሐይ ፡ ሲጠልቅ ፡ ዋሻውን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ይሄዳል ፤ ሲራመድም ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ እያደባ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዱካው ፡ አይሰማም ፤ ፍለጋውም ፡ እንዳይታይ ፡ በጭራው ፡ እያ ጠፋው ፡ ይሄዳል ፡ ይባላል ። ጸጥ ፡ ባለ ፡ ጊዜም ፡ የሚያስፈራ ፡ ድምጹን ፡ ያሰማል ፤ በሌሊትም ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ያስደነግጣል፡ ። ወደ ፡ መንደርም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ውሾች ፡ ጩኸታቸውን ፡ ያሰማሉ ፤ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ እንሰሳት ፡ ሁሉ ፡ ድምጹን ፡ ያውቃሉና ፡ በፍርሃት ፡ ይናወጣሉ ፤ ይንበደበዳሉ ። ሰዎችም ፡ እርሱን ፡ ለማብረር ፡ ሲሻቸው ፡ ችቦ ፡ አብርተው ፡ ያወዛውዛሉ ። አንበሳው ፡ ግን ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አይቆጥረውም ። ከብት ፡ ወደሚኖርበት ፡ ስፍራ ፡ ሄዶ ፡ እንሰሶችን ፡ ይሰብራልና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሰሜን ፡ አፍሪቃ ፡ ሰዎች ፡ ከመንጎቻቸው ፡ ብዙ ፡ ያጣሉ ።

ስለሆነም ፡ አንበሳ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይመሽ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ዋሻውን ፡ ይለቃል ፤ በተራበ ፡ ጊዜም ፡ ቀን ፡ ለቀን ፡ ሜዳ ፡ ለሜዳ ፡ ሲዞር ፡ ይገኛል ። በዚያም ፡ የሜዳ ፡ አህዮችና ፡ አጋዘኖች ፡ መንጋ ፡ ሁነው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲሉ ፡ ይገኛሉ ፤ በሩቅም ፡ ሳለ ፡ ያንበሳው ፡ ጠረን ፡ ይሰማቸዋል ።

ድምጹንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በበረሃው ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ይበራሉ ።

አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በድንጋጤ ፡ ተንበርክከው ፡ አንበሳው ፡ ወደ ፡ ተሸሸገበት ፡ ይደርሳሉ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያደፍጥና ፡ ዐይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ያያቸዋል ። ወዲያውም ፡ ባንድ ፡ ዝላይ ፡ ድል ፡ ይነግቸቸዋል ።

አንበሳ ፡ ረዥም ፡ ጐፈር ፡ ያለው ፡ ዳለቻ ፡ መሳይ ፡ ነው ። እንስቲቱ ፡ አንበሳ ፡ ከተባቱ ፡ አንበሳ ፡ አነስተኛ ፡ ናትና ፡ ጐፈር ፡ የላትም ፤ መኖሪያዋንም ፡ ጽፍቅ ፡ በሆነ ፡ ዱር ፤ ወይም ፡ በደን ፡ ውስጥ ታደርጋለች ፤ በዚያም ፡ ከግልገሎቿ ፡ ጋራ ፡ ትኖራለች ፤ አንበሳዪቱ ፡ በዋሻዋ ፡ ሳለች ፡ ለሚደርስ ፡ አውሬ ፤ ወይም ፡ ሰው ፡ ወዮለት ።

አንበሳን ፡ ለምን ፡ ምሳሌ ፡ ልናደርገው ፡ ይገባናል ?



## የሜዳ አህያ ።

የሜዳ ፡ አህያ ፡ ያህዮች ፡ ወገን ፡ ከሚሆኑ ፡ እንሰሶች ፡ የሚበልጥና ፡ የሚያምር ፡ ነው ። ሰፈሩና ፡ ኑሮውም ፡ በአፍሪቃ ፡ በረሃ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ቆዳውም ፡ እንደ ፡ ከፈይ ፡ ለስላሳነት ፡ ያለው ፡ ነው ፤ ከራሱ ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍሩ ፡ ድረስ ፡ ሁለንተናው ፡ ዝንጉርጉር ፡ ነው ። ከሜዳም ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉብታ ፡ ስፍራ ፡ ይወዳል ። ደንባሪ ፡ እንሰሳ ፡ ነውና ፡ ባንዳች ፡ ነገር ፡ በደነገጠ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ይጠጋል ።

ያገር ፡ ጐብኞችም ፡ (መንገደኞች) የሚያማምሩ ፡ መንጋዎች ፡ ባንድነት ፡ ተሰብስበው ፡ ከምንጭ ፡ ውሃ ፡ ሲጠጡ ፡ በአፍሪቃ ፡ ይገኛሉ ፡ እያሉ ፡ ይናገራሉ ። በምንጩም ፡ ላይ ፡ የሚገኙበት ፡ ጊዜ ጧትና ፡ ማታ ፡ ነው ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ጥፋታቸውን ፡ ሳያስቡ ፡ በድንገት ፡ አንበሳ ፡ ይከተላቸዋል ።

የሜዳ ፡ አህዮች ፡ የጠላታቸውን ፡ መቅረብ ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ዱር ፡ ለዱር ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ይበራሉ ። ጨረቃም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ አንበሳው ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ በሩቁ ፡ ይታያልና ፡ ወደ ፡ ምንጭ ፡ አይሄዱም ፡ ይባላል ።

እርሱ ፡ ጨለማ ፡ ይወዳል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ መልካሚቱ ፡ የሜዳ ፡ አህያ ፡ ላንበሳው ፡ ምርኮው ፡ ትሆነዋለች ። ይህን ፡ የሚያምር ፡ ፍጥረት ፡ ለማዳ ፡ ለማድረግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሁኖ ፡ ተገኝቷል ። እንደ ፡ ፈረስና ፡ እንደ ፡ አህያም ፡ ሥራ ፡ ለማስያዝ ፡ አይቻልም ።

በአፍሪቃ ፡ በረሃ ፡ በየቅረብቶቹና ፡ በየተራሮቹ ፡ መላ ፡ ዘመኑን ፡ እየፋነነ ፡ በነጻነት ፡ ለመኖር ፡ የተፈጠረ ፡ ይህ ፡ የሜዳ ፡ አህያ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የሚዳን ፡ እህያ ፡ እርነት ፡ ማን ፡ አወጣው ፡ ? በበረሃስ ፡ የሚ
ዞረውን ፡ እህያ ፡ ከእስራቱ ፡ ማን ፡ ለቀቀው ?

## የአሜሪካ ነብር ::

የአሜሪካ ፡ ነብር ፡ ኑሮው ፡ ባዲሱ ፡ ዓለም ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ በደን ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ቆዳው ፡ ከመጥቆሩ ፡ በቀር ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡ ይመስላል ፣ ይህም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ አውሬ ፡ የአሜሪካ ፡ ነብር፡ ይባላል ። ከምግብም ፡ ሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚወደው ፡ የዝንጀሮ ፡ ሥጋ ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ ፈጣኖች ፡ አራዊቶች ፡ ለመያዝ ፡ ችግር ይሆንበታል ። ስለ ፡ ሆነ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ሲያንጉ ላቹ ፡ ድንገት ፡ ሳያውቁ ፡ ይደርስና ፡ በመዳፉ ፡ እየመታ ፡ ወደ ፡ መሬ ት ፡ ይጥላቸዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ የገደላቸውን ፡ ምርኮኞቹን ፡ ይበላል ።

መንገደኞቹም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በደኑ ፡ ውስጥ ፡ ሲያልፉ ፡ የነብ ርና ፡ የዝንጀሮ ፡ ውካታ ፡ ይሰማሉ ። ይህም ፡ ውካታ ፡ በዛፉ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የአራዊት ፡ አሟሟት ፡ ያመለክታል ፣ የአሜሪካ ፡ ነብር ፡ ሌላም ፡ እንስሳ ፡ እየገደለ ፡ ይበላል ።

አንድ ፡ ፈረስ ፣ ወይም ፡ አንድ ፡ አጋዘን ፡ መግደል ፡ አያውክ ውም ፣ የአሜሪካን ፡ ነብር ፡ አንዲት ፡ አውሬ ፡ ሲያባርር ፡ ወደ ፡ ውሃ፡ ውስጥ ፡ ብትገባበት ፡ ወዲያው ፡ ገብቶ ፡ አውጥቶ ፡ ይበላታል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አታመልጠውም ።

ዓሣዎችን ፡ መመገብ ፡ ስለሚወድ ፡ በውሃው ፡ ዳር ፡ ተቀምጦ ፡ ይጠባበቃቸዋል ። አንዲት ፡ ዓሣ ፡ ብቅ ፡ ስትል ፡ በመዳፉ ፡ ጠልፎ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ ይጥላታል ። ወፍም ፡ ብትሆን ፡ ሊይዛት ፡ አታውከውም ፣ ከመፍጠኑ ፡ የተነሣ ፡ ከመብረርዋ ፡ በፊት ፡ ወፉዋን ፡ ዘሎ ፡ ያንቃ ታል ።

ከነብሩ ፡ ለማምለጥ ፡
ምን ፡ ዘዴ ፡ ያስፈልጋል ?



## ፈረስ ::

ፈረስ ፡ አንድ ፡ የሚጠቅም ፡ ገራም ፡ እንስሳ ፡ ነው ፣ ሰውን ፡ ሊጠ ቅም ፡ እንጂ ፡ ሊጐዳ ፣ ወይም ፡ ሊገድል ፡ አልተፈጠረም ። ለሥ ራም ፡ ፈቃደኛና ፡ ታዛዥ ፡ ነው ። ሣር ፡ ድርቆሽ ፣ እህል ፡ ይበላል ፡ እንጂ ፡ ማናቸውንም ፡ ሕይወት ፡ ያለውን ፡ ፍጥረት ፡ አይመገብም ።

ፈረስ ፡ ጌታውን ፡ ይወዳል ፣ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ታሪክ ፡ ይተረ ካል ። ለአንድ ፡ ወታደር ፡ አንድ ፡ የታመነ ፡ ፈረስ ፡ ነበረው ፡ ያም ፡ ፈረስ ፡ ጌታው ፡ እንደ ፡ ተቀመጠበት ፡ ጊዜ ፡ አድርጎ ፡ መቼም ፡ ቢ ሆን ፡ ደስ ፡ አይለውም ፡ ነበር ፣ ጌታው ፡ በተቀመጠበት ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡ ንቃት ፡ ይንቀራጠጥ ፡ ነበር ፣ በመጨረሻ ፡ በሚያስፈራ ፡ ጦርነት ፡ ወታደሩ ፡ ከፈረሱ ፡ ወድቆ ፡ ሞተና ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋ ላ ፡ ሬሳው ፡ ሲፈለግ ፡ ይኸ ፡ የታመነ ፡ ፈረስ ፡ ባጠገቡ ፡ ተገኘ ።

ይህን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ውሃ ፡ ሳይጠጣ ፡ ሣር ፡ ሳይበላ ፡ የጌታ ውን ፡ ሬሳ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ። ባጠገቡም ፡ ቁሞ ፡ አሞራዎችን ፡ ይከላከል ፡ ነበር ፡ እስኪ ፡ ይኸ ፡ እንስሳ ፡ ባለውለታ ፡ መባል ፡ አይገባውምን ?

ከፈረስ ፡ ይልቅ ፡ ታማኝ ፡ ሊሆን ፡ የሚገባው ፡ ማን ፡ አለ ?

## ፀዋቂ ሰው ::

ተሰማ ፣ መልካም ፡ አድርጎ ፡ የሚያውቃት ፡ አንዲት ፡ ልጃገረድ ፡ ነበረችና ፡ በቤትዋ ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ስትቀመጥ ፡ አይቶ ፡ እኔ ፡ አሁኑኑ ፡ በቶሎ ፡ ፈጽሜ ፡ አንድ ፡ ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ የምሆን ፡ ይመ ስለኛል ፡ ብሎ ፡ ተናገራት ።

እርሷም ፡ መልካም ፡ ነው ፡ አንዳንዶች ፡ ልጆች ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ የሆኑ ፡ ይመስላቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልጆች ፡ ነው ፡ አለችው ።

እንደ ፡ ገናም ፡ መልሳ ፡ እንዲህ ፡ አለችው ። አንተስ ፡ አንድ ፡ ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ብትሆን ፡ ኑሮ ፡ ድንጋይ ፡ ባልወረወርኽብኝም ፣

ውሻዬንም ፡ ባላስቆጣኸውም ፣ በእግርህም ፡ ጠልፈህ ፡ ባላስናከልኸኝም ፣ ባለጌዎች ፡ ልጆች ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ አይተህም ፡ ባልሣቅህ ፡ ነበር ።

ሦስተኛም ፡ መልሳ ፡ እንዲህ ፡ አለች ። ትንሽም ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ነፍስ ፡ ያወቅህ ፡ ብትሆን ፡ ሥራህ ፡ ፈጽሞ ፡ የዐዋቂ ፡ ሰው ፡ እስኪሆን ፡ ከሰው ፡ አልቆጥርህም ። እውነተኛ ፡ ሰው ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ አይሠራም ። እውነተኛ ፡ ሰው ፡ ጀግናና ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ።

ነገሩንም ፡ ሁሉ ፡ ሳይፈራና ፡ ሳይጠራጠር ፡ በቅንነት ፡ አስተካክሎ ፡ ይሠራል ፣ ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ እንድትታስብበት ፡ ይሁን ፡ አለችው ።

ተሰማም ፡ የምትዪው ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ነውና ፡ ይሁን ፡ እሺ ፡ አስብበታለሁ ፣ እውነተኛ ፡ ሰውም ፡ እስክሆን ፡ ድረስ ፡ መልካም ፡ ልጅ ፡ ሁኖ ፡ ለማደግ ፡ እጥራለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ።

ማነው ፡ ከናንተ ፡ እስቦ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ በቁመቱ ፡ ላይ ፡ መጨመር፡ የሚችል ፡ ? በሕጻንነትህ ፡ ወራት ፡ ፈጣሪህን ፡ አስብ ።

የጭንቀትህ ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፣
ደስ ፡ አያሰኙም ፡ የምትላቸው ፡ ዓመታት ፡ ሳይደርሱ ፣

## መልካሚቱ ትንሽ ልጃገረድ ::

አንድ ፡ ቀን ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሲሄዱ ፡ ነፋሱ ፡ በጣም ፡ በርትቶ ፡ ነበርና ፡ በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ መሄድ ፡ የተሳነው ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ አገኙ ። ወዲያው ፡ የዚህን ፡ ሽማግሌ ፡ ባርኔጣ ፡ ነፋሱ ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፡ ባውራ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ጣለው ።

ሽማግሌውም ፡ ባርኔጣውን ፡ ሩጦ ፡ ማንሣት ፡ ተሳነውና ፡ ልጆቹን ፡ ጠርቶ ፡ ልጆቹ ፡ ሆይ ፣ ባርኔጣዬ ፡ ተበላሽቶ ፡ ይቀርብኛልና ፡ ቶሎ ፡ ቁማችሁ ፡ እንሡልኝ ፡ ብሎ ፡ ይጮህ ፡ ጀመረ ። ልጆቹ ፡ ግን ፡ ባርኔጣውን ፡ ነፋስ ፡ ሲያንከባልለው ፡ ማየት ፡ ማለፊያ ፡ ጨዋታ ፡ መስሎ ፡ ታያቸውና ፡ እንዲያው ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ ቁመው ፡ ብቻ ፡ ይሥቁ ፡ ነበር ።



ቀጥሎ ፡ ወደዚያው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ የምትሄድ ፡ አንዲት ፡ ልጃ ፡ ገረድ ፡ ስትመጣ ፡ ታየች ፣ እሷም ፡ ይኸን ፡ ተመልክታ ፡ እየሮጠች ፡ ሄደችና ፡ ባርኔጣውን ፡ አነሣች ፣ ሽማግሌውም ፡ ሳይነግራት ፡ ባርኔጣውን ፡ ጠራርጋ ፡ አሳምራ ፡ ሰጠችው ። እሱም ፡ ድኃ ፡ ለሆነ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ትሕትና ፡ ስለ ፡ ሠራሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥሽ ፡ ብሎ ፡ መረቀና ፡ ተቀበላት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ልጆችና ፡ ይህች ፡ ልጃገረድ ፡ ባንድነት ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ።

ይህም ፡ ሲደረግ ፡ ሳለ ፡ መምህራቸው ፡ ባንደኛው ፡ መስኮት ፡ ዘልቆ ፡ ያስተውል ፡ ኑሮ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በተማሪ ፡ ቤቱ ፡ ክፍል ፡ ያሉትን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ትምህርታቸውን ፡ እንዲያበቁ ፡ አዘዛቸው ። ቀጥሎም ፡ ስለ ፡ ሽማግሌው ፡ ባርኔጣ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ተረከላቸውና ፡ ወዲያው ፡ እንዲት ፡ ያማረች ፡ ሥዕል ፡ አንሥቶ ፡ ይህን ፡ ትሕትና ፡ ለሠራች ፡ ለዚች ፡ ልጃገረድ ፡ ሊሰጥ ፡ እስቦ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አወጣ ፡ ከመጽሐፉም ፡ ውስጥ ፡ በመጀመሪያው ፡ ስሟ ፡ ተጽፎበታል ፣ ከስሟ ፡ በታችም ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ቃል ፡ አለበት ።

ትንሽ ፡ የትሕትና ፡ ሥራ ፣
ትንሽም ፡ የፍቅር ፡ ቃሎች ፣

ይህን ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ቤት ፡ ያደርጉታል ፡ ይላል ፡ እነዚያም ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በሠሩት ፡ የስንፍና ፡ ሥራቸው ፡ አዘኑና ፡ አፈሩ ።

እንጀራህን ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ ስደድ ፣ ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ ታገኘዋለህ ።

ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ መምር ፡
ማን ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ?

## መንገደኛውና አንበሳው ::

በአፍሪቃ ፡ ደቡብ ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ ተነሥቶ ፡ ረዥም ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ ፡ ሳለ ፡ ከቤቱ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ እን

ዳለፈ ፡ ሰውዮው ፡ አንበሳውን ፡ በሩቅ ፡ ተመለከተው ። አንበሳ ውም ፡ ሰውዮውን ፡ አይቶ ፡ በቀስታ ፡ ሊከተለው ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡ ወዲያው ፡ አስተዋለ ።

መንገደኛው ፡ ፈጥኖ ፡ ሲራመድ ፡ አንበሳው ፡ እንዲሁ ፡ ይራ መዳል ፤ ሲቆምም ፡ ይቆማል ፤ እንግዲህ ፡ አንበሳው ፡ እስኪጨል ም ፡ ተከትሎ ፡ እንደማይለቀው ፡ ሰውዮው ፡ አሰበና ፡ ተረዳ ።

ስለዚህ ፡ አንበሳውን ፡ ለማታለል ፡ ሰውዮው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አሰበና ፡ ሥንጣቃ ፡ ገደል ፡ ወዳለበት ፡ ቋጥኝ ፡ ድንጋይ ፡ ተጠግቶ ፡ አንበሳው ፡ እንዳያየው ፡ ከቋጥኙ ፡ በስተኋላ ፡ ተሸሸገ ።

ከዚያም ፡ በቋጥኙ ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ የበቀለ ፡ አንድ ፡ ቅርን ጫፍ ፡ አገኘና ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ እንዲታይለት ፡ ባርኔጣውንና ፡ ኮቱን ፡ በቅርንጫፉ ፡ አንጠልጥሎ ፡ ተሸሽጎበት ፡ በነበረው ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ጨበጠ ። አንበሳውም እነዚያን ፡ ባርኔጣና ፡ ኮት ፡ አየና ፡ ወደርሳቸው ፡ እየመለገ ፡ ቀርቦ ፡ ሰውዬው ፡ መስለውት ፡ በድንገት ፡ ዘሎ ፡ ተከመረባቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰውዮው ፡ ተሸሽጎበት ፡ የነበረውን ፡ ስፍራ ፡ አልፎት ፡ ሄዶ ፡ ተወረወረና ፡ በሥንጣቃው ፡ ቋጥኝ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ተፈጠፈጠ ።

መንገደኛውም ፡ ሰውዬ ፡ ከአንበሳው ፡ ድኖ ፡ ወዲያው ፡ ሳይ ቆይ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ደረሰ ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ ይህነን ፡ ተመልከታችሁ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ጠቢባን ፤ እንደ ፡ ርግብም ፡ የዋሃን ፡ ሁኑ ።

መንገደኛው ፡ ሰው ፡ ከአንበሳው ፡ የዳነበትን ፡ ዘዴ ፡ አስተው ላችሁታልን ?

## ነብር ::

በሕንድ ፡ አገር ፡ በጣም ፡ ጠፍ ፡ የሆነ ፡ ሰፋፊ ፡ በረሃ ፡ አለ ፤ በዚ ያም ፡ የቋያ ፡ ሣርና ፡ ረጃጅም ፡ ቍጥቋጦ ፡ ይበቅልበታል ። ይኸ ውም ፡ ነብር ፡ የሚሸምቅበት ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ አድብቶ ፡ ሰዎችን ፡ ይነጥቅበታል ። ብርቱና ፡ ጨካኝ ፡ አውሬ ፡ እሱ ፡ ነው ፡



ነብር ፡ ያማረና ፡ ዝንጕርጕር ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ አለው ፤ እንዲ ዲሁም ፤ በዱር ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩ ፡ አውሬዎች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የሚያስፈራ ፡ ብርቱ ፡ ነው ። ሰዎችም ፡ ከአንበሳ ፡ ይልቅ ፡ እሱን ፡ አጥብቀው ፡ ይፈሩታል ። አንበሳ ፡ ተርቦ ፡ ሳለ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ያህል ፡ ካገኘ ፡ ይጠግባል ። ነብር ፡ ግን ፡ አይጠግብም ።

ሁልጊዜ ፡ ሰውንና ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ለማጥፋት ፡ ይጥራል ። ዘወትር ፡ የሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ የተንኰልና ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ድምጡንና ፡ ኮቴውን ፡ ሳያሰማ ፡ ለማደን ፡ ወደሚፈልገው ፡ ስፍራ ፡ ይቀርባል ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ዘሎ ፡ በፍጥነት ፡ እንስሳ ውን ፡ ለመያዝ ፡ ይችላል ። ፈረስ ፡ እንደሚሮጥ ። ሁሉ ፡ አይሮጥም ፤ ፈጥኖ ፡ ይዘላል ፡ እንጂ ፤ ወታደሮች ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡ ድንገት ፡ ቢሰፍሩ ፡ ይህ ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባ ቸዋል ። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ አንዱን ፡ ከመሃከላቸው ፡ ነጥቆ ፡ እንዲወስደው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ነብር ፡ ቀትረ ፡ ቀላልና ፡ ፈጣን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሲታደን ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወንዝ ፡ ይቀርብና ፡ ሳይቸገር ፡ ቆይቶ ፡ ለማምለጥ ፡ ይሆንለታል ። ስለዚህ ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ በዠኖንና ፡ በውሾች ፡ ይታደናል ።

ነብር ፡ በእስያ ፤ በኤሮጳ ፡ በአፍሪካም ፡ አለ ። ግን ፡ ዐይነቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ።

## በመጨረሻ የቁጣ ቃል ::

አንዲት ፡ ልጃገረድ ፡ የወዳጅዋን ፡ ሞት ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ እንባ ፡ እያነቃት ፡ ዋይ ፡ ብላ ፡ ሙሾችና ፡ ያንለታ ፡ ያየኋት ፡ ጊዜ ፡ የመጨ ረሻ ፡ ጊዜዋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐውቄ ፡ ቢሆን ፡ ወዳጄን ፡ በተሰናበት ኋት ፡ ነበር ፡ ብላ ፡ አዘነች ።

እንዲህ ፡ ማለቷ ፡ ፊት ፡ ባንድነት ፡ ሳሉ ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ ተናግራ ፡ አሳዝናት ፡ ነበርና ፡ ያ ፡ ቍጣ ፡ በልቧ ፡ ውስጥ ፡ እንዳንድ ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ ሁኖ ፡ ይኖር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ። ይህም ፡ ስለ ፡ ርኅ ራሄ ፡ መልካም ፡ አገባብ ፡ ያመለክተናል ።

ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ የምትናገረው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያነጋገር ፡ ፍጻሜ ፤ እንዲሆንልህ ፡ አስበህ ፡ ከአባትህ ፤ ወይም ፡ ከናትህ ፤ ከወንድምህ ፡ ወይም ፡ ከእኅትህ ፡ ከጎረቤትህ ፡ ከሌላም ፡ ካንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በፍቅርና ፡ በርኅራኄ ፡ ተነጋገር ፤ ቍጣ ፡ ቀይቶ ፡ ቢያስቡት ፡ ያሳዝናል ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ሌላውን ፡ ሳትጕዱ ፤
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተዋደዱ ።
ወንድምህ ፡ ቢቆጣ ፡ ክፉ ፡ ቢናገርህ ፤
አንዳች ፡ እንዳትመልስ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ አደራህ ።

በወንድሙ ፡ ላይ ፡ በከንቱ ፡ የተቆጣ ፡ በፍርድ ፡ ይፈረድበታል።

የተወደዳችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፤ የሰው ፡ ቍጣ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ አያሠራምና ፤ ከናንተ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለመስማት ፡ የፈጠነ ፤ ለመናገርና ፡ ለቍጣ ፡ የዘገየ ፡ ይሁን ።

## ዳቦ ጋጋሪና እንጨት ሸመሳሳሽ ።

አንድ ፡ ዕንጨት ፡ አመላላሽ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ዳቦ ፡ ጋጋሪ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሳለ ፡ ጋጋሪው ፡ ከዳቦ ፡ ገገር ፡ ገንዘቡን ፡ እቀበላለሁ ፡ ሲል ፡ ሌባ ፡ በጐን ፡ መጣና ፡ አንድ ፡ ዳቦ ፡ ሰርቆ ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ይህም ፡ ዕንጨት ፡ አመላላሽ ፡ ሰውዬ ፡ ሌባውን ፡ ይመለከተው ፡ ኑሮ ፡ ሩጦ ፡ ሂዶ ፡ ጕሮሮውን ፡ አንቆ ፡ ያዘና ፡ ዳቦውን ፡ ከሌባው ፡ አስጣለው ።

ዳቦ ፡ ጋጋሪውም ፡ ሰውዬ ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ ነበርና ፡ በማግሥቱ ፡ ያነን ፡ ዕንጨት ፡ አመላላሽ ፡ ሰው ፡ አግኝቶ ፡ ትላንትና ፡ ከሌባው ፡ ያስጣልኸውን ፡ ዳቦዬን ፡ ወዴት ፡ አደረስኸው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ በላሁት ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ዳቦ ፡ ጋጋሪውም ፡ እንግዲያማ ፡ ዳቦዬን ፡ ከበላህ ፡ የዳቦዬን ፡ ዋጋ ፡ አትሰጠኝምን ፡ ብሎ ፡ ቢቆጣጠረው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ እሰጣለሁ ፡ ሌባውን ፡ ተከትዬ ፡ እስክደክም ፡ ሩጬ ፡ ዳቦውን ፡ ከሌባው ፡ ያስጣልሁበት ፡ የድካሜ ፡ ዋጋ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ አለው ።



ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ዳቦ ፡ ጋጋሪ ፡ በነገሩ ፡ ተደንቆ ፡ ትላንትና ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ ሰንት ፡ ወንበዴዎች ፡ ኑረውብኝ ፡ ኑሯል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ይባላል ።

ከዳቦ ፡ ጋጋሪውና ፡ ከዕንጨት ፡ አመላላሹ ፡
ማናቸውን ፡ አከብረህ ፡ ታያለኽ ፡

## ልጆችና እንቁራሪቶች ።

አንድ ፡ ቀን ፡ በኩሬው ፡ አጠገብ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ሲመለከቱ ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ እንቁራሪቶችን ፡ አዩ ። ታላቁም ፡ ልጅ ፡ እንግዲህ ፡ በእንቁራሪቶቹ ፡ ልጫወትባቸው ፡ አለና ፡ ደንጊያውን ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪቶቹ ፡ ወረወረው ።

ታናሹ ፡ ግን ፡ ደንጊያ ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪቶቹ ፡ መወርወርና ፡ እነሱን ፡ መጉዳት ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ገሠጸው ። እንቁራሪቶቹ ፡ የሚናገሩ ፡ ቢሆኑ ፡ ምን ፡ ይሉ ፡ ኑሮ ፡ ይሆን ፡ ? ምናልባት ፡ ደንጊያ ፡ መወርወር ፡ ለናንተ ፡ ጨዋታ ፡ ይመስላችኋል ። ደንጊያ ፡ ይጐዳልና ፡ ለኛ ፡ ግን ፡ ጨዋታ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ ለልጆቹ ፡ ይመልሱላቸው ፡ ነበር ።

እንቁራሪቶችን ፤ በራሪዎች ፡ ወፎችንና ፡ ተንቀሳቃሾችን ፡ ሁሉ ፡ መጉዳት ፡ አይገባም ። እሊህ ፡ አይናገሩምና ፡ በተጐዱ ፡ ጊዜ ፡ አንዳች ፡ ሊመልሱ ፡ አይችሉም ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ።

ለእንስሳ ፡ ሁሉ ፡ ርኅሩኃን ፡ ሁኑ ። የሚራሩም ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ። ምሕረት ፡ ያገኛሉና ፤ ለእንስሳ ፡ ነፍስ ፡ የሚራራ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ነው ።

የዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድነው ፡ ?
እፍታተህ ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህን ፡ ?

## ፀሐይ ።

ፀሐይ ፡ ክብና ፡ ሁለንተናው ፡ ነበልባላዊ ፡ የሆነ ፡ ብርሃንና ፡ ሙቀት ፡ የሚሰጥ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚጠቅምና ፡ አታክልትንም ፡ ሁሉ ፡ የሚያበስል ፡ ነው ። እርሱም ፡ ከምድርና ፡ ከጨረቃ ፡ በጣም ፡ ይርቃል ።

ፀሐዩ ፡ ቆሞ ፡ ሳለ ፡ ምድሩ ፡ እየተሽከረከረ ፡ ቀኑንና ፡ ሌሊቱን ፡ በሐያ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይዞራል ፣ ምድርም ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡ በተመለሰች ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይ ፡ እንዴት ፡ አደራችሁ ፡ ነግቷልና ፡ ተነሡ ፡ ይለናል ። ምድርም ፡ ዳግመኛ ፡ ከፀሐይ ፡ በዞረች ፡ ጊዜ ፡ ጭልምልም ፡ ይላል ። ፀሐዩም ፡ ደኅና ፡ እደሩ ፣ ለመኝታም ፡ ጊዜ ፡ ተፈቅዷል ፡ ብሎ ፡ ይሄዳል ።

ጥያቄ ፣ ፀሐዩን ፡ ማን ፡ ፈጠረው ? እግዚአብሔር ፡ ፈጠረው ። በስፍራውም ፡ አኖረው ። ፀሐይም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ያደርጋል ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘንን ፡ ማድረግ ፡ ይገባናል ።

አቤቱ ፣ ሥራኸ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ? ሁሉን ፡ በጥበብ አደረግኸ ። ምድርም ፡ በባለጸግነትህ ፡ መላች ።

## ወደ ባለእጅ ቤት መሄድ ።

ወደ ፡ ባለእጅ ፡ ቤት ፡ እንሂድና ፡ እንይ ፣ ምን ፡ ይሠራ ፡ ይሆን ? ብረቱን ፡ እንዲያግል ፡ በወናፎቹ ፡ እሳቱን ፡ ያናፋል ። አሁን ፡ ብረቱን ፡ በጉጠት ፡ አውጥቶ ፡ በመስፉ ፡ ላይ ፡ ያኖረዋል ። በመዶሻም ፡ ይመታዋል ፣ እንዴት ፡ ጠንክሮ ፡ ይሠራል ፣ ጠለሸቱም ፡ ይበራል ፣ ፍንጣቂዎቹም ፡ ፍንጥቅጥቅ ፡ ይላሉ ።

ባለእጁ ፡ ምን ፡ ያበጃል ፣ ምስማርና ፡ የፈረስ ፡ ሚስማ ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ይሠራል ። ምስማሩና ፡ የፈረሱ ፡ ሚስማ ፡ የተሠሩት ፡ ከምንድን ፡ ነው ? እነሱ ፡ የተሠሩት ፡ ከብረት ፡ ነው ። ብረት ፡ ለኛ ፡ ብዙ ፡ የሚጠቅመን ፡ ነው ።

ማረሻ ፡ መንኰራኩር ፡ መርከብ ፡ በወላፈን ፡ የሚሄድ ፡ መኪና ሌላም ፡ ሁሉ ፡ ዐይነት ፡ ይሠራበታል ። ያለ ፡ ብረት ፡ ምንም ፡ ልንሠራ ፡ አይሆንልንም ።

ባሕረ ፡ ወጥ ፡ ብረት ፡ እጅግ ፡ ብሩህና ፡ ስለታም ፡ ብርቱም ፡ ነው ። ቢላዋና ፡ መቀስ ፡ ሁሉ ፡ ከባሕረ ፡ ወጥ ፡ ብረት ፡ ይሠራል ።

ሰው ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ማረሻ ፡ ሊሠራ ፡ ይችላልን ?

ወይስ ፡ ወደ ፡ ባለእጅ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ ይገባዋልን ?

## አንድ ልጅና የሚበላ ፍሬ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ቅርጫት ፡ ሙሉ ፡ ፍሬ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ሲሄድ ፡ ሳለ ፣ ከፍሬው ፡ ሦስት ፣ ወይም ፡ አራት ፡ ያህል ፡ ተንጠባጥቦ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። ሰውዬውም ፡ ፍሬው ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ አላወቀም ፡ ኑሯል ። አንድ ፡ ምስኪን ፡ ብላቴና ፡ ግን ፡ ፍሬዎቹ ፡ ሲወድቁ ፡ አያቸውና ፡ ለቀማቸው ፣ ወዲያውም ፡ ይኸው ፡ ይኸው ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ሰውዬው ፡ ሮጦ ። ሰውዬውም ፡ የልጁን ፡ ጩኸት ፡ ሰምቶ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ ልጁ ፡ ፍሬዎቹን ፡ አምጥቶ ፡ በሰውዬው ፡ እጅ ፡ ጣለለት ።

ሰውዬውም ፡ ፍሬውን ፡ ተቀበለና ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥህ ፡ ብሎ ፡ ቅርጫቱን ፡ ከመሬት ፡ አሳረፈና ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ የታመንህ ልጅ ፡ ነህ ። የሚሻልህንም ፡ መርጠህ ፡ አንዱን ፡ ለራስህ ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

ሰውዮው ፡ ግን ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ጐበዝ ፡ መጣና ፡ ልጁን እንዲህ ፡ አለው ። የወደቀውን ፡ ሁሉ ፡ ለራስህ ፡ አስቀርተህ ፡ ቢሆን ለኔም ፡ ጥቂት ፡ ታተርፍልኝ ፡ ነበር ።

ልጁ ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ አይገባም ፡ ልሰጥህ ፡ የሚ የሚገባኝን ፡ ውሰድ ፡ እንጂ ፡ ለኔ ፡ ያልሆነውን ፡ ብሰጥህ ፡ ሌባ ፡ መሆኔ ፡ አይደለምን ? ድኃም ፡ እንኳ ፡ ብሆን ፡ በመልካሙ ፡ ስሜ ፡ ብኰራ ፡ ይሻለኛል ። ስሜንም ፡ ከማጥፋት ፡ ድኃ ፡ ሁኜ ፡ እመካ

ለሁ ፡ አለ ። ከመልካም ፡ ሽቱ ፡ መልካም ፡ ስም ፡ ይሻላል ።

ማንም ፡ ትምክሕቴን ፡ ሲያበላሸው ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል ።
ስሙንና ፡ ትምክሕቱን ፡ ሊጠብቅ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ምን ፡
ማድረግ ፡ ይገባዋል ?

## ማመልከቻ ::

ለድጉ ፡ አዳሪዎች ፡ የሚጠቅም ፡ ቻይ ፡ ወይም ፡ ቻሂ ፡ የሚባል ፡ መጠጥ ፡ ካንድ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፡ ቅጠል ፡ ተለቅሞ ፡ ይደራጃል ፤ ማር ፡ ከንብ ፡ ይሠራል ።

ቅቤ ፡ ከላም ፡ ወተት ፡ ተንጦ ፡ ይወጣል ።

የቱፋህ ፡ ጭማቂ ፡ የዕንጨቱን ፡ መልክ ፡ ያሳምራል ። ከወይን ዘለላ ፡ ጭማቂ ፡ ቀይና ፡ ነጭ ፡ መጠጥ ፡ ይወጣል ።

ቡሽ ፡ ሼን ፡ የሚባል ፡ ያንድ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ቅርፊት ፡ ነው ፡
ሰፍነግ ፡ እንደ ፡ ተክል ፡ የጥልቅ ፡ ጥልቅ ፡ ከሆነ ፡ ባሕር ፡
ይበቅላል ።

ዘይት ፡ ከዓሣና ፡ ከተልባ ፡ ከሌላም ፡ ዐይነት ፡ ተክል ፡ ይወጣል ።

ሻማ ፡ ከሞራና ፡ ከሰም ፡ ይሠራል ።
ልብስ ፡ ከተልባ ፡ እግር ፡ ጭረት ፡ ይሠራል ።
ወረቀት ፡ ከዕንጨት ፡ ከሣርና ፡ ከጨርቅ ፡ ይሠራል ።
የሱፍ ፡ ፈትል ፡ ከለስላሳና ፡ ከሙቀታም ፡ ጠጉር ፡ ይሠ
ራል ።
ሐር ፡ በትል ፡ ተፈትሎ ፡ ይደራጃል ።
ሰው ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡
የሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ምንድን ፡ ነው ?
አታጥፉ ፡ አትሻ ፡ አታባክን ።

ብዙ ፡ ራብተኞች ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ስጦታ ፡ ያስቡታልና ፡ ልበ ላው ፡ የማልፈቅደውን ፡ በወለሉ ፡ መወርወር ፡ አይገባኝም ።

በፈቃድ ፡ መበተን ፡ ተቸግሮ ፡ መሻትን ፡ ያመጣል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከወረወርሁት ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ ማግኘት ፡ እንዴት ፡ እመ ኛለሁ ።



## ሦስት አታላዮች ::

ብራህማን ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ የሕንድ ፡ ካህን ፡ ከገበያ ፡ ፍየል ፡ ገዛና ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ አታላዮቹ ፡ አይተው ፡ ሰውዬ ውን ፡ አታለው ፡ ፍየሉን ፡ ሊወስዱ ፡ አሰቡ ።

እርሳቸውም ፡ ወዴት ፡ እንዲሄድ ፡ አስተውለው ፡ በየራሳቸው እልፍ ፡ እልፍ ፡ እያሉ ፡ ተቀመጡ ። ይህም ፡ ብራህማን ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ርኩስ ፡ እንሰሳ ፡ እንዳይነካ ፡ የታወቀ ፡ ልማድ ፡ ነበርና ፡ ስለ ዚህ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያው ፡ አታላይ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ርኩስ ፡ ውሻ ፡ በጫንቃህ ፡ ተሸክመህ ፡ የምትሄድ ፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየ ቀው ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ እንደ ፡ ብራህማን ፡ ያለ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ርኩሱን ፡ እንሰሳ ፡ ቢነካ ፡ ይረከሳልና ፡ ስለዚህ ፡ ነበር ።

ብራህማን ፡ ግን ፡ ፍየል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ውሻ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ጥቂትም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ሁለተኛው ፡ አታላይ ፡ ደግሞ ፡ አገኘውና ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ሁሉ ፡ ውሻ ፡ ተሸ ክመህ ፡ መሄድህ ፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ አለና ፡ ጠየቀው ።

ብራህማንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ፍየሉን ፡ ከትከሻው ፡ አወረደና ፡ እያገላበጠ ፡ ያይ ፡ ይመረምር ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ ያው ፡ ፍየል ፡ እንጂ ፡ ውሻ ፡ እንዳልሆነ ፡ ተረዳና ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መንገዱን ፡ ይጓዝ ፡ ጀመረ ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሦስተኛው ፡ አታላይ ፡ ወዳለበት ፡ ብራህማን ፡ ፍየሉን ፡ እንደ ፡ ተሸከመ ፡ ቢደርስ ፡ እነዚያው ፡ ሁለቱ ፡ አታላዮ ች ፡ እንደ ፡ ጠየቁት ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቀው ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ብራህማን ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ መሰለውና ፡ ፍየሉን ፡ ከትከሻው ፡ አውርዶ ፡ ጣለው ። ርኩሱንም ፡ እንሰሳ ፡ የተሸከመበትን ፡ ትከሻ ውን ፡ ሊያጥብና ፡ ሊያነጻ ፡ ሄደ ።

እነዚህም ፡ አታላዮች ፡ ፍየሉን ፡ ወሰዱና ፡ ብራህማን ፡ ባደ ረገው ፡ ሞኝነት ፡ እየሣቁና ፡ እየዘበቱ ፡ ጊዜያቸውን ፡ አሳለፉ ።

በባልንጀራህ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ አታድርግ ። በምንም ፡ በምን ፡ አትበላለጠው ። በማናቸውም ፡ የግድ ፡ አትበለው ።

ይህ ፡ ትምህርት ፡ ለምን ፡ ይጠቅማል ?

## የምድር ማዕድኖች ፡፡

ማዕድኖች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያው ፡ ንጥረው ፡ ይገኛሉ ። ሌላም ፡ ጊዜ ፡ ከአፈር ፡ ወይም ፡ ከድንጋይ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ማዕድን ፡ ጋራ ፡ ተደባልቀው ፡ ይገኛሉ ። ከነዚህም ፡ የሚለዩት ፡ በማጠብ ፡ በመውቀጥ ፡ በማቃጠል ፡ ነው ።

ወርቅ ፡ ብሩህና ፡ ብጫ ፣ ከባድና ፡ ለስላሳ ፡ ነው ። በአውስትሬያሊያ ፡ በአፍሪቃና ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ በብዙ ፡ ይገኛል ።

ወርቅ ፡ የሚገኝበት ፡ አውራጃ ፣ የወርቅ ፡ ማውጫ ፡ ይባላል ፡ አብዛኙ ፡ ጥቃቅን ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እየተድበለበለ ፡ ይወጣል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ክር ፡ በቀጭኑ ፡ ረዝሮም ፡ ሁኖ ፡ ይገኛል ።

ወርቅ ፡ ወንዝ ፡ ለወንዝ ፡ በአሸዋ ፡ ላይ ፡ ተመልቶ ፡ ይገኛል ።

የወርቅ ፡ ዋጋው ፡ ከማዕድናት ፡ ሁሉ ፡ ይበዛል ። ይልቁንም ፡ ጌጥና ፡ ገንዘብ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራል ። ቀለበት ፣ ድሪ ፣ ጉትቻ ፣ ጽዋ ፣ አምባር ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከወርቅ ፡ ይሠራል ።

ብር ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ አይደለም ፡ እንጂ ፡ ብሩህና ፡ ከባድ ፡ ነው ። በአሜሪካ ፡ በብዙ ፡ ይገኛል ። ዋጋውም ፡ ከወርቅ ፡ ቀጥሎ ፡ ይገመታል ። ጌጥና ፡ ገንዘብ ፡ እየሆነም ፡ ይሠራል ። በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ገንዘባችን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ነው ። ብር ፡ አንድ ፡ አላድ ፣ አንድ ፡ ሩብ ፡ መሐለቅ ፡ እየሆነ ፡ ይሠራል ። ቤሳ ፡ ግን ፡ ከነሐስ ፡ ነው ።

ደግሞ ፡ ወለባ ፡ ጉትቻ ፡ ቀለበት ፣ ድሪ ፣ ሰንሰለት ፣ የሰንጢ ፡ እጀታ ፣ ሹካ ፣ ማንካ ፣ ጉብጉብ ፣ የፈረስ ፡ ቤንቻ ፣ ቢተዋ ፣ አምባር ፡ ማልድያ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከብር ፡ ይሠራል ።

እርሳስ ፡ መልኩ ፡ ደበስ ፡ ያለ ፡ ብልጭልጭታ ፡ ያለው ፡ ከማዕድናቱ ፡ ሁሉ ፡ የለሰለሰ ፡ ነው ። በእንግሊዝ ፡ ደሴቶች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ክፍል ፡ በዓለምም ፡ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ ይገኛል ። እርሳስ ፡ ከማዕድናቱ ፡ የተለመደና ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እጅግ ፡ ለስላሳ ፡ በመሆኑ ፡ እንዳደረጉት ፡ ሆኖ ፡ ለመሥራት ፡ ይመቻል ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለቤት ፡ ክዳን ፡ ይጠቅማል ። ለውሃ ፡ ፓምፕና ፡ ለበርሜልም ፡ ይሆናል ።



ብረት ፡ ጠቆር ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ ነው ። ብርቱና ፡ ተሰባሪ ፡ ነው ። ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ይወጣል ። ብረት ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያለው የታወቀ ፡ ማዕድን ፡ ለንግድ ፡ ሁሉ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ።

መርከቦች ፣ መኪና ፣ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፣ የሠረገላ ፡ ዐይነት ፡ ሁሉ ፡ ትልቅ ፡ ሆነ ፡ ትንሽ ፡ ሲሠራ ፡ ብረት ፡ ያስፈልገዋል ።

ከወርቅና ፡ ከብር ፡ ገንዘባችንን ፡ እንሠራለን ። ዕዳችንንም ፡ እንከፍላለን ፣ ሰውነታችንን ፡ እናስጌጣለን ።

ከብረት ፡ መሣሪያችንን ፡ እንሠራለን ። ስለ ፡ ሀገራችንም ፡ እንመከትበታለን ፣ ብዙ ፡ የችግራችንንም ፡ ቀዳዳ ፡ እንደፍንበታለን ።

ብረት ፣ ወርቅና ፡ ብር ፡ እንደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡
በኢትዮጵያም ፡ ይገኝ ፡ ይመስልሀልን ?
ያለበትን ፡ ስፍራ ፡ ለማወቅ ፡ ትችላለህን ?

## ዕውር ፡፡

በምድር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚለምነውን ፡ ሰው ፡ ታያለህን ? እሱ ፡ ዕውር ፡ ነውና ፡ አያይህም ። እስኪ ፡ እየው ፣ እንዴት ፡ እንደ ፡ ታወረ ፡ ብንጠይቀው ፡ ዕውር ፡ ሁኜ ፡ ተወለድሁ ፡ ይለናል ፡ እንጂ ፡ ማናቸውንም ፡ ማየት ፡ አይችልም ። ያባቱን ፡ ወይም ፡ የናቱን ፡ የወንድሞቹን ፡ ወይም ፡ የእኅቶቹን ፡ ፊት ፡ ከቶ ፡ አይቶ ፡ አያውቅም ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ የሚያምሩትንም ፡ አበቦች ፡ አላየም ። ለርሱ ፡ ሁል ጊዜ ፡ ጨለማ ፡ ነው ። ዕውር ፡ ሁኖ ፡ የሚወለድ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ አያሳዝንምን ?

አንድ ፡ ቀን ፡ ባንድ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ዐይነ ፡ ስውር ፡ በመንገድ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲለምን ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ የሚመኘው ፡ ምኞት ፡ ነበረው ። ይኸውም ፡ ዐይኑ ፡ እንዲበራለት ፡ ነው ፣ ያ ፡ ታላቅ ፡ መምህር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባጠገቡ ፡ ሲያልፍ ፡ ሰምቶ ፡ ወዲያው ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እያለ ፡ ይጮህ ፡ ጀመረ ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ቀረበና ፡ ምን ፡ እንዳደርግልህ ፡ ትወዳለህ ፡ ብሎ ፡ በርኅራኄ ፡ ቢጠይቀው ፣ ጌታ ፡

ሆይ ! እይ ፣ ዘንድ ፣ ነዋ ፣ ብሎ ፣ ዕውሩ ፣ መለሰለት ።

ድውይ ፣ የመፈወስ ፣ ኀይል ፣ ያለው ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስም ፣ ሃይማኖት ፣ አለህና ፣ እይ ፣ ብሎ ፣ በዚያው ፣ ጊዜ ፣ ፈወሰው ። ዕውሩም ፣ ፈጥኖ ፣ ዳነ ፣ ለማየትም ፣ ቻለ ።

ዕውርነትን ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ እንደ ፣ ተላከ ፣ መርገም አድርገን ፣ እንየው ። ብዙዎች ፣ ይህን ፣ አስበው ፣ ለዕውሮች ፣ አይ ራሩም ፤ ዕውር ፣ የሚያደርግ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ አለና ፣ ሐኪሞች ፣ በብዙ ፣ ነገር ፣ ዕውሮች ፣ እንዲያዩ ፣ ያደርጋሉ ።

ሰው ፣ ከታወረ ፣ በኋላ ፣ ደስ ፣ አያሰኝም ። ደግሞ ፣ አይጠቅምም ። አንዳንዶቹ ፣ ግን ፣ ብልሆች ፣ ይሆኑና ፣ ይተጋገዛሉ ።

አንዳንዶችም ፣ ያለ ፣ መሪ ፣ ካንዱ ፣ ቤት ፣ ወደ ፣ ሌላ ፣ ሊሄዱ ፣ ይችላሉ ። ዕውር ፣ በጣቱ ፣ እየቆጠረ ፣ ሊያነባቸው ፣ የሚችልባቸው ፣ ነጥብ ፣ ነጥብ ፣ ያላቸው ፣ መጻሕፍት ፣ አሉ ። አያሌም ፣ ዕውሮች ፣ ደኅና ፣ አድርገው ፣ ይማሩና ፣ እንደሚያዩ ፣ ሰዎች ፣ ሁሉ ፣ ፈተናውን ፣ ለማለፍ ፣ ይችላሉ ። ዕውር ፣ ምንጣፍና ፣ ሌላም ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ እንደሚጠቅም ፣ አድርጎ ፣ ለመሥራት ፣ ይችላል ። እግዚአብሔር ፣ ዕውሮችን ፣ ይጠብቃቸዋልና ፣ በርኅራኄ ፣ እንዘንላቸው ። ደግሞም ፣ ኑሯቸውን ፣ እንዲያሻሽሉ ፤ በልመናም ፣ እንዳይኖሩ ፣ እንርዳቸው ፤ እናስተምራቸው ።

እግዚአብሔር ፣ የዕውሮችን ፣ ዐይን ፣ ይከፍታል ። ለችግረኛው የሚያስብ ፣ ብፁዕ ፣ ነው ። እግዚአብሔር ፣ በክፉ ፣ ቀን ፣ ያድነዋል ።

ለዕውሮች ፣ ምን ፣ ልናደርግላቸው ፣ ይገባል ?



## ሦስት የሊቀ መኳስ ልጆች ::

አንድ ፣ ባለጸጋ ፣ የእንግሊዝ ፣ ሊቀ ፣ መኳስ ፣ ሊሞት ፣ ባልጋ ፣ ላይ ፣ ሁኖ ፣ ሲያጣጥር ፣ ሦስቱን ፣ ወንዶች ፣ ልጆቹን ፣ እንዲመጡና ፣ እንዲናዘዝላቸው ፣ አስጠራቸው ። ከዚህ ፣ ወዲህ ፣ እነሱ ፣ እንደመጡ ፣ ከዚህ ፣ በታች ፣ የተሰጠውን ፣ ጥያቄ ፣ እያንዳንዳቸው ፣ እንዲመልሱ ፣ ነገራቸው ። ልጆቼ ። ሆይ ፣ ወፍ ፣ ለመሆን ፣ የሚቻል ፣ ቢሆንና ፣ ፈቃድ ፣ ቢኖራችሁ ፣ ከወፎች ፣ ማናቸውን ፣ ዐይነት ፣ ወፍ ፣ ለመሆን ፣ ትወዱ ፣ ነበር ? አላቸው ፤ ከነሱ ፣ መሀከል ፣ ታላቁ ፣ ልጁ ፣ ተነሣና ፣ እኔ ፣ በቅሚያ ፣ የምትኖረውን ፣ ጭልፊን ፣ ለመሆን ፣ እወዳለሁ ፣ ሲል ፣ መለሰ ።

ሁለተኛው ፣ ልጅ ፣ እኔ ፣ ግን ፣ ሽመላ ፣ የምትባለውን ፣ ወፍ ፣ ለመሆን ፣ እወዳለሁ ፣ ከባልንጀሮቿ ፣ ጋራ ፣ በማኅበር ፣ አንድነት ፣ ሁና ፣ ትበርራለችና ፣ አለ ።

ሦስተኛው ፣ ትንሹ ፣ ልጅ ፣ ሲመልስ ፣ እኔ ፣ ዝዬ ፣ ለመሆን ፣ እወዳለሁ ፣ ረገርም ፣ አንገት ፣ አላትና ፤ አንዳች ፣ ነገር ፣ ለመናገር ፣ ባሰብሁኝ ፣ ጊዜ ፣ መልስ ፣ ለመስጠት ፣ ከአሳቤ ፣ እስካወጣውና ፣ ይህን ፣ ረዥሙን ፣ አንገት ፣ እስኪያልፍ ፣ ድረስ ፣ ብዙ ፣ ጊዜያት ፣ አገኛለሁ ፣ አለ ።

ከዚህ ፣ ወዲህ ፣ አባታቸው ፣ ይህነን ፣ ሁሉ ፣ መልስ ፣ ከሰማ ፣ በኋላ ፣ ለታላቁ ፣ ልጁ ፣ ይህነን ፣ በጭልፊነት ፣ መኖር ፣ የተመኘኸውን ፣ ምኞትህን ፣ እንደምመለከተው ፣ ከእንግሊዝ ፣ አገር ፣ ያለውን ፣ ርስቴን ፣ ሁሉ ፣ አወርሽሃለሁ ፣ የሰላምና ፣ የሐቀኝነት ፣ ሥራ ፣ ያለበት ፣ አገር ፣ ነውና ፣ በሸፍጥ ፣ ለመቀመጥ ፣ አይመችህም ፣ አለው ።

ሁለተኛውን ፣ ልጁን ፣ ሲለው ፣ በማኅበር ፣ ለመኖር ፣ ስለ ፣ ወደድኸ ፣ በዌልስ ፣ አገር ፣ ያለኝን ፣ ርስቴን ፣ አወርሽሃለሁ ። ስምምነት ፣ የሌለበትና ፣ የጦር ፣ አገር ፣ ነውና ፤ በዚያውም ፣ የሚኖሩ ፣ አውሬዎች ፣ ቂማቸውን ፣ ወደኛ ፣ ሲያመጡብን ፣ ታበርድልናለህ ፣ አለው ።

ከዚህ ፣ ወዲህ ፣ ሦስተኛውን ፣ ልጁን ፣ ላንተ ፣ የዓለም ፣ ነገር ፣ ከቶ ፣ አላወርስህም ፣ አንተ ፣ ብልህና ፣ ጥንቁቅ ፣ ነህና ፣ የሚበቃህን ፣ በጥበብህ ፣ መልካም ፣ አድርገህ ፣ ልታገኝ ፣ ትችላለህ ፣ አለው ።

ይህም ፣ ታናሹ ፣ ልጁ ፣ ጥቅም ፣ ባለው ፣ ጥበቡ ፣ አስቀድሞ ፣ እንደ ፣ ተናገረ ፣ ለእንግሊዝ ፣ አገር ፣ ዋና ፣ የፍርድ ፣ ፈራጅ ፣ ምክትል ፣ ሆኖ ፣ ወዲያውም ፣ ከንጉሡ ፣ በታች ፣ ቢትወደድ ፣ ተብሎ ፣ እንደራሴነትን ፣ ተሹሞ ፣ ተከብሮ ፣ ይኖር ፣ ነበር ፣ ይባላል ።

አንተሳ ፣ ከነዚህ ፣ ከሦስቱ ፣ ልጆች ፣ ማናቸውን ፣ ልትመርጥ ፡ የትኛውንስ ፣ ልትሆን ፣ ትወዳለህ ?

## የሦስት ክፍል መንግሥት ፍጥረቶች ::

የፕሩሲያ ፡ ንጉሥ ፡ ፍሬድሪክ ፡ ዊልያም ፡ በግዛቱ ፡ ሀገሮች ፡ ውስጥ ፡ ለመናፈስ ፡ ሲሄድ ፡ ሳለ ፡ ወዳንድ ፡ ወደ ፡ ተዋበች ፡ መንደር ፡ ደርሶ ፡ በዚያውም ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ቆየ ። በዚያውም ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ንጉሣቸውን ፡ ለማየት ፡ በጣም ፡ ናፍቆት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጡልን ፡ ሲሉ ፡ አንዳችም ፡ የመቀበያ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ሊሰጡትም ፡ አደራጅተው ፡ ቆዩት ።

በዚያም ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ተማሪዎች ፡ ስለ ፡ ደስታ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ መልካም ፡ ሽታ ፡ የሚሸቱ ፡ አበባዎች ፡ በተኑ ። ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ አንዲቱ ፡ ልጃገረድ ፡ ተማሪ ፡ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ ጐበኙን ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ደስታችን ፡ መቀበያ ፡ ሰትል ፡ ግጥም ፡ ከልቧ ፡ ፈልስፋ ፡ አውጥታ ፡ መልካም ፡ ግጥም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆማ ፡ አዜመች ። ንጉሡም ፡ በጸጥታ ፡ አዳመጣትና ፡ እንደዚህ ፡ ሥራዋን ፡ በማከናወኗ ፡ አመሰገናት ።

ከዚያም ፡ በላይ ፡ የትምህርታቸውን ፡ አጠናን ፡ ሊመረምር ፡ አንዳች ፡ ጥያቄ ፡ አደረገ ። በንጉሡም ፡ አጠገብ ፡ ባለ ፡ ባንድ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ንጉሡን ፡ ሲቀበሉ ፡ በጨዋታ ፡ ላሸነፈ ፡ እንዲሰጡ ፡ የተሰናዱ ፡ በኸረ ፡ ሎሚዎች ፡ ነበሩ ። ንጉሡ ፡ የዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ ከነዚሁ ፡ በኸረ ፡ ሎሚዎች ፡ አንዱን ፡ አነሣና ፡ ይህ ፡ የበኸረ ፡ ሎሚ ፡ አትክልት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተባሉት ፡ መንግሥቶች ፡ ውስጥ ፡ ወደማንኛው ፡ ወገን ፡ ይቆጠራል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

ከልጃገረዶቹም ፡ አንዲቱ ፡ አትክልት ፡ ወደሚያስተክል ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ይቆጠራል ፡ አለችው ።

ዳግም ፡ ከኪሱ ፡ አንድ ፡ ወርቅ ፡ አወጣና ፡ ይህስ ፡ ወደማንኛው ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ይቆጠራል ፡ አለ ። ማዕድን ፡ በሚያሠራና ፡ በሚያስወጣ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ይቆጠራል ፡ ብላ ፡ መለሰች ።

እርሷም ፡ የመለሰችለት ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ተገነዘበ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ እኔስ ፡ በማንኛው ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ እቆጠራለሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃት ። እርሷም ፡ በእንስሳ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ትቆጠራለህ ፡ ብላ ፡ መለሰች ። ይህንም ፡ ስትመልስ ፡ ንጉ



ሡን ፡ የእንስሳ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ባፍ ፡ የሚያስቀይም ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ መሰላት ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ አእምሮዋን ፡ አጸጸተችውና ፡ ሰውነቷ ፡ በጣም ፡ ተለዋወጠ ። ዳግም ፡ አሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ እግዚአቤሔር ፡ ሰውን ፡ በአምሳሉ ፡ ነው ፡ የፈጠረው ፡ የሚለውን ፡ አስባና ፡ ተመልክታ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እየችና ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ነህ ፡ አለችው ። ንጉሡም ፡ በዚህ ፡ ደስ ፡ በሚለውና ፡ ቀና ፡ በሆነው ፡ ቃልዋ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከመቀመጫው ፡ ቆነጥነጥ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነሣና ፤ እጁንም ፡ እትከሻዋ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሥ ፡ እንድሆን ፡ ባረከኝ ፡ እያለ ፡ በኀዘንና ፡ በትካዜ ፡ ተናገረ ።

ይኸ ፡ ምሳሌ ፡

የሚያስተምረን ፡ ምንድን ፡ ነው ?

## ገንዘብ ::

### ለወዳጆችህ ፡ ታዘዝ ።

በጣም ፡ የሚዋደዱ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩና ፡ ሁልጊዜ ፡ አብረው ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። ያንደኛው ፡ ልጅ ፡ አባት መልካም ፡ የሆነ ፡ ያትክልት ፡ ስፍራ ፡ ነበረውና ፡ ባትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ማንጎ ፡ የሚባል ፡ ብዙ ፡ ዛፍ ፡ ነበረው ። በዛፉም ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ ነበረ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ሄደው ፡ ሳሉ ፡ አንደኛው ፡ ካትክልቱ ፡ ቀጥፎ ፡ ሊበላ ፡ ፈለገና ፡ ከፍሬው ፡ እንውሰድ ፡ ብሎ ፡ ለባልንጀራው ፡ አማከረው ። ያም ፡ ልጅ ፡ ያለፈቃድ ፡ አንዳች ፡ እንዳንወስድ ፡ አባቴ ፡ አስጠንቅቆኛልና ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ አይገባንም ፡ አለ ።

ያ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ አንዳች ፡ ብንወስድ ፡ ማንም ፡ እያየንምና ፡ አባትህ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ፡ ቢያውቅም ፡ እንኪ ፡ ርጎሩን ፡ ነው ፡ አይነካህም ፡ አለ ።

እርሱም ፡ መልሶ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ አባቴ ፡ ርጎሩን ፡ ነውና ፡ አይጐዳኝም ፡ ግን ፡ ያለርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ፍሬውን ፡ ብወስድ ፡ አባቴን ፡

እጐዳዋለሁ ፡ አለ ፣ እንደምን ፡ ትጐዳዋለህ ፡ ብሎ ፡ መልሶ ፡ ቢጠ
ይቀው ፡ አባቴ ፡ ያምነኛልና ፡ ባልታዘዘው ፡ በጣም ፡ ያዝንብኛል ፡ አለ ።
ሌላው ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ አባትህ ፡ አላየህምና ፡ ይህነን ፡ ከቶ ፡
ምንም ፡ አያውቅም ፡ አለው ። አሁንም ፡ ልጁ ፡ መልሶ ፡ አባቴ ፡
ባያውቅ ፡ ምንም ፡ ባያየኝ ፡ እኔ ፡ ፊቱን ፡ ለማየት ፡ አልችልም ፣
ፍሬውንም ፡ መውሰድ ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕሊናዬ ፡ ይነግር
ብኛልና ፡ አባቴን ፡ እጐዳዋለሁ ፣ ዳግመኛም ፡ አያምነኝም ፡ ብሎ ፡
አለ ። እርሱ ፡ እውነተኛ ፡ ልጅ ፡ ነበርና ፡ ለወዳጁ ፡ እውነቱን ፡
ለመንገር ፡ አልፈራም ።

እንዲሁም ፡ እውነተኛ ፡ ለመሆን ፡ አንፈር ። ይህ ፡ አጭር ፡
ታሪክ ፡ የሚያስተምረን ፡ ሰው ፡ አያየንም ፡ ብለን ፡ ኃጢአት ፡ እንዳ
ንሠራ ፡ ነው ፣ እግዚአብሔር ፡ ያያልና ።

የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ በስፍራው ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ፣ ጻድቃ
ንንና ፡ ኃጢአተኞችን ፡ ይመለከታሉ ።

ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ አንዳች ፡ ከርሱ ፡ የሚሰወር ፡ የለም ። ሁሉ ፡
ባይኑ ፡ ፊት ፡ የተከፈተና ፡ የተገለጸ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነገርም ፡ ያለን ፡
ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

በምንም ፡ ነገር ፡ ማንም ፡ አያታላችሁ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ምክን
ያት ፡ በማይታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቍጣን ፡ ያመጣ
ልና ፡ ባልንጀሮችም ፡ አትሁኗቸው ።

## ዝንጋዔ ::

ኒው ፡ ቶን ፡ የሚባለው ፡ በጣም ፡ የተከበረው ፡ ፈላስፋ ፡ አንዳ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ ብርቱ ፡ ብርቱ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ግዴታ ፡ ነበረውና ፡ አሳ
ቡንም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ያሳርፍበት ፡ ነበርና ፣ በአእምሮው ፡ ጥፋት ፡
በፍጹም ፡ ነገር ፡ ይረሳ ፡ ጀመረ ። በዚሁም ፡ አሳብ ፡ ምክንያት ፡
በክፍሉ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ እንዲያነጋግረው ፡ አይፈቅድም ፡
ነበርና ፡ መዝጊያውን ፡ እየዘጋ ፡ ይቀመጥ ፡ ጀመር ። አንድ ፡ ቀን ፡
ጪት ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ ሲያስብ ፡ ሳለ ፡ ከቤ
ት ፡ ሰቦቹ ፡ ጋራ ፡ ምሳውን ፡ ለመብላት ፡ አልፈቀደም ፡ ነበር ።



የምሳ ፡ አሰናጂዎችም ፡ አሰቃ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጠሙን ፡ ሲውል ፡
ያመዋል ፡ በማለት ፡ ፈርቶ ፡ አንደኛውን ፡ አሸከር ፡ እንቁላልና ፡
አንድ ፡ የውኃ ፡ ማፍሊያ ፡ የብረት ፡ ድስት ፡ አሲዞ ፡ እሚሠራበት ፡
ቤት ፡ ድረስ ፡ ላከለት ።

ይህም ፡ የአሸከሮች ፡ አሰቃ ፡ ለዚሁ ፡ ለተላከው ፡ አሸከር ፡
እንቁላሉን ፡ እንዲያፈላለትና ፡ ጌትየውም ፡ በልቶ ፡ እስኪነግ ፡
እንዲቁይ ፡ ነግሮት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ ወዶ ፡
እኔው ፡ ራሴ ፡ አፍልቼ ፡ እበላለሁና ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ አሸከሩን ፡ መልሶ ፡
ላከው ።

አሸከሩም ፡ እንቁላሉንና ፡ ድስቱን ፡ በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ በሰ
ዓቱ ፡ አጠገብ ፡ አስቀመጠና ፡ ሦስት ፡ ደቂቃ ፡ ብቻ ፡ እንዲያፈላው ፡
ነግሮት ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ። አሸከሩም ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ በአሳብ ፡ ብዛት ፡
ይረሳዋል ፡ በማለት ፡ አስቦ ፡ በፍጥነት ፡ ተመለሰና ፡ ቢያየው ፡ አሰ
ቃው ፡ እንዳለው ፡ አሳብ ፡ ገብቶት ፡ ኖሮ ፡ ባንዱ ፡ እጁ ፡ እንቁ
ላሉን ፡ ይዞ ፡ አሳስቶ ፡ ሰዓቱን ፡ እድስቱ ፡ ውስጥ ፡ ጨምሮ ፡ ቆሞ ፡
ሲያፈላ ፡ ሳለ ፡ ደርሶ ፡ አገኘው ።

እንደ ፡ ፈላስፋው ፡ አድርጎ ፡ ማሰብ ፡ ይገባልን ?

## ተርብና ንብ ::

እየተመመ ፡ የሚሄድ ፡ አንድ ፡ ተርብ ፡ ንብን ፡ አየና ፡ እንዲህ
አለው ። ትንሹ ፡ ያጐቴ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፣ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ በሰዎች ፡
ዘንድ ፡ የተወደድኸው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፣ ልትነግረኝ ፡
ትችላለህን ፡ ? ጀርባዬ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ያበራል ፡ እንደ ፡ ወር
ቅም ፡ ያምራል ፣ ለማየትም ፡ በትክክል ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ያም ፡
ቢሆን ፡ ሰው ፡ እንደማይወደኝ ፡ ነገሩኝ ።

ንብም ፡ ሲመልስ ፡ አጐቴ ፡ ሆይ ፡ ሁሉም ፡ እውነትህ ፡ ነው ።
ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ተንኰለኛ ፡ ብሆን ፡ ካንተ ፡ አብልጠው ፡ አይወ
ዱኝም ፡ ነበር ። ደም ፡ ግባትህ ፡ መልካም ፡ ነው ። ክንፍህም ፡ ለስ
ላሳ ፡ ነው ፣ ለሰው ፡ ፊት ፡ ሰው ፡ ትመስላለህ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡
ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ መናደፍህን ፡ አይተው ፡ አያምኑሁምና ፡

ነው ፡፡ ዳግመኛም ፡ ለአደራ ፡ የማትበቃ ፡ ስለ ፡ መሆንህ ፡ ነው ፡፡
አሁንም ፡ አንተ ፡ እንደምታይ ፡ ሁለንተናዬ ፡ ደስ ፡ የሚያ
ሰኝ ፡ ለስላሳ ፡ ነውና ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሁኖ ፡ የሚያዝን ፡ የለም ፡፡ ሠራተኛ
ነኝ ፡ እንጂ ፡ የምጎዳ ፡ አይደለሁም ፡ አለ ፡፡

እንግዲያስ ፡ እንደ ፡ ተርቡ ፡ ጠባዩ ፡ ክፉ ፡ ከሆኑ ፡ ምንም ፡
እንኳ ፡ ቢምያሩ ፡ ከቶ ፡ አይወደዱምና ፡ ይህችን ፡ ትንሽ ፡ ታሪክ ፡
ተመልክተው ፡ ሰዎች ፡ እንዲጠነቀቁ ፡ ምሳሌው ፡ ያስተምረናል ፡፡

ከዚህ ፡ ትንሽ ፡ ታሪክ ፡ ተጠንቀቁ ፡ እባካችሁ ፡
በኒህ ፡ የደረሰ ፡ እንዳይደርስባችሁ ፡፡

## በባሳገር ቤት ፡፡

በእርሻው ፡ አቅራቢያ ፡ ፈረስ ፡ ላምና ፡ በግ ፡ የሚግጡበት ፡
መስክ ፡ ነበር ፡፡ ግን ፡ ፈረሱ ፡ ከእነዚህ ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋራ ፡ እንዳይ
ሰማራ ፡ ኩርቶ ፡ ጌታዬንና ፡ እመቤቴን ፡ በጀርባዬ ፡ ለመሸከም ፡
የምችል ፡ እኔ ፡ ክብር ፡ የለኝምን ? ወይስ ፡ እመቤቴንና ፡ ልጆች
ዋን ፡ በሠረገላ ፡ ይዤ ፡ አልሄድምን ? አለና ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ተለ
ይቶ ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፡፡

ላሚቱ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ኩርታ ፡ ነበረችና ፡ ከበጊቱ ፡ ጋራ
እንዳትበላ ፡ አስባ ፡ ቀጥለን ፡ የምንጽፈውን ፡ ቃል ፡ ተናገረች ፡፡ የ
ሚጠጣውን ፡ ወተት ፡ ለጌታዬ ፡ እኔ ፡ አልሰጥምን ፡ ? ወይስ ፡ ደግ
ሞ ፡ ከቡንና ፡ ከቻይ ፡ ጋራ ፡ የሚወጣ ፡ ስልባቦት ፡ ከወተቴ ፡ አይ
ገኝምን ፡፡ ደግሞስ ፡ ከወተቴ ፡ ቅቤና ፡ አይብ ፡ አይገኝምን ?
አለች ፡፡

በጊቱም ፡ ራሳቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረጉትን ፡ የነዚህን ፡
የሁለቱን ፡ ባልንጀሮቿን ፡ ነገር ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አላገባችውም ፡፡
ከእነዚህም ፡ ከሁለቱ ፡ ይልቅ ፡ በጣም ፡ አብልጣ ፡ ለጌታዋ ፡ እን
ድምትጠቅም ፡ አስታወቀች ፡፡ እንደዚህም ፡ ተናገረች ፤ ለጌታዬና ፡
ለእመቤቴ ፡ ለልጆቻቸውም ፡ ለሙቀት ፡ ልብስ ፡ የሚሆነውን ፡
ጠጉር ፤ የብርድ ፡ ልብሱን ፡ ሥጋጃውን ፡ ደግሞም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ አልሰጥምን ?



ኧረ ፡ ገና ፡ እንዴት ፡ አገረማለሁ ፡ በዚያ ፡ በረዥሙ ፡ በክረ
ምት ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ የሚገኘውን ፡ ለስላሰውን ፡ ጠጉር ፡ ባያገኙ ፡
ብርዱን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሁነው ፡ በዘለቁት ፡ ነበር ፡፡ ጌታዬና ፡ እመ
ቤቴ ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ባይቀመጡ ፤ ወተትም ፡ ባይጠጡ ፡ ቅቤና ፡
አይብም ፡ ባያገኙ ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ፡፡ የሚ
ሞቅ ፡ ልብስ ፡ ግን ፡ ባይኖራቸው ፡ በጤና ፡ መኖር ፡ አይሆንላቸ
ውም ፡ ብላ ፡ ነገሯን ፡ ወሰነች ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ልባቸውን ፡ የሚያስታብዩትን ፡ ይጠላል ፡
ለትሑታን ፡ ግን ፡ ጸጋውን ፡ ይሰጣል ፡፡

ከናንተ ፡ እያንዳንዱ ፡ ባልንጀራውን ፡ ከራሱ ፡ አልቆ ፡ ያከ
ብር ፡፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ አይመልከት ፤ ለባልንጀራ
ውም ፡ እንጂ ፡፡

## የእግዚአብሔር መንገድ ደበልጣል ፡፡

አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ከገበያ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ለመግባት ፡
ሲጋልብ ፡ ሳለ ፤ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ የመላበት ፡ ከረጢት ፡ ወድሎ ፡
ነበር ፡፡ ዝናሙም ፡ በጣም ፡ ክፉኛ ፡ ይዘንም ፡ ነበርና ፡ ልብሱን ፡
ሁሉ ፡ ዘልቆ ፡ አካላቱን ፡ ሁሉ ፡ አቀዘቀዘው ፡፡ በዚሁም ፡ ዝናም ፡
በጣም ፡ ተመርሮ ፡ እኔ ፡ መንገድ ፡ ስሄድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዛሬን ፡
ቀን ፡ ለምን ፡ የዝናም ፡ ቀን ፡ አደረገብኝ ፡ እያለና ፡ እያጉረመረመ
ይሄድ ፡ ነበር ፡፡ እርሱም ፡ ወዲያው ፡ ጥቅጥቅ ፡ ካለ ፡ ደን ፡ ደርሶ ፡
እየፈራ ፡ ሲጓዝ ፡ አንድ ፡ ወንበዴ ፡ ከደኑ ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡
ጠመንጃውን ፡ ደቀነና ፡ ሊገድለው ፡ ቃታውን ፡ ሳብ ፡ አድርጎ ፡
ተኩሰበትና ፡ ሳይመታው ፡ ቀረ ፡፡ ይህም ፡ ወንበዴ ፡ የተኩሰው ፡
ክልቡ ፡ ሊገድለው ፡ ነበር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቀኑ ፡ ዝናም ፡ ሆኖ ፡ ጠመ
ንጃውና ፡ ጥይቱ ፡ ስለ ፡ ረጠበና ፡ ስለ ፡ ዛገ ፡ እርሳሱ ፡ ከሸፎ ፡
ርቆ ፡ ለመሄድ ፡ አልቻለም ፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይኸ ፡ ነጋዴ ፡ ሰው ፡ ፈረሱን ፡ ኩረኩረና ፡
ለማምለጥ ፡ ቻለ ፡፡ እርሱም ፡ በዳነ ፡ ጊዜ ፡ ለብቻው ፡ ሆኖ ፡ ሲነጋ
ገር ፡ እንደሚከተለው ፡ አለ ፡፡ የዚያን ፡ የዝናም ፡ አከፋፍ ፡ ሳማርር ፡

የነበርሁት ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዕብድ ፡ ኖሬያለሁ ። ቀኑ ፡ ዝናምና ፡ ወጨፎ ፡ ባይሆን ፡ ሰማዩም ፡ ጠርቶ ፡ ፀሐይ ፡ ብቻ ፡ ኑሮ ፡ ቢሆን ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ሞቼ ፡ ሬሳዬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተዘርሮ ፡ ይቀር ፡ ነበር ።
ልጆቼም ፡ አባታችን ፡ ይመለሳል ፡ ብለው ፡ ሲጠብቁ ፡ በከንቱ ፡ ሳያገኙኝ ፡ ይቀሩ ፡ ነበር ። እኔም ፡ ተመርሬ ፡ ያጉረመረምሁበት ፡ ዝናም ፡ ገንዘቤንና ፡ ሕይወቴን ፡ አዳነልኝ ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተጸጸተ ።

አሁንም ፡ ለወደፊቱ ፡ በዚሁ ፡ ምሳሌ ፡ ለዘለዓለም ፡ እግዚአ አብሔር ፡ የላከውና ፡ ያዘዘው ፡ ይሻላል ፡ ብዬ ፡ እጥራለሁና ፡ አስ ባለኙ ፡ ብሎ ፡ ምስጋናውን ፡ ፈጸመ ።

የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ምንድን ፡ ነው ?
ትርጓሜውን ፡ ልታውቅ ፡ ትችላለህን ?

## ጅብና አንበሳ ።

አንድ ፡ አንበሳና ፡ ዘጠኝ ፡ ጅብ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ሄዱ ፡ ይባላል ። ሲያድኑ ፡ ዐሥሩ ፡ ዐሥር ፡ ፍሪዳ ፡ አገኙ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢዋደዱ ፡ እየድርሻቸው ፡ መካፈል ፡ አይቀርምና ፡ እንካ ፈል ፡ ተባባሉ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከዘጠኙ ፡ አንዱ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ መቼም ፡ ፈሪ ፡ አይጸድቅምና ፡ ዘጠኙ ፡ ፍሪዳ ፡ ላቶ ፡ አንበሳ ፡ አንዱ ለዘጠኛችን ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ተናገረና ፡ እየድርሻቸው ፡ ተካፍለው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የዋለ ፡ መጠየቅ ፡ አይቀርምና ፡ ከከተማ ፡ የዋለ ፡ የእንጀራ ፡ አባታቸው ፡ የዋሉበትን ፡ ምክንያት ፡ ቢጠይቃቸው ፤ ይኸው ፡ አንበሳና ፡ ዘጠኝ ፡ ጅቦች ፡ ሆነን ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ሄደን ፡ ዋልን ። ለዐሥራችንም ፡ ዐሥር ፡ አግኝተን ፡ አሁን ፡ እንደምታየን ፡ ለዘጠኛችን ፡ አንድ ፡ ፍሪዳ ፡ ተካፍለን ፡ መምጣታችን ፡ ነው ፡ አሉት ።

እንዴት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ጕር ፡ የማይሰማው ፡ የለም ፡ ላንድ ፡ አንበሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ለዘጠኝ ፡ ጅቦች ፡ አንድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ መካፈል ፡ ነው ። ላሚቷን ፡ ንዱና ፡ አንዷን ፡ ሰጥቼ፡ዘጠኙን ፡ እሰ



መልሳለሁ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ አንበሳው ፡ ቤት ፡ እየፎከረ ፡ ደረሰና ፡ እውነትም ፡ የአንበሳን ፡ ፊት ፡ ቢለመከተው ፡ እንኳንስ ፡ እንዲቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ዘጠኙን ፡ ሊመልስና ፡ ካሥር ፡ ፍሪዳ ፡ አንዲቱ ፡ ስለጐደለችበት ፡ ለካ ፡ በሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ጸጸት ፡ አድሮበት ፡ ኑሮ ፡ እሳት ፡ ለብሶ ፤ እሳት ፡ ጕርሶ ፡ ቆየውና ፡ በል ፡ የመጣህበትን ፡ ጉዳይ ፡ ተናገር ፡ ቢለው ፤

ዋ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፤ ያቺን ፡ የዘጠኝ ፡ ድርሻ ፡ ትሁን ፡ የተባለችውን ፡ ፍሪዳ ፡ ዐሥረኛ ፡ አድርገው ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ በልጆቼ ፡ ስም ፡ ሁኘ ፡ እለምንዎታለሁ ፡ ብሎ ፡ ጨርሶ ፡ አበረከተው ። እቶ ፡ አንበሳም ፡ ከብልህ ፡ ቀንሶ ፤ ከሞኝ ፡ ጨርሶ ፡ የሚኖር ፡ ብልዋ ፡ ነውና እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ብሎ ፡ በሣቅና ፡ በጨዋታ ፡ ሸኘው ፤ ይባላል ።

ምክር ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፤ ዘጠኙ ፡ ጅቦች ፡ ያለ ፡ አቅማቸውና ፡ ያለጓደኛቸው ፡ ከአንበሳ ፡ ጋራ ፡ አደን ፡ ውለው ፡ የዕለት ፡ ራት ፡ አጥተው ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ እናንተም ፡ አለኩያችሁ ፡ ዐመጸኛ ፡ ከሆነ ፡ ጋራ ፡ ጓድ ፡ አትሁኑ ። እርሱን ፡ ተጠግተን ፡ እንጠቀማለን ፡ ስትሉ የያዛችሁትን ፡ ከማጣት ፡ ትደርሳላችሁ ።

ምሳሌ ፤ ከአንበሳ ፡ መንጋጋ ፤ ማን ፡ ያወጣል ፡ ሥጋ ።

### ጥያቄ ።

፩ኛ ፤ አንበሳ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ አውሬ ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ ገላውስ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ቀለም ፡ ነው ?
፫ኛ ፤ አንበሳ ፡ በምን ፡ ይመስላል ?
፬ኛ ፤ አደን ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፭ኛ ፤ አደን ፡ የሄዱት ፡ ስንት ፡ ጓደኞች ፡ ሆነው ፡ ነው ?
፮ኛ ፤ ሲያድኑ ፡ ውለው ፡ ምን ፡ አገኙ ?
፯ኛ ፤ እንደ ፡ ምን ፡ ተከፋፈሉ ?

# የልጆች ጨዋታ ፡፡

ሁለት ፡ አብሮ ፡ አደጎች ፡ ልጆች ፡ ሲጫወቱ ፡ መቼም ፡ ጓደኛ ፡ ከሆኑ ፡ እንኳን ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ዐዋቂም ፡ ቢሆን ፡ ጠብ ፡ አይቀርምና ፡ መጫወቻዩን ፡ ወሰድህብኝ ፡ በማለት ፡ ተጣልተው ፡ ሲታገሉ ፤ ሲተናነቁ ፡ ቆይተው ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ጣለውና ፡ ሸሸ ። ያም ፡ የወደቀው ፡ ተነሥቶ ፡ ያባርረው ፡ ጀመረ ። ያም ፡ የጣለው ፡ የወደቀ ፡ ይመስል ፡ ሲሸሽ ፡ ያስደንቅ ፡ ነበረ ። ከዚህ ፡ ልጆች ፡ ከሚጫወቱበት ፡ ቦታ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዕርቅ ፡ ይዘው ፡ ነበርና ፡ ያ ፡ የጣለው ፡ ልጅ ፡ መቸም ፡ ሁለተኛ ፡ ጠብ ፡ አልፈለገምና ፡ ወደ ፡ ሽማግሌዎች ፡ አጠገብ ፡ ሄዶ ፡ ሽማግሌዎቹን ፡ ያፍር ፡ መስሎት ፡ ተጠጋ ። ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ ልጅ ፡ በመውደቁ ፡ ነዶታልና ፡ ሽማግሌዎቹን ፡ ሳያፍር ፡ ዐይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ መጣበት ። ያም ፡ ልጅ ፡ መሂጃ ፡ ሲቸግረው ፡ ጊዜ ፡ ተቆጣና ፡ በይ ፡ ነይ ፤ ያ ፡ የፊተኛው ፡ ጉልበትሽ ፡ አይደለምን ? ብሎ ፡ ተጠጋው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሲተናነቁ ፡ ያው ፡ ቀድሞ ፡ የጣለው ፡ ልጅ ፡ ጣለው ። እነዚያም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ቢገላግሉ ፡ እንቢ ፡ ብሏቸው ፡ ነበርና ፡ ለካስ ፡ ለውርደቱ ፡ ኖሯል ፡ እንዲህ ፡ ያቅለበለበው ፡ ተባባሉ ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፤ ወዳቂው ፡ አይታወቅምና ፡ ባልንጀሮቻችሁን ፡ እጅግ ፡ አሳዳችሁ ፡ አትጣሏቸው ። ቢያሳድዳችሁ ፡ ግን ፡ በግፋቸው ፡ ይወድቃሉና ፡ አትፍሯቸው ።

### ጥ ያ ቄ ።

ሁለት ፡ ልጆች ፡ ሲጫወቱ ፡ ምን ፡ ተዳረጉ ?
አንደኛውስ ፡ አንዱን ፡ ምን ፡ አደረገው ?
የወደቀው ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተከታተለው ?
የጣለው ፡ ልጅ ፡ ሸሽቶ ፡ ወዴት ፡ ተጠጋ ?
ሽማግሌዎቹስ ፡ ገላገሏቸውን ?



# ስለ ትምህርት ፡፡

ትምህርት ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፤ ካለማወቅ ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፤ ከክሕደት ፡ ወደ ፡ እምነት ፤ ከትሕትና ወደ ፡ ልዕልና ፡ ከድኅነት ፡ ወደ ፡ ባለጸግነት ፤ ከጭካኔ ፡ ወደ ፡ ርኅራኄ ፡ ከስንፍና ፡ ወደ ፡ ትጋት ፡ የምትመራ ፡ ዋና ፡ የቀናች ፡ አውራ መንገድ ፡ ናት ፤ ምናልባት ፡ የትምህርትን ፡ ጥቅምና ፡ ፍሬዋን ፡ እንዲያውም ፡ ፈጽመው ፡ ዝናዋን ፡ የማይሰሙና ፡ የማያውቁ ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ መንገድ ፡ የሚመላለሱ ፡ ይሆናሉ ። ምንም ፡ ሰው ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ቢመስል ፡ እንኳ ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ የትምህርት ፡ ዕውቀት ፡ ካልጨመረበት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሰውነቱና ፡ ለንብረቱ ፡ ትልቅ ፡ እንቅፋት ፡ ይሆንበታል ፡ ስለዚህ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ትምህርት ፡ በግድ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሆነ ። የተማረ ሰው ፡ ጥበብና ፡ ትሕትና ፤ ፍቅርና ፡ አንድነት ፡ እንዲጠቀሙ ፡ ድንቊርናና ፡ ትዕቢት ፤ ጥልና ፡ መለያየት ፡ እንዲጎዱ ፡ ለይቶ ፡ ያውቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ትምህርት ፡ ምንድንናት ፤ የሚበቃ ፡ ገንዘብና ፡ ንብረት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መዓርግና ፡ ክብር ፡ አለን ። ተምረንስ ፡ ምን ፡ ልናተርፍ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ፍሬና ፡ ጥቅም ፡ የሚያገኙበትን ፡ ጊዜያቸውን ፡ በከንቱ ፡ ጨዋታ ፡ ያሳልፉታል ። የትምህርትን ፡ ፍሬዋንና ፡ ጥቅሟን ፡ በተረዳችው ፡ አገር ፡ ግን ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ የሆኑ ፡ ልጆች ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፤ ወይም ፡ እስከ ፡ ፳ና ፡ ፴ ፡ ድረስ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ኀላፊና ፡ ጠፊ ፡ ያልሆነች ፤ ከዕንቊና ፡ ከወርቅ ፡ የከበረች ፡ ጥበብንና ፡ ትምህርትን ፡ በልባቸው ፡ ጽላት ፡ ሲቀርጹ ፡ ያድጋሉ ፤ እያሉ ፡ መጻሕፍትና ፡ ሰዎች ፡ ተናግረዋል ። ስለዚህ ፡ ስማቸው ፡ በሐውልት ፡ ተጽፎ ፡ በደንጊያ ፡ ተቀርጾ ፤ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ይቆያቸዋል ። መታሰቢያቸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ልጆቻቸውም ፡ አባቶቻችን ፤ በዚህ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ይህን ፡ ፈለሰፉ ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማለት ፡ ሳይኖርባቸው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፡ እየተባባሉ ፡ ይሽቀዳደማሉ ። ስለዚህ ፡ በባሕርና ፡

በየብስ ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ በእግር ፡ የሚሽከረከሩ ፡ እንደ ፡ አዕዋፍ ፡ በክንፍ ፡ የሚበሩ ፣ ደግሞ ፡ በነፋስ ፡ አውታር ፡ ተይዘው ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ተዘርግተው ፡ በደመና ፡ ተጭነው ፡ ሁለት ፣ ወይም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚቆዩ ፡ መኪናዎች ፡ ፈለሰፉ ።

ትምህርት ፡ በሰነፎች ፡ ዘንድ ፡ የተዋረደችና ፡ የተናቀች ፡ ናት ፡ ባዋቂዎች ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የከበረችና ፡ ከፍ ፡ ያለች ፡ ናት ፡ ትምህርትን ፡ ፈጽሞ ፡ ለማስረዳት ፡ የበቃ ፡ ዕውቀት ፡ ባይኖረኝ ፡ እንኳን ፡ መግቢያዋንና ፡ መውጫዋን ፡ ለማመልከት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ። እውነት ፡ ነው ። ሰው ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ትንሽ ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ ሳይል ፡ ሊማርና ፡ ሊመረምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሉ ፡ መሣሪያና ፡ ልብ ፡ ሰጥቶታል ።

ይህም ፡ መሣሪያ ፡ ባ፭ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። አንደኛ ፡ ዐይን ፡ ሁለተኛ ፡ እጅ ፣ ሦስተኛ ፡ አፍንጫ ፣ አራተኛ ፡ ምላስ ፣ አምስተኛ ፡ ጕሮሮ ፡ ናቸው ። እንግዴህ ፡ እነዚህ ፡ ከልብ ፡ ፈቃድ ፡ አይወጡም ። የልብን ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽማሉ ፡ እንጂ ፣ ልብም ፡ ያለነሱ ፡ አንዳች ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። እንዲያውም ፡ ፈጽሞ ፡ ሕይወት ፡ የለውም ። ከነዚህም ፡ አንዳቸው ፡ የጐደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የፈዘዘና ፡ የደነዘዘ ፡ ወይም ፡ የተሰበረና ፡ የሰለለ ፣ ወይም ፡ የቆሰለና ፡ የጐሰቆለ ፣ ወይም ፡ የደከመና ፡ የዛገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰውዮው ፡ ሙሉ ፡ ዕውቀት ፡ አያገኝም ። አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፣ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ዕውቀት ፡ የተቀነሰበት ፡ ማለት ፡ ነው ።

በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ አፍነውን ፣ እንደ ፡ ቤት ፡ ከበውን ፣ እንደ ፡ ውሃ ፡ አጥልቀውን ፣ እንደ ፡ ጉም ፡ ሸፍነውን ፣ እንደ ፡ ተራራ ፡ ጋርደውን ፣ የሚኖሩ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቶችን ፡ ባይናችን ፡ አይተን ፡ በእጃችን ፡ ዳስሰን ፣ ባፍንጫችን ፡ አሽትተን ፣ በምላሳችን ፡ ቀምሰን ፣ በጕሮሮዋችን ፡ ሰምተን ፡ ብንመረምራቸው ፡ ልባችንን ፡ የሚያረካ ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጡናል ። ዳግመኛም ፡ ከነሱ ፡ የራቁትን ፡ አቅርበን ፡ የረቀቁትን ፡ አጉልተን ፣ የተሠወሩትን ፡ ገልጸን ፡ ለመመርመር ፡ ኀይል ፡ እናገኛለን ። አንተ ፡ ታካች ፡ ወደ ፡ ገብረ ፡ ጉንዳን ፡ ሂድ ። መንገድዋንም ፡ ተመልከት ። አካሄድዋንም ፡ ሥራዋንም ፡ ሁሉ ፡ መርምር ። ጠቢብም ፡ ሁን ። ዐይን ፡ አይቶ ፡ ልብ ፡ ይፈርዳል ። እንደተባለ ፡ በመጀመሪያ ፡ ዐይናችን ፣ የሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ ቅርጽ ፡ መልክ ፡ ዐይነት ፡ ቀለም ፣ ወርድና ፡ ስፋት ፡



ርዝመታቸውን ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ ለልብ ፡ ይነግራል ። ልብም ፡ ለሐሳብ ፡ የተስማማውን ፡ አይቶ ፡ አንዱን ፡ ዐይነት ፡ ለይቶ ፡ እንዲያመጣለት ፡ እጅን ፡ ይልካል ። የቀሩትም ፡ እንደዚሁ ፡ በየሥራቸው ፡ ለልብ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ። ትምህርትም ፡ የምትገኘውና ፡ የምትሰጠው ፡ በነዚህ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፣ አምስቱ ፡ አዕማደ ፡ ሕዋሳት ፡ ተባሉ ። በሌላም ፡ ቃል ፡ አምስቱ ፡ የዕውቀት ፡ በሮች ፡ ተባሉ ፡ ስለዚህ ፡ ዐይናችን ፡ ለማየት ፣ እጃችን ፡ ሊመሥራት ፣ ጕሮሮዋችን ፡ ለመስማት ፡ የፈጠኑ ፡ ይሁኑ ።

## የትምህርት ፍቅር ::

ሰው ፡ ሁሉ ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ያገኘውን ፡ ዕውቀቱን ፡ ለማጐልመስና ፡ የሚያሰናክለውን ፡ መጥፎ ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ ሊያስወግድበት ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልገዋል ።

ለዚሁ ፡ ምሳሌ ፡ ባጭሩ ፡ እገልጻለሁ ። አንድ ፡ ጥንቁቅ ፡ ገበሬ ፡ ተክል ፡ ይተክልና ፡ እንዳይደርቅ ፡ ውሃ ፡ አጠጥቶ ፣ ከብት ፡ እንዳይረግጠው ፡ አጥሮ ፣ ነፋስ ፡ እንዳይጥለው ፡ አስደግፎ ፣ ኋላም ፡ ለፍሬ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወፍ ፡ እንዳይበላበት ፡ ጠብቆ ፡ ያኖረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የተከለው ፡ ዛፍ ፡ አንዱ ፡ ዘለላ ፡ ፴ ፣ አንዱ ፡ ፷ ፣ አንዱ ፡ መቶ ፡ ያፈራለትና ፣ እሱም ፡ በልቶ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶቹንም ፡ አብልቶ ፣ ለጎረቤቶቹ ፡ ትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ይችላል ።

እንዲሁም ፡ ሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ ያገኘውን ፡ ዕውቀት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ጥንቁቅ ፡ አስተማሪው ፡ በመልካም ፡ ምክር ፡ ልቡን ፡ እያነጸ ፣ የእግዚአብሔርንም ፡ መንገድ ፡ እያሳየ ፣ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ለሀገሩ ፡ ፍቅር ፡ ለመንግሥቱ ፡ ጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ ትምህርት ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፣ ይህ ፡ በትምህርት ፡ ያገኘው ፡ ዕውቀት ፡ ለራሱ ፡ ይቅርና ፡ ለመላ ፡ ሀገሩ ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጥ ፡ አይጠረጠርም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፣ ሰው ፡ ይህን ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ያገኘውን ፡ ዕውቀት ፡ በትምህርት ፡ ካላጐለመሰው ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ በቀለች ፡ አትክልት ፡ ባደገችም ፡

ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ ፈጥኖ ፡ እንደሚጥላት ፡ እንዲሁም ፡ በትምህርት ፡ ያልተገኘች ፡ ዕውቀት ፡ ትንሽ ፡ ፈተና ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥና ፡ ወደ ድንቍርና ፡ እንደምታደርስ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። ግን ፡ አእምሮዋ ቸው ፡ ጐደሎ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ልጆቻችንን ፡ ከቶ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ተማሪ ፡ አናደርግም ፡ ሲሆን ፡ ወታደር ፡ ነጋዴ ፡ ባይሆንም ፡ ገበሬ እናደርጋቸዋለን ፡ እንጂ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ሞልተዋል ።

ይሁንና ፡ ወታደርነት ፤ ንግድ ፤ ግብርና ፤ እነዚህንም ፡ የመ ሰሉ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ በትምህርት ፡ መገኘታቸውን ፡ ማን ፡ ባስ ረዳልን ? እንግዲያውማ ፡ ሰው ፡ ካልተማረ ፡ ሰማያዊስ ፡ ምድ ራዊስ ፡ ርስት ፡ እንዴት ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ? ማለት ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ የሥላሴን ፡ አንድነትና ፡ ሦስትነት ፡ ማ ወቅ ፡ ይቻላል ? ሰማያዊ ፡ ርስት ፡ ይሁን ፡ ምድራዊ ፡ ርስት ፡ እን ዴት ፡ ይታጣ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ይመልከት ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰው ፡ ሐሳቡን ፡ የሚፈጽምበት ፡ ጽሕፈትና ፡ ቍጥር ፤ ሌላም ፡ ለንግድና ፡ ለእርሻ ፡ ይህንኑ ፡ ለመ ሰለ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚበቃ ፡ ትምህርት ፡ ከሌለው ፡ ኑሮውን ፡ በየጊዜው ፡ እያሻሻለ ፡ በሰላም ፡ ለመኖር ፡ እንዴት ፡ ይችላል ?

እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ነገሩ ፡ እንመለስ ፡ ትምህርት ፡ ለሰ ው ፡ በግድ ፡ ማስፈለጉን ፡ ከተረዳን ፡ በኋላ ፡ እንዲሁም ፡ ለሥጋዊ ና ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ወገን ፡ የሚሆኑ ፡ የሰውን ፡ ሐሳብ ፡ በንጹሕ ፡ መንፈስ ፡ የሚያንጹ ፡ መጻሕፍት ፡ ያስፈልጋሉ ። ስለ ፡ ሆነ ፡ ለመ ንፈሳዊ ፡ ወገን ፡ የሚሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ የቀድሞ ፡ ሊቃውንትና ፡ መነኰሳት ፡ የደረሱዋቸው ፡ አዋልድ ፡ የሚባሉ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ይገኛሉ ። ደግሞም ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ ብንጠራጠር ፡ ስንኳን ፤ የብሉያትንና ፡ የሐዲሳትን ፡ መጻሕፍት ፡ ብንመለከት ፡ በመንፈ ሳዊ ፡ ትምህርት ፡ በኩል ፡ አጉልቶ ፡ ያስረዳናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሥጋዊ ፡ ትምህርት ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ ለጊዜው ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ የሚሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ አንዳንድ ፡ ሊቃውንት ፡ ቢጽፉልን ፡ እነ ዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ በሥጋዊ ፡ በኩል ፡ ለሚሆን ፡ ትምህርት ፡ ጠን ቅቀው ፡ የሚያስረዱን ፡ አይደሉም ።

ስለዚህ ፡ የዓለምን ፡ ታሪክና ፡ የሰውን ፤ የእንስሳን ፤ የዕጽዋ ትን ፡ የእሳት ፡ የውሃን ፡ የብረት ፤ የድንጋይን ፤ ሌሎችም ፡ እነዚ ህን ፡ የመሰሉ ፡ በዐይን ፡ የማይታዩ ፤ በእጅ ፡ የማይጨበጡ ፤ ጤናን



ጉምን ፤ ነፋስን ፡ ደመናን ፡ እነዚህንም ፡ የመሳሰሉትን ፡ ፍጥረቶች ፡ ሁሉ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረታቸውን ፡ ተመራምሮ ፡ ሕክምናና ፡ መሐንዲስ ነትን ፡ እነዚህንም ፡ የመሳሰሉትን ፡ ታላላቅ ፡ ትምህርቶችን ፡ ለመማር ፡ ከአውሮፓዎች ፡ ቋንቋ ፡ አንዳንድ ፡ ቋንቋ ፡ መማር ፡ ግዴታ ፡ አለብን ።

## የመልካም አባት ኑዛዜ ::

አንድ ፡ ገበሬ ፡ ሞቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹን ፡ ጠርቶ ፡ ባጠ ገቡ ፡ አቁሞ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ተናዘዘላቸው ። ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ አሁን ፡ በሽታው ፡ ስላጣደፈኝ ፡ ከቦታችን ፡ የደበቅሁትን ፡ ወርቅ ፡ ቦታውን ፡ ላመለከታችሁ ፡ አልተቻለኝምና ፡ ቦታውን ፡ በመደዳ ው ፡ ቆፍራችሁ ፡ እንድትፈልጉት ፡ አላቸው ። ልጆችም ፡ የሞተው ን ፡ አባታቸውን ፡ ከቀበሩ ፡ በኋላ ፡ ያባታቸውን ፡ ኑዛዜ ፡ ተከትለው ዶማቸውንና ፡ አካፋቸውን ፡ ይዘው ፡ ወርቁን ፡ ለማግኘት ፡ ቦታቸ ውን ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ቆፈሩት ፡ ይባላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ አባታቸው ፡ እንደዚህ ፡ ያላቸው ፡ ልጆቹ ፡ ሥራ ፡ እንዳይፈቱ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርግጥ ፡ ወርቅ ፡ ደብቆ ፡ አይደ ለም ። ልጆቹም ፡ ወርቁን ፡ ባጡት ፡ ጊዜ ፡ እንግዲህ ፡ ወርቁን ፡ ከጣ ነው ፡ የቆፈርነውን ፡ ቦታችንን ፡ ስንዴና ፡ ገብስ ፡ እንዝራው ፡ ብለ ው ፡ ዘሩትና ፡ የዘሩት ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ አፈራላቸው ። ስየለዚህ ፡ የዘ ሩትን ፡ ፍሬ ፡ እየሸጡ ፡ ወርቃቸውን ፡ ይሰበስቡ ፡ ጀመር ። ያን ጊዜ ፡ ጥቅማቸውን ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹም ፡ ሥራ ፡ እንዳይፈቱና ቦታውም ፡ እንዳይቦዝን ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አባታቸው ፡ ወርቅ ፡ እንዳልደበቀ ፡ ተረዱት ፡ ይባላል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ መልካሙ ፡ ገበሬ ፡ ሞቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹን ሰብስቦ ፡ ምን ፡ ተናገራቸው ?

፪ ፤ ልጆችስ ፡ ምን ፡ አደረጉ ?

፫ ፤ አባታቸው ፡ ወርቅ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ እውነት ፡ ደብቆ ፡ ኖሯልን ?

፬ ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ቆፍራችሁ ፡ ፈልጉት ፡ አላ ቸው ?

## ፍቅር ::

ፍቅር ፡ ፋክክርን ፤ ትምክሕትን ፡ ታሸንፋለች ።

አምስት ፡ ጣቶች ፡ እኔ ፡ አዝዛለሁ ፤ እኔ ፡ አዝዛለሁ ፡ በማለት ፡ ተጣልተው ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሂዱና ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ይነጋገሩ ፡ ጀመር ። መጀመሪያ ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ አቀረበ ። ከሁላችሁ ፡ የበለጥሁ ፡ ወፍራም ፡ ነኝ ። በትግ ልም ፡ ከናንተ ፡ አንድም ፡ የሚያሸንፈኝ ፡ የለምና ፡ ለኔ ፡ እንድት ታዘዙኝ ፡ ነው ፡ የሚገባችሁ ፡ አላቸው ።

ሌባ ፡ ጣትም ፡ ይህንን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ አንተ ፡ ብትወፍር ፡ ይልቅ ፡ ካንተ ፡ የበለጥሁ ፡ ዐዋቂ ፡ እኔ ፡ ነኝ ። ሰውዮውም ፡ በኔ ፡ አድርጎ ፡ የፈለገውን ፡ ይነጋገራል ፤ ያመለክታ ልም ። ስለዚህ ፡ ሁላችሁም ፡ ለኔ ፡ እንድትታዘዙልኝ ፡ ይገባች ኋል ፡ አላቸው ፤ መሐከለኛው ፡ ጣትም ፡ ይህንን ፡ ሰምቶ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። አንተም ፡ ብትወፍር ፤ አንተም ፡ ብታውቅ ፡ ከሁላ ችሁ ፡ ይልቅ ፡ የበለጥሁ ፡ ረጅም ፡ እኔ ፡ ነኝና ፡ ለኔ ፡ ልትታዘዙልኝ ይገባችኋል ፡ አላቸው ።

የቀለበትም ፡ ጣት ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ። እናንተ ፡ እኔ ፡ ከበ ርቴው ፡ እያለሁ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ የምትባባሉት ። ሰውም ፡ ሁሉ ፡ እኔን ፡ ነው ፡ የሚሸልመኝ ። ስለዚህ ፡ ለኔ ፡ ለክበርቴው ፡ ልትታዘ ዙልኝ ፡ ነው ፡ የሚገባችሁ ፡ አላቸው ።

ትንሹም ፡ ጣት ፡ ፋንታውን ፡ ተነሣና ፡ አባካችሁ ፡ ወንድ ሞቼ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ንግግራችሁ ፡ አላማረኝም ። ይልቅ ፡ ብትቀበ ሉኝም ፡ ባትቀበሉኝም ፡ ትንሽ ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ልንገራችሁ ፡ አዳምጡኝ ፡ ብሎ ፡ ሰበሰባቸውና ፡ የምክሩን ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ያከታትል ፡ ጀመር ። ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ በማይረባ ፡ ነገር ፡



ትጣላላችሁ ፡ እኔ ፡ አዝዛለሁ ፡ እኔ ፡ አዝዛለሁ ፡ ብትባባሉ ፡ እኛ ፡ መቾም ፡ የሰውዮው ፡ ታዛዦች ፡ ነንና ፡ ተስማምተን ፡ ሥራችንን ፡ እንድንሠራ ፡ እኔ ፡ ትንሹ ፡ ወንድማችሁ ፡ እጥብቄ ፡ እለምናችኋለሁ ። ለዚሁ ፡ የሚስማማውን ፡ ጥቅስ ፡ ልጥቀስላችሁ ፡ ብሎ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ጠቀሰላቸው ።

አንድነትና ፡ መስማማት ፡ ኀይል ፡ ይሰጣል ፡ አላቸው ።

ጥያቄ ።

፩ ፤ አምስት ፡ ጣቶች ፡ ምን ፡ ተባብለው ፡ ተጣሉ ?

፪ ፤ አውራ ፡ ጣት ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ተመካ ?

፫ ፤ ሌባስ ፡ ጣት ፡ እንዴት ፡ ብሎ ፡ ተፎካከረ ?

፬ ፤ መሀከለኛውስ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ተወዳደረ ?

፭ ፤ የቀለበት ፡ ጣትስ ፡ እንዴት ፡ ተከራከረ ?

፮ ፤ ትንሹስ ፡ ጣት ፡ በመጨረሻ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ አስማማቸው ?

## የአንበሳና የጅብ ጓደኝነት ::

አንበሳና ፡ ጅብ ፡ በጓደኝነት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጫካ ፡ ሲኖሩ ፤ ስለ ፡ ኑሮዋቸው ፡ ምክር ፡ አሰቡ ። ምክሩም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ጅብ ፡ እኔ ፡ አህያ ፡ ፍለጋ ፡ በሄድሁ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ መጫሪያውን ፡ ወልውሎ ፡ ካራውን ፡ ስሎ ፡ አህያዩን ፡ ለመብላት ፡ ጅብ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ አንገቱን ፡ እለዋለሁ ፡ ሲል ፡ ሰማሁት ፡ አለ ።

አንበሳም ፡ ታልህስ ፡ እኔም ፡ በግና ፡ ፍየል ፤ ላምም ፡ ፍለጋ ፡ በሄድሁ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቶቹ ፡ ወጥመድ ፡ እናጥምድና ፡ ከወጥመዳችን ወስጥ ፡ ማባበያ ፡ ትንሽ ፡ ሥጋ ፡ ባደረግንለት ፡ ጊዜ ፡ ለመብላት ፡ ገብቶ ፡ ወጥመዱ ፡ ሲይዘው ፡ አንገት ፡ አንገቱን ፡ ብለን ፡ እንገድ ለዋለን ፡ እያሉ ፡ ሲፎክሩ ፡ ሰማሁ ፡ አለው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነሱ ፡ እንዲህ ፡ ከሚፎክሩብን ፡ እኛስ ፡ እን ደነሱ ፡ ከብት ፡ ብናረባ ፡ ይሆን ፡ የለም ? ይልቁንም ፡ የኛን ፡ ገን

ዞብ ፡ ፈላጊ ፡ የለውም ፤ በመልካም ፡ ሊረቡልን ፡ ይችላሉ ፡ ተባብለው ፡ ጅብ ፡ ጊደር ፡ ገዛ ። አንበሳም ፡ በሬ ፡ ገዛ ፡ ሁለቱንም ፡ ባንድ ፡ ደን ፡ ውስጥ ፡ አኑረዋቸው ፡ ሳሉ ፤ የጅብ ፡ ጊደር ፡ ወለደች ፡ ወንድሚ ፡ አቶ ፡ አንበሳ ፡ የኔ ፡ ጊደር ፡ ወለደች ፤ ያንተ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆነልህ ፡ አለው ። እሱም ፡ ከጉያው ፡ ደም ፡ ቀባና ፡ የኔም ፡ በሬ ፡ ወለደ ፡ አለው ። ጅብም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ካደው ።

ይህነንም ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ይፍረድ ፤ ማን ፡ ይፍረድ ፡ ተባብለው ፡ ፍርዱ ፡ በጠጣ ፡ ሊፈጸም ፡ ተስማምተው ፡ ከተፈጣጠሙ ፡ በኋላ ፡ መላክተኛ ፡ ዝንጀሮ ፡ ሆኖ ፡ አቶ ፡ አንበሳና ፡ ጅብ ፡ ተጣልተው ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ተቸግረናልና ፡ መጥተሽ ፡ እንድትፈርጂ ፡ ብለውሻል ፡ ብሎ ፡ ከነገራት ፡ በኋላ ፡ ጠጣዩቱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይታ መጣች ።

አንበሳም ፡ በጉልህ ፡ ቃል ፡ አንቺ ፡ በቶሎ ፡ ነይ ፡ ብለን ፡ ብንልክብሽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እስካሁን ፡ ቆየሽ ። አሁንም ፡ በይ ፡ ሳልደቁስሽ ፡ በቶሎ ፡ ፍረጂ ፡ ብሎ ፡ በሚያስፈራ ፡ ቃል ፡ ቢናገራት ፤ ጌታዬ ፡ አቶ ፡ አንበሶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ልናገር ፡ አድምጠኝ ፡ የቆየሁት ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ተቀዶብኝ ፡ እሱን ፡ ስሰፋ ፡ ነው ፡ አለችው ። የትአባሽ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ይቀደዳል ፡ አላት ። አንተ ፡ የትአባትህ ፡ በሬ ፡ ይወልዳል ? ብላ ፡ ፈርዳበት ፡ ከዛፏ ፡ ተሰቀለች ፡ ይባላል ።

### ጥ ያ ቄ ።

አንበሳና ፡ ጅብ ፡ በምን ፡ ስፍራ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ?
አብረው ፡ ሲኖሩ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ተማከሩ ?
አንበሳ ፡ ምን ፡ ገዛ ፡ ? ጅብስ ?
ጊደሪትዋ ፡ ብትወልድ ፡ አንበሳ ፡ ምን ፡ አለ ?
ሁለቱ ፡ የእኔ ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ በመባባል ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ ማን ፡ ፈረደ ?
ፍርዱ ፡ እንደ ፡ ምንድር ፡ ነው ?



## ስይጥና ድመት ፡፡

ድመቶች ፡ ሴት ፡ ልጆቻችሁን ፡ ስጡን ፡ እንጋባ ፡ እንዛመድ ፡ ሲሉ ወደ ፡ አይጦች ፡ አማላጅ ፡ ላኩና ፤ አይጦች ፡ ይሁን ፡ አሉ ። በዚሁም ፡ ተስማምተው ፤ ተዋውለው ፡ ተፈጣጠሙ ።

ከሰርጉ ፡ በፊት ፡ ከአይጦች ፡ አንዲቱ ፡ ወገኖችዋን ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ መከረቻቸው ። ድመት ፡ አንዳች ፡ ሳንበድለው ፡ እንዳጠፋን ፡ መኖሩን ፡ ታውቃላችሁ ። ዛሬ ፡ እንጋባ ፡ እንዛመድ ፡ ይለናል ፡ ለማታለልስ ፡ እንደሆን ፡ ምኑ ፡ ይታወቃል ። ለዚህ ፡ ጉድጓድ ፡ እንማስ ። በሰላም ፡ ቢመጣ ፡ በሰላም ፡ እንሸኘዋለን ። ክፉ ፡ ቢከጅል ፡ ከጉድጓዳችን ፡ እንገባለን ። ምክሩ ፡ አይጦችን ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። ጉድጓድ ፡ ተማሰ ፤ ሰርጉ ፡ ደረሰ ። ድመት ፡ ሆ ! እያለ ፡ ሲመጣ

እንቅ ፡ እንቅ ፡ እለ ።
እይጦችም ፤ ጥልቅ ፡ ጥልቅ ።
እኛም ፡ መክረናል ።
ጉድጓድ ፡ ምሰናል ፤ እያሉ ፡ ከየጉድጓዳቸው ፡ ገብተው ፡
እመለጡ ።
እትዝለል ።
ትገባለህ ፡ ገድል ።
ደመኛህን ፡ ታረቅ ።
ውልህን ፡ አትልቀቅ ።

### ጥ ያ ቄ ።

የአይጥ ፡ ደመኛ ፡ ማነው ?
እይጥ ፡ ከሚያበላሸው ፡ ዕቃና ፡ ቡቃያ ፡ ያንዳንዱን ፡ ስም ፡ ንገር ።
ድመት ፡ ለሰው ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ ይውልለታል ?
ከተረቱ ፡ ምን ፡ ምክር ፡ አገኘህበት ?

## የቆጡን አውርድ ብሳ የብብቷን ጣለች ::

ባንድ ፡ አገር ፡ የነበሩ ፡ እንሰሶች ፡ በየወገናቸው ፡ እንደ ፡ ዘር ፡
እንደ ፡ ዘራቸው ፡ ተሰብስበው ፡ ባልንጀርነት ፡ ገጥመው ፡ ሲማከሩ ፤
ሣሩ ፡ ከለመለመበት ፤ ውሃው ፡ ከጠራበት ፤ ሰው ፡ ከሌለበት ፤ እል
ም ፡ ጥቅጥቅ ፡ ካለ ፡ ዱር ፡ እንግባና ፡ የዕድሜያችንን ፡ ያህል ፡
በተድላና ፡ በደስታ ፡ እንኑር ፡ ብለው ፡ ተመካከሩና ፡ ሄዱ ።

የሚፈልጉትንም ፡ ቦታ ፡ አገኙና ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ ያለ
አሳብ ፡ በሰላምና ፡ በዕረፍት ፡ ሲኖሩ ፤ ከመሀከላቸው ፡ ያለው ፡
አንዱ ፡ ባልንጀራቸው ፡ አህያ ፡ እጅግ ፡ ወፈረና ፡ በጣም ፡ ጥጋብ ፡
ተሰማው ። በየነገዳቸው ፡ ያሉትን ፡ ጓደኞቹን ፡ ጠርቶ ፡ ሰበሰበና ፡
አሁን ፡ የጠራኋችሁ ፡ አሳቤን ፡ ሳላማክራችሁ ፡ አልሄድም ፡ ብዬ ፡
ነው ። ነገሬንም ፡ ስሙኝ ፤ ከመሀከላችሁ ፡ አሳቤን ፡ የሚቃወመኝ ፡
በከንቱ ፡ ቂም ፡ እናተርፋለን ፡ እንጂ ፡ ያሰብኩትን ፡ ሳልፈጽም ፡
የምቀር ፡ አይደለሁም ። ዕወቁት ፡ የተነሣብኝ ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ ነው ።
ሥላቄ ፡ ጓደኞችን ፡ አቶ ፡ በሬ ፡ ያለውን ፡ መሣሪያ ፡ ተመልከቱ ፡
እሱም ፡ ከገጉሮው ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ የሚያምረው ፡ እጅግ ፡ የሚያ
ኰራው ፡ ቀንዱ ፡ ነው ። እኔም ፡ በጣም ፡ ቀንድ ፡ ማውጣት ፡ አም
ሮኛል ። በገጉር ፡ ብቻ ፡ አጊጨ ፡ ለመኖር ፡ አልችልም ፡ ብሎ ፡ ነገ
ራቸው ።

የተሰበሰቡት ፡ ጓደኞቹ ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ሆነው ፡ ተው
ባልንጀራችን ፤ ጓደኛችን ፡ ሆይ ፡ ይቅርብህ ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ ቀንድ ፡
ፍለጋ ፡ ስትሄድ ፡ አብሮህ ፡ የተፈጠረውን ፡ የሚያምረውን ፡ አካል
ህን ፡ ጆሮህን ፡ ታስወስዳለህ ፡ አርፈህ ፡ ተቀመጥ ፡ ብለው ፡ ቢመከ
ሩት ፡ መቼም ፡ አምላክ ፡ ሲጣላ ፡ ምክር ፡ እንዳይሰማ ፡ ያደርጋልና ፡
እንቢ ፡ ብሎ ፡ ከዚያ ፡ ከነበረበት ፡ ቦታ ፡ ፈንጥዞ ፡ ወጣ ።

ከመንገድ ፡ አንድ ፡ ጕበዝ ፡ ከአውድማ ፡ ውሎ ፡ እህሉን ፡ በታ
ላቅ ፡ ዳውላ ፡ ተሸክሞ ፡ አገኘውና ፡ አቶ ፡ አህያ ፡ ወዴት ፡ ልትሄድ ፡
ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። አህያውም ፡ ቀንድ ፡ አምሮኝ ፡ የሚሸጥም ፡
የሚተከልም ፡ ባገኝ ፡ እፈልጋለሁ ፡ አለው ።

ያም ፡ ሸክም ፡ ያቃተው ፡ ጕበዝ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡
ቆየኝ ፡ ቀንድ ፡ የምታበቅልበትን ፡ ቦታ ፡ አሳይሀለሁ ፡ ብሎ ፡ ቀስ ፡



አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ተመስገን ፡ ፈጣሪዬ ፡ አለና ፡ ከዚያው ፡ ግድም ፡
ከሚያውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ መጫኛ ፡ ለመነና ፡ ያንን ፡ ዳውላ ፡ በጀ
ርባው ፡ ላይ ፡ ደብልሎ ፡ ጫነና ፡ እንገዴህ ፡ ሂድ ፡ አለው ። አህያው ፡
አንድ ፡ ሜዳ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ ያንን ፡ ዳውላ ፡ አንቀርቅቦ ፡
ተሸክሞ ፡ ሲሰግር ፡ ቆየና ፡ ዐቀበቱን ፡ ሲያያዝ ፡ ትንፋሹ ፡ ቅትት ፡
ቅትት ፡ ማለት ፡ ጀመረ ። ያም ፡ ጎበዝ ፡ እንግዴህ ፡ መቃተት ፡
የለምና ፡ ሂድ ፡ አለው ። ደከመኝ ፡ አለና ፡ ቆመ ፤ ቢያዘው ፡ የከት
ከታ ፡ ዱላ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ታፋውን ፡ ጨረገደው ። ትንሽ ፡ አዘገ
መና ፡ ቆመ ። ዳግም ፡ በዚያው ፡ ዱላ ፡ ቀበተተው ። አሁንም ፡ ትን
ሽ ፡ እንዳዘገመ ፡ ወደቀ ። ያም ፡ ጎበዝ ፡ እኔ ፡ ሆይ ፡ አለና ፡ አንዱን ፡
ጕሮውን ፡ ከሥር ፡ ቆረጠው ። ቆጠቆጠውና ፡ ተነሣ ፤ ደሙን ፡ እያ
ዘራ ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሄደ ፡ ከሰውዮው ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስ ፡
ፈጽሞ ፡ ወደቀ ። ሰውዮውም ፡ የተረፈ ፡ ጕሮውን ፡ ግጥጥ ፡ ሙጥጥ ፡
አድርጎ ፡ ከሥሩ ፡ ቆረጠና ፡ ዳውላውን ፡ አራግፎ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡
ሄደ ።

ያም ፡ ጥጋበኛ ፡ አህያ ፡ ሁለት ፡ ጕሮውን ፡ አስረክቦ ፡ ከወደ
ቀበት ፡ ተነሥቶ ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ቦታ ፡ እያዘገመ ፡ ሄደና
ከጓደኞቹ ፡ ሲገናኝ ፡ ሁለት ፡ ጕሮው ፡ ተምዋጦ ፡ የሚያስደነግጥ ፡
ሆኖ ፡ ብቅ ፡ አለባቸው ። ሁሉም ፡ ደነገጡና ፡ ወደሱ ፡ ተሰብስበው ፡
አዬ ፡ ጉድ ፡ አዬ ፡ ጉድ ፡ ቀንድ ፡ አበቅላለሁ ፡ ብለህ ፡ ምክራችንን ፡
ጥሰህ ፡ ሄደህ ፡ ጕሮህን ፡ አስቆርጠህ ፡ መገረሚያና ፡ መሣለቂያ ፡
ሆንህ ፡ መጣህ ? አሉት ።

ምሳሌ ፤ አተርፍ ፡ ባይ ፡ አጉዳይ ።

ጥያቄ ።

፩ኛ ፤ ከጓደኞቹ ፡ መሀከል ፡ ጥጋብ ፡ የተሰማው ፡ ማነው ?
፪ኛ ፤ ምን ፡ ለማግኘት ፡ ተለይቶ ፡ ሄደ ?
፫ኛ ፤ ጓደኞቹስ ፡ ምን ፡ ብለው ፡ መከረውት ፡ ኖርዋል ?
፬ኛ ፤ አህያውስ ፡ ሲጓዝ ፡ ሳለ ፡ ማን ፡ አገኘው ?
፭ኛ ፤ አግኝቶስ ፡ ምን ፡ አደረገው ?
፮ኛ ፤ በመጨረሻው ፡ ምን ፡ ሆነ ?

# ምስክር ::

ከዚህ ፡ ከበረሃ ፡ ከሜካ ፡ ውስጥ ፡ ብቻህን ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ? አሁን ፡ ብገልህ ፡ ደምህን ፡ የሚያወጣልህ ፡ ማነው ?

ባትገድለኝ ፡ ደግ ፡ ነበር ። ያውስ ፡ ምን ፡ ሠራሁህና ፡ ትገድለኛለህ ?

ይልቅ ፡ ለጠየቅሁህ ፡ መልስ ፣ ብገድልህ ፡ ማነው ፡ ደምህን ፡ የሚያወጣልህ ?

ደሜን ፡ የሚያወጣልኝ ? እግዚአብሔር ፣ መሬትና ፡ ንጉሥ ፡ ናቸው ።

ይሁን ፡ እነርሱ ፡ ደምህን ፡ ሲያወጡልህ ፡ እያለሁ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ እንደተናገረው ፡ ወዲያው ፡ በሰውዮው ፡ ላይ ፡ ተነሣበትና ፡ ገደለው ። ሬሳውንም ፡ አፈር ፡ አለባብሶ ፡ መንገዱን ፡ ሄደ ።

ይህ ፡ በሆነ ፡ በብዙ ፡ ዘመን ፡ እግር ፡ ጥሎት ፡ ሰውዮውን ፡ ከቀበረበት ፡ ቦታ ፡ ቢደርስ ፡ ትርንጎ ፡ አብቅሎ ፣ አፍርቶ ፡ አገኘው ። ይህንስ ፡ ለንጉሥ ፡ ቢያበረክቱት ፡ የሚያስመሰግን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቆርጦ ፡ በስልቻ ፡ አሰናድቶ ፡ ተሸክሞ ፡ ለንጉሥ ፡ ንገሩልኝ ፣ በረከት ፡ የሚሆን ፡ ይዤለሁ ፡ አለ ። ነገሩለት ። ገብቶም ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ! ላንተ ፡ የሚገባ ፡ መልካም ፡ ትርንጎ ፡ ይዤለሁ ፡ ብሎ ፡ ከስልቻው ፡ ቢያወጣው ፡ የሰው ፡ ጭንቅላት ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። ሁለቱም ፡ ደነገጡ ።

ንጉሡም ፡ መጀመሪያ ፡ ትርንጎ ፡ አመጣሁልህ ፡ ብለህ ፡ ተናግረህ ፡ ነበር ፡ የት ፡ አለ ? ብሎ ፡ ጠየቀው ። ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የሠራውን ፡ ኃጢአት ፡ ገልጾ ፡ ተናገሮ ፡ ከንጉሡ ፡ ይቅርታ ፡ ለመነ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ ላንተ ፡ ይቅርታ ፡ ባደርግልህ ፡ እኔን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ይቅር ፡ ይለኛል ። ይኸነንማ ፡ መቼ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የፈረድሁብህ ፡ ሥራህ ፡ ፈረደብህ ፡ እንጂ ፡ ብሎ ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ አስገደለው ።

አሁንም ፡ ሁልጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አይለየንም ። የሰውንም ፡ ደም ፡ በከንቱ ፡ ማፍሰስ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ። የሰው ፡ ደም ፡ በአምላክ ፡ ፊት ፡ ስትጮህ ፡ ትገኛለች ። እሱም ፡ ስለ ፡ ቃየልና ፡ ስለ ፡ አቤል ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይፈጸምበታል ።



ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ተመልከቱ ፣ ከንቱን ፡ ነገር ፡ አትከተሉ ፣ ጥበብን ፡ ብትከተሉ ፡ ደግ ፡ ሥራን ፡ ትመራችኋለች ።

ምሳሌ ፣ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ባይወርድ ፣ ለድኃ ፡ ይፈርድ ።

ጥያቄ ።

፩ኛ ፣ ነፍስ ፡ በመግደል ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ይመጣል ?
፪ኛ ፣ እግዚአብሔርስ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ይፈርዳል ?
፫ኛ ፣ ንጉሥ ፡ እንዴት ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሊጠብቅ ፡ ይችላል ?

# ጣዖት ::

አንድ ፡ አናጢ ፡ ሥራው ፡ ዕንጨት ፡ መጥረብ ፣ ጣኦት ፡ ማነጽ መሸጥ ፣ መለወጥ ፡ ነበረ ። እሱም ፡ ራሱ ፡ በእጁ ፡ በሠራው ፡ ያመልከበታል ። አንድ ፡ ልጅ ፡ ነበረውና ፡ ያንኑ ፡ ጣኦቱን ፡ ገሚሱን ፡ ከቤት ፡ ዘግቶ ፡ እኩሌታውን ፡ ለመሸጥ ፡ አውጥቶ ፡ እገባያ ፡ ለመሄድ ፡ ልጂ ፡ ሆይ ፡ እነዚህን ፡ አማልክቶቼን ፡ ስትጠብቅ ፡ ቆየኝ ፡ እኔ ፡ ይህነን ፡ ሸጬ ፡ እፍኝ ፣ ዝግኝ ፣ ጥርኝ ፡ የምትሆን ፡ እህል ፡ ገዝቼ ፡ እመጣለሁ ፡ ያንን ፡ አንተም ፡ እናትህም ፡ ሁነን ፡ እንቃመሳለን ፣ ደኅና ፡ ዋል ፡ ልጂ ፡ ብሎት ፡ ተሰነባብተው ፡ ወደ ፡ ገበያው ፡ ሄደ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ያንን ፡ ጣኦት ፡ ቤቱን ፡ ከፍቶ ፡ ገብቶ ፡ ትልቁን ፡ ጣኦት ፡ ብቻ ፡ ትቶ ፡ ትንሹን ፡ ሰባብሮ ፡ ቆየው ።

አባትዮውም ፡ ከገባያ ፡ ሲመለስ ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ቢመለከት ፡ ትልቁ ፡ ብቻ ፡ ቀርቶ ፡ ትንንሾቹ ፡ ጣኦቶች ፡ ተሰባብረው ወድቀው ፡ ቢያገኛቸው ፡ አዝኖ ፣ ተክዞ ፡ ልጁን ፡ አማልክቶቼን ፡ ጠብቅ ፡ ብዬህ ፡ ብሄድ ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ሰባብሮ ፡ የጣላቸው ፡ ማነው ፡ አለው ።

ልጁም ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ዐውቄ ፡ ያ ፡ ትልቁ ፡ ጣኦትህ ፡ ሰብሮ ፡ ጥሏቸው ፡ ይሆናል ። ገብተህ ፡ አትጠይቀውምን ፡ ? አለው ። እሱም ፡ ገብቶ ፡ ትልቁ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፣ ትንንሾቹን ፡ ማነው ፡ የሰባበ

ራቸው ፡ በል ፡ ንገረኝ ፡ እያለ ፡ ሲያገላብጠው ፡ ልጁ ፡ ከውጪ ፡
ቁሞ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ አምላክህ ፡ ፈዘኛ ፡ ነውና ፡ ተለግሞ ፡
ይሆናል ፡ በቅጡ ፡ ጠይቀው ። አባቴ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ አምላክህ ፡
እርቦት ፡ ይሆናል ፡ ምሳውን ፡ አብላው ፡ ሲለው ፤ አባቱ ፡ ተቆጥቶ ፡
ወደ ፡ እሱ ፡ ቢመጣበት ፡ ከዚያ ፡ ሸሽቶ ፡ ሄደ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲገባለት ፡ ከዚያው ፡
ከጣኦቱ ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ የአባቴን ፡ አምላክ ፡ የሰበርህ ፡ አንተ ፡
ነህ ? ንገረኝ ፡ እያለ ፡ እያነጣ ፡ ሲወረውረው ፡ በእግሩ ፡ ሲረግ
ጠው ፡ ቆይቶ ፡ በመንደርና ፡ በገበያ ፡ እያዞረ ፡ ጣኦት ፡ ዋጁ ፤ ዦሮ ፡
ያለው ፡ የማይሰማ ፡ አምላክ ፡ ግዙ ፤ ዐይን ፡ ያለው ፡ የማያይ ፡ እያለ
ሲያዞረው ፡ ውሎ ፡ አንድ ፡ የሚጠይቀው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ አጣ ፡ ከአ
ንዲት ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ አግብቶ ፡ የአባቴ ፡ አምላክ ፡ ራበኝ ፡ አብ
ላኝ ፡ የአባቴ ፡ ጣኦት ፡ ውሃ ፡ ጠማኝ ፡ አጠጣኝ ፡ እያለ ፡ ሲያላግ
ጥበት ፡ ውሎ ፡ ከዚያው ፡ ከጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ሰባብሮ ፡ ጥሎት ፡
ተመለሰ ።

ልጆቼ ፡ ሆይ ፤ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ ማምለክ ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፡
ከዚህ ፡ መራቅ ፡ ያስፈልጋል ።

እግዚአብሔርም ፡ እኔ ፡ አምላካችሁ ፡ ቀናተኛ ፡ ነኝና ፡ ሌላ ፡
ባዕድ ፡ አምላክ ፡ አታምልኩ ፡ ብሎ ፡ አዝዞናል ።

ጥያቄ ።

፩ኛ ፤ የአናጢ ፡ ሥራው ፡ ምንድር ፡ ነው ?
፪ኛ ፤ ጣኦት ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ?
፫ኛ ፤ አባትየው ፡ እገበያ ፡ ሲሄድ ፡ ልጁን ፡ ምን ፡ ብሎ ፡
አዘዘው ?
፬ኛ ፤ ልጁስ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ቆየው ።
፭ኛ ፤ ከ፲ቱ ፡ ቃላት ፡ ባንደኛው ፡ ምን ፡ ያዝዘናል ?



# ብልጠት ::

ከእንግሊዝ ፡ መጽሐፍ ፡ የተተረጐመ ፡ ምሳሌ ።

ባንድ ፡ ትንሽ ፡ ድንኳን ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። አንድ ፡
ቀንም ፡ አንዲት ፡ ግመል ፡ ትንሽቱን ፡ ድንኳን ፡ ከሩቅ ፡ አይታ ፡
ወደ ፡ ርስዋ ፡ መጣች ። ከድንኳኒቷም ፡ ውጭ ፡ በጣም ፡ ብርድ ፡ ነበ
ርና ፡ የምትጠጋበት ፡ አጥታ ፡ ተጨንቃ ፡ ነበር ። ከድንኳኒቷ ፡
ውስጥ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ሙቀትና ፡ ብዙ ፡ ምቾት ፡ ነበረ ።
ግመሊቷም ፡ ወደዚያች ፡ ድንኳን ፡ ጠጋ ፡ ብላ ፡ ሰውዮውን ፡
በውስጡ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ታመሰግነውና ፡ በጥሩ ፡ ስፍራ ፡ መሆኑን ፡
ትነግረው ፡ ጀመረች ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሰውዮው ፡ ምስጋናውንና ፡
በጥሩው ፡ ስፍራ ፡ መሆኑን ፡ ሰምቶ ፡ ዝም ፡ ባላት ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ዕፍ
ረት ፡ በግልጽ ፡ እባክህ ፡ አፍንጫዬን ፡ ብቻ ፡ ወደዚች ፡ ድንኳን ፡
ውስጥ ፡ እንዳስገባና ፡ ትንሽ ፡ ሞቅ ፡ እንዲለኝ ፡ ፍቀድልኝ ፡ አለ
ችው ።
የሰውዮውም ፡ ልቡ ፡ ገር ፤ ርኅሩኅ ፤ ቀና ፡ ነበርና ፡ አንቺ ፡ ድኃ
በብርድ ፡ የምትሣቀዪ ፡ ግመል ፡ ብሎ ፡ በጣም ፡ አዝኖ ፡ አካላት
ሽን ፡ ሁሉ ፡ እንዳታስገቢ ፤ እንደምታዪው ፡ ድንኳኔ ፡ በጣም ፡ ትንሽ
ናት ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ እንዳልሺው ፡ አፍንጫሽን ፡ ለማስገባትና ፡ ከብ
ርድ ፡ ለመዳን ፡ በደስታ ፡ እፈቅድልሻለሁ ፡ ብሎ ፡ አፍንጫዋን ፡
ከድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ እንድታስገባ ፡ ፈቀደላት ።
ከድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ሙቀት ፡ ስፍራ ፡ እንዳለ ፡
አየችና ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ታግሣ ፡ ሌላውን ፡ አካላቱዋን ፡ ለማስገባ
ት ፡ ያልተጣጣረች ፡ መስላ ፡ ቆየት ፡ ብላ ፡ እባክህ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡
ራሴን ፡ ሁሉ ፡ ከድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ላስገባ ፡ አለች ። ሰውዮውም ፡
እሰበና ፡ ለግመሉዋ ፡ ራስ ፡ የሚሆን ፡ ስፍራ ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ እሺ ፡
ራስሽንም ፡ ከድንኳኔ ፡ ውስጥ ፡ እንድታስገቢና ፡ ከብርድ ፡ እንድ
ትድኚ ፡ እፈቅድልሻለሁ ፡ አላት ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በራሷ ፡ የድንኳኑን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሽቅብ ፡
ገፍታ ፡ እስከ ፡ አንገቷ ፡ ገብታ ፡ የፊት ፡ እግሮቼን ፡ ለማስገባት ፡
አትፈቅድልኝም ፡ ወይ ፡ አለችው ። ያም ፡ ለራሱ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡
ከመፈለግና ፡ ከማሰብ ፡ በተቀር ፡ በኋላ ፡ የሚመጣበትን ፤ ተንቅሎ ፡

መውደቁን ፡ የማያውቅ ፡ ቀና ፡ ሰው ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ መዛወር ፡ ወይ ም ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ መቀመጥ ፡ እስኪቸግረው ፡ ድረስ ፡ በዚያች ፡ ጠባብ ፡ ድንኳን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ተጠግቶ ፡ ተኛ ።

ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ እኩል ፡ አካሏ ፡ ከገባና ፡ ከተመቻት ፡ ስፍራውንም ፡ ከያዘች ፡ በኋላ ፡ ልመናውን ፡ ትታ ፡ በኀይል ፡ ያላንድ ፡ ጥያቄ ፡ አካላቷን ፡ ሁሉ ፡ አስገባች ። ያቺን ፡ የምትሞቅ ፡ ጥሩ ፡ የነበረች ፡ ድንኳኑንም ፡ አበላሽታ ፡ ሽቅብ ፡ አንሥታ ፡ ሰለ ፡ ለበሰቻት ፡ ባለድንኳኑ ፡ ሰውዮ ፡ ከግመል ፡ ጋራ ፡ መጋፋቱንና ፡ መንገቱን ፡ ተመርሮ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ብርዱ ፡ ወድቆ ፡ መከራውን ፡ ይቀበል ፡ ጀመር ። ያቺም ፡ ጥሩ ፡ ድንኳን ፡ የግመሏ ፡ ሆና ፡ ቀረች ።

ወይ ፡ ንዴት ? ያ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ተጠንቅቆ ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ ባልደረሰም ፡ ነበር ።

## አ ቡ ጊ ዳ ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ቡ | ጊ | ዳ | ሄ | ው | ዞ |
| በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ዦ |
| ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ዥ | ሖ |
| ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ዤ | ሕ | ጦ |
| ሀ | ዉ | ዚ | ዣ | ሔ | ጥ | ጮ |
| ወ | ዙ | ዢ | ሓ | ጤ | ጭ | ዮ |
| ዘ | ዡ | ሒ | ጣ | ጬ | ይ | ኮ |
| ዠ | ሑ | ጢ | ጫ | ዬ | ክ | ኾ |
| ሐ | ጡ | ጪ | ያ | ኬ | ኽ | ሎ |
| ጠ | ጩ | ዪ | ካ | ኼ | ል | ሞ |
| ጨ | ዩ | ኪ | ኻ | ሌ | ም | ኖ |
| የ | ኩ | ኺ | ላ | ሜ | ን | ኞ |
| ከ | ኹ | ሊ | ማ | ኔ | ኝ | ሶ |
| ኸ | ሉ | ሚ | ና | ኜ | ስ | ሾ |
| ለ | ሙ | ኒ | ኛ | ሴ | ሽ | ዖ |
| መ | ኑ | ኚ | ሳ | ሼ | ዕ | ፎ |
| ነ | ኙ | ሲ | ሻ | ዔ | ፍ | ጾ |
| ኘ | ሱ | ሺ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ |
| ሰ | ሹ | ዒ | ፋ | ጼ | ቅ | ሮ |
| ሸ | ዑ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ሦ |
| ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ሥ | ቶ |
| ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሤ | ት | ቾ |
| ጸ | ቁ | ሪ | ሣ | ቴ | ች | ኆ |
| ቀ | ሩ | ሢ | ታ | ቼ | ኅ | ጶ |
| ረ | ሡ | ቲ | ቻ | ኄ | ጵ | ፆ |
| ሠ | ቱ | ቺ | ኃ | ጴ | ፅ | ፖ |
| ተ | ቹ | ኂ | ጳ | ፄ | ፕ | ጆ |
| ቸ | ኁ | ጲ | ፃ | ፔ | ጅ | ኦ |
| ኀ | ጱ | ፂ | ፓ | ጄ | እ | ቦ |
| ጰ | ፁ | ፒ | ጃ | ኤ | ብ | ጎ |
| ፀ | ፑ | ጂ | ኣ | ቤ | ግ | ዶ |
| ፐ | ጁ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ |
| ጀ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ |